### ልዩ ገጽታ

የማርቆስ ወንጌልን ልዩ የሚያደርጉት አራት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) ክርስቶስ በተናገረው ላይ አጽንዖት ከማድረግ ይልቅ፣ በአከናወነው ተግባር ላይ አጽንዖት በማድረጉ የተግባር ወንጌል ተብሎአል (የማርቆስ ወንጌል ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሳያመለክት ዐሥራ ስምንት ታምራትን የያዘ ሲሆን፣ አራቱን የጌታን ምሳሌዎች ብቻ አካቶ ይገኛል)። (2) የአይሁድን የትውልድ ሐረግና የትውልድ ታሪኮችን በማስቀረት፣ ባህላቸውን በመግለጽ፣ የአራማይክ ቃላትን በመተርጐም፣ የላቲን አባባሎችንም በማስገባት፣ ሮማውያንን ተደራስያን በማድረግ የተጻፈ ወንጌል ነው። (3) ከአንድ ታሪክ ወደ ሌላ ታሪክ ሲሸጋገር ድንገት ተጀምሮ በጥድፊያ በሚጓዝ፣ የግሪክን የግስ ገላጭ ማለትም፣ "ወዲያው" የሚለውን ቃል ብዙ ጊዜ (42 ጊዜ) በማስገባት ትረካን ያካተተ ወንጌል ነው። (4) የኢየሱስን የሕይወት ታሪክ ቍልጭና እጥር ምጥን አድርጎ፣ ሥዕላዊ በሆነ መልክና የሥነ ጽሑፍ ባለሙያ በተጠበበት የጥበብ ስልት የቀረበ ወንጌል ነው።

### የማርቆስ ወንጌልን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የማርቆስ ወንጌልን ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በሃያ ዘጠኝ ቀናት መነበብ ይኖርበታል፤

❑ 1፥1-20 ❑ 1፥21-45 ❑ 2፥1-22 ❑ 2፥23—3፥12 ❑ 3፥13-35 ❑ 4፥1-20 ❑ 4፥21-41 ❑ 5፥1-20 ❑ 5፥21-43 ❑ 6፥1-29 ❑ 6፥30-56 ❑ 7፥1-23 ❑ 7፥24—8፥13 ❑ 8፥14-26 ❑ 8፥27—9፥13 ❑ 9፥14-32 ❑ 9፥33-50 ❑ 10፥1-31 ❑ 10፥32-52 ❑ 11፥1-26 ❑ 11፥27—12፥17 ❑ 12፥18-44 ❑ 13 ❑ 14፥1-26 ❑ 14፥27-52 ❑ 14፥53-72 ❑ 15፥1-20 ❑ 15፥21-47 ❑ 16

ማስታወሻ

### የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

*1፥2-8 ተጓ ምብ ማቴ 3፥1-11፤*
*ሉቃ 3፥2-16*

1 የእግዚአብሔር ልጅ[ሀ]፣ የኢየሱስ ክርስቶስ
ወንጌል መጀመሪያ።
[2]በነቢዩ በኢሳይያስ፣ እንዲህ ተብሎ
ተጽፎአል፤ "እነሆ መንገድህን የሚያዘጋጅ
መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ፤ [3]"የጌታን
መንገድ አዘጋጁ፤ ጥርጊያውንም አስተካክሉ
እያለ በበረሓ የሚጮኽ ድምፅ'።"
[4]ስለዚህ መጥምቁ ዮሐንስ በበረሓ
እያጠመቀና ለኀጢአት ስርየት የንስሓ
ጥምቀት እየሰበከ መጣ። [5]የይሁዳ አገር
በሞላ፣ የኢየሩሳሌም ሰዎች በጠቅላላ ወደ
እርሱ በመሄድ ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ
በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቁ።
[6]ዮሐንስ የግመል ጠጕር ይለብስ፣ በወገቡ
ጠፍር ይታጠቅ፣ አንበጣና የበረሓ ማር
ይበላ ነበር። [7]ስብከቱም፣ "እኔ ጐንበስ ብዬ
የጫማውን ማሰሪያ መፍታት የማይገባኝ፣
ከእኔ የሚበልጥ ከእኔ በኋላ ይመጣል፤ [8]እኔ
በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ እርሱ ግን በመንፈስ
ቅዱስ ያጠምቃችኋል" የሚል ነበር።

1፥1 ማቴ4፥3
1፥2 ሚል3፥1፤ ማቴ11፥10፤ ሉቃ7፥27
1፥3 ኢሳ40፥3፤ ዮሐ1፥23
1፥4 ሥ8፤ ማቴ3፥1፤ ሉቃ1፥77፤ ዮሐ1፥26፡33፤ ሐሥ1፥5፡22፤ 11፥16፤ 13፥24፤ 18፥25፤ 19፥3፡4
1፥6 ዘሌ11፥22፤ 2ነገ1፥8
1፥7 ሐሥ13፥25
1፥8 ኢሳ44፥3፤ ኢዩ2፥23፤ ዮሐ1፥33፤ ሐሥ1፥5፤ 2፥4፤ 11፥16፤ 19፥4-6
1፥9 ማቴ2፥23፤ 3፥1
1፥10 ዮሐ1፥32
1፥11 ማቴ3፥17
1፥13 ዘፀ24፥18፤ 1ነገ19፥8፤ ማቴ4፥10፤ ዕብ4፥15
1፥14 ማቴ3፥1፤ 4፥12፡23

### የኢየሱስ መጠመቅና መፈተን

*1፥9-11 ተጓ ምብ — ማቴ 3፥13-17፤*
*ሉቃ 3፥21-22*
*1፥12፡13 ተጓ ምብ — ማቴ 4፥1-11፤*
*ሉቃ 4፥1-13*

[9]በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የገሊላ ከተማ ከሆነችው
ከናዝሬት መጥቶ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ
እጅ ተጠመቀ። [10]ከውሃው በሚወጣበትም
ጊዜ፣ ሰማያት ተከፍተው፣ መንፈስ ቅዱስ
እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ሲወርድ አየ፤
[11]"የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ
ይለኛል" የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ።
[12]ወዲያውም መንፈስ ቅዱስ ወደ በረሓ
መራው፤ [13]በሰይጣንም እየተፈተነ አርባ
ቀን በበረሓ ቈየ። ከአራዊትም ጋር ነበር፤
መላእክትም አገለገሉት።

### የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት መመረጥ

*1፥16-20 ተጓ ምብ — ማቴ 4፥18-22፤*
*ሉቃ 5፥2-11፤ ዮሐ 1፥35-42*

[14]ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ፣ ኢየሱስ
የእግዚአብሔርን ወንጌል እየሰበከ ወደ ገሊላ

[ሀ] 1፥1 አንዳንድ ቅጆች የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው ሐረግ የላቸውም።

**1፥4 ንስሓ፤** ማቴዎስ 3፥2 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**1፥5 የይሁዳ አገር በሞላ፤** የመጥምቁ ዮሐንስን አገልግሎት ተከትሎ የመጣ በይሁዳና በገሊላ አገር መንፈሳዊ መነቃቃት ነበር፤ ከዚህም የተነሣ በተራው (በብዙኀኑ) ሕዝብ ዘንድ የእስራኤል መንፈሳዊ ሁኔታ ተለወጠ፣ ይህም እግዚአብሔር ሥጋው በሆነው ልጁ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሙሉ በሙሉ ይገለጽ ዘንድ አስተዋፅኦ አደረገ።

**1፥8 በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል፤** ስለ ኢየሱስ የምሥራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰበከ መጥምቁ ዮሐንስ ነው። ስብከቱም በወንጌላዊው በማርቆስ አማካይነት በአንድ ዐቢይ ሐሳብ ዙሪያ ላይ ዕጥር ምጥን ብሎ ቀርቦአል፤ ይኸውም የሚመጣውና በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው ኢየሱስ መሆኑን በማወጅ ነው። ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርገው የተቀበሉ ሁሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው፣ አሁንም እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ማወጅ አለባቸው (ሐሥ 1፥8፤ 2፥4፡38-39፤ በሉቃ 3፥16 ላይ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅ የተሰጠውን ተስፋ ማብ ይመ፤ ሐሥ 1፥5 እና ማብ ይመ)።

**1፥9 ኢየሱስ ... ተጠመቀ፤** ማቴ 3፥13 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**1፥10 መንፈስ ቅዱስ ... በእርሱ ላይ ሲወርድ፤** ማቴ 3፥16 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**1፥11 የምወድህ ልጄ፤** በኢየሱስ ጥምቀት ላይ ሦስቱም የሥላሴ አካላት ተሳታፊዎች ናቸው (ማቴ 3፥17 እና ማብ ይመ)። በዚህ ላይና በሌላውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር አንድ መለኮት ሆኖ፣ በሦስት አካላት የተገለጠ ሲሆን ሦስቱም የጋራ የመለኮት ባሕርይ አላቸው፤ ሦስቱም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው (ከማቴ 3፥16-17፤ 28፥19፤ ከ2ቆሮ 13፥14፤ ከኤፌ 4፥4-6፤ ከ1ጴጥ 1፥2፤ ከይሁ 20፥21 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ እግዚአብሔር በአንድ በኩል አንድ ነው (ይኸውም አንድነት አለው)፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሦስትነት አለው (በገጽ 908 ላይ፣ "የእግዚአብሔር ባሕርያት" የሚለውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (1) መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድ ባሕርይ፣ አንድ መለኮትና ፍጹም አንድነት ያለው አምላክ መሆኑን ያውጃል (12፥29፤ ዘዳ 6፥4፤ ገላ 3፥20)። ከሦስቱ የሥላሴ አካላት ውስጥ አንዱ ያለ ሌላው አምላክ አይደለም፤ እያንዳንዱ አካል ከሌሎቹ ጋር አምላክ ነው።

(2) ሦስቱ የተለያዩ ባይሆኑም እንኳ፣ አንዱ አምላክ፣ ጕልሕ በሆኑ፣ የየራሳቸው መለዮ ባላቸው አካላት አለ። ሦስቱ፣ ሦስት መለኮትና አይደሉም፤ ወይም ደግሞ ሦስት ቅርንጫፎች ወይም ሦስት መለኮትና መገለጫዎች አይደሉም፤ ነገር ግን ሦስት አካላት ሆነው አንዱና ዘላለማዊው አምላክ ናቸው። ወልድና መንፈስ ቅዱስ ያሏቸው ባሕርያት ለእግዚአብሔር ብቻ የሆኑ ባሕርያት ነው (ዘፍ 1፥2፤ ኢሳ 61፥1፤ ዮሐ 1፥1፡14 እና ማብ፤ 5፥18 እና ማብ፤ 14፥16፤ 16፥8፡13፤ 20፥28 እና ማብ፤ ሐሥ 5፥3-4፤ ሮሜ 8፥2፡26-27፤ 1ቆሮ 2፥10-11፤ 2ተሰ 2፥13፤ ዕብ 9፥14 ይመ)። ከሦስቱ አካላት አንዱም እንኳ ከቶ አልተሠራም ወይም አልተፈጠረም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ተተካካይ በሆነ አካል፣ ባሕርይ፣ ኀይልና ክብር ይኖራል።

(3) ይህ በሦስት አካላት የሚገኘው አንድ አምላክ፣ በአካላቱ መካከል ዘላለማዊ የሆነ የእርስ በርስ ፍቅር፣ ኅብረት፣ መለኮታዊ ባሕርይ፣ የጋራ የሆነ ዕውቀትና የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲኖር አድርጎአል (ከዮሐ 10፥15፤ 11፥27፤ 17፥24፤ ከ1ቆሮ 2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**1፥13 በሰይጣንም እየተፈተነ፤** ማቴ 4፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**1፥14 ወንጌል፤** 14፥9 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

ተከትለውት ስለ ነበር፣ ከኢየሱስና
ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ይመገቡ ነበር።
16ከፈሪሳውያን ወገን የነበሩ ጸሐፍት
ከኃጢአተኞችና ከቀረጥ ሰብሳቢዎች ጋር
ሲበላ ባዩት ጊዜ፣ ደቀ መዛሙርቱን "ከቀረጥ
ሰብሳቢዎችና ከኃጢአተኞች ጋር ለምን
ይበላል?" ሲሉ ጠየቋቸው።
17ኢየሱስም የሚናገሩትን ሰምቶ፣
"ሐኪም የሚያስፈልጋቸው ሕመምተኞች
እንጂ ጤነኞች አይደሉም፤ እኔ
ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ወደ ንስሓ
ልጠራ አልመጣሁም" አላቸው።

## ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ

*2፥18-22 ተጓ ምብ — ማቴ 9፥14-17፤*
*ሉቃ 5፥33-38*

18የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን
ይጾሙ ነበር፤ አንዳንድ ሰዎችም መጥተው
ኢየሱስን፣ "የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ
መዛሙርት ሲጾሙ፣ የአንተ ደቀ መዛሙርት
የማይጾሙት ለምንድን ነው?" አሉት።
19ኢየሱስም፣ እንዲህ አላቸው፤
"ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ
ሊጾሙ ይችላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ
ጋር እያለ ሊጾሙ አይችሉም፤ 20ሙሽራው
ከእነርሱ የሚወሰድበት ወቅት ይመጣል፤
በዚያን ጊዜ ግን ይጾማሉ።
21"በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ ጨርቅ
የሚጥፍ ማንም የለም፤ ይህ ቢደረግ ግን፣
አዲሱ ጨርቅ አሮጌውን ይቦጭቀዋል፤
ቀዳዳውም የባሰ ይሰፋል። 22እንዲሁም
አዲስ የወይን ጠጅ በአሮጌ አቍማዳ
የሚያስቀምጥ የለም፤ ይህ ከተደረገማ
የወይን ጠጁ አቍማዳውን ያፈነዳዋል፤
የወይን ጠጁም አቍማዳውም ይበላሻሉ።
ስለዚህ አዲስ የወይን ጠጅ መቀመጥ ያለበት
በአዲስ አቍማዳ ነው።"

## ኢየሱስ የሰንበት ጌታ ነው

*2፥23-28 ተጓ ምብ — ማቴ 12፥1-8፤*
*ሉቃ 6፥1-5*
*3፥1-6 ተጓ ምብ — ማቴ 12፥9-14፤*
*ሉቃ 6፥6-11*

23በሰንበት ቀን ኢየሱስ በእርሻ መካከል
ሲያልፍ፣ አብረውት በመንገድ ላይ የነበሩት
ደቀ መዛሙርቱ እሸት ይቀጥፉ ጀመር።
24ፈሪሳውያንም፣ "እነሆ፤ በሰንበት ቀን
ለምን የተከለከለ ነገር ያደርጋሉ?" ሲሉ
ጠየቁት።
25እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ዳዊት
በተራበና የምግብ ፍላጎት በጸናበት ጊዜ
አብረውት ከነበሩት ሰዎች ጋር ያደረገውን
አላነበባችሁምን? 26በሊቀ ካህናቱ በአብያታር
ዘመን ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብቶ፣ ካህናት
ብቻ እንዲበሉት የተፈቀደውን የተቀደሰ
ኅብስት ራሱ በልቶ አብረውት ለነበሩትም
ሰዎች ሰጣቸው።"
27ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ "ሰንበት
ለሰው ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለሰንበት
አልተፈጠረም፤ 28ስለዚህ የሰው ልጅ
የሰንበት ጌታዋ ነው።"
3 በሌላ ጊዜ ወደ ምኵራብ ገባ፤ በዚያም እጁ
የሰለለች ሰው ነበር። 2በምክንያት ሊከሱት
የሚፈልጉ ሰዎችም በሰንበት ቀን ይፈውሰው
እንደ ሆን ለማየት ይጠባበቁ ነበር። 3እርሱም
እጁ የሰለለችውን ሰው፣ "በተሰበሰበው
ሕዝብ ፊት ተነሥተህ ቁም" አለው።
4ኢየሱስም፣ "በሰንበት ቀን የተፈቀደው
መልካም ማድረግ ነው ወይስ ክፉ? ሕይወት
ማዳን ነው ን ወይስ ማጥፋት?" አላቸው።
እነርሱ ግን ዝም አሉ።
5በልባቸው ደንዳናነት አዝኖ በዙሪያው
የቆሙትን በቍጣ ተመለከታቸውና
ሰውየውን፣ "እጅህን ዘርጋ!" አለው፤
ሰውየውም እጁን ዘረጋ፤ እጁም ፍጹም
ደኅና ሆነችለት።
6ፈሪሳውያንም እንዴት ሊያጠፉት
እንደሚችሉ ከሄሮድስ ወገን ከሆኑት ጋር
መመካከር ጀመሩ።

## ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ተከተሉ

*3፥7-12 ተጓ ምብ — ማቴ 12፥15-16፤*
*ሉቃ 6፥17-19*

7ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ
ባሕሩ ሄደ፤ ከገሊላ የመጣ እጅግ ብዙ
ሕዝብም ተከተለው፤ 8የሚሠራውን ነገር
የሰሙ ሰዎችም ከይሁዳ፣ ከኢየሩሳሌም፣
ከኤዶምያስ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ካለው አገር
እንዲሁም ከጢሮስና ከሲዶና አካባቢ ወደ

2፥16 ሐሥ23፥9፤ ማቴ9፥11
2፥17 ሉቃ19፥10፤ 1ጢሞ1፥15
2፥18 ማቴ6፥16-18፤ ሐሥ13፥2
2፥20 ሉቃ17፥22
2፥23 ዘዳ23፥25
2፥24 ማቴ12፥2
2፥26 ዘሌ24፥5-9፤ 1ሳሙ21፥1-6፤ 2ሳሙ8፥17፤ 1ዜና24፥6
2፥27 ዘፀ23፥12፤ ዘዳ5፥14፤ ቈላ2፥16
2፥28 ማቴ8፥20
3፥1 ማቴ4፥23፤ ሉቃ1፥21
3፥2 ማቴ12፥10፤ ሉቃ14፥1
3፥6 ማቴ12፥14፤ 22፥16፤ ማር12፥13
3፥7 ማቴ4፥25
3፥8 ማቴ11፥21

**2፥17 ኃጢአተኞችን እንጂ … ልጠራ፤** ማቴ 9፥11 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**2፥20 በዚያን ጊዜ ግን ይጾማሉ፤** ማቴ 9፥15 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**2፥22 አዲስ የወይን ጠጅ በአሮጌ አቍማዳ፤** ማቴ 9፥17 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**2፥23 በሰንበት ቀን፤** ማቴ 12፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**2፥27 ሰንበት ለሰው ተፈጠረ እንጂ፤** ሰንበት ለሰው ልጅ በረከት እንዲሆን እግዚአብሔር የፈቀደው ቀን ነው (ዘፀ 20፥8 እና ማብ ይመ)። በዚህ ቀን ከዕለት ሥራችን መታቀብ ይኖርብናል። በምትኩ ግን ጤንነታችን እንዲጠበቅ፣ በመንፈስ እንድንጠነክርና እንድንታደስ፣ እግዚአብሔርን ማምለክና ከእርሱም ጋር ኅብረት ይኖረን ዘንድ መሻት ይኖርብናል (ኢሳ 58፥13-14)። ሰንበት እንዲከበር የተሰጠውን መርሕ ችላ የሚሉ ሁሉ በራሳቸው ላይ ጥፋትን ይጋብዛሉ (ማቴ 12፥1 እና ማብ ይመ)።

**3፥5 በቍጣ ተመለከታቸውና፤** የኢየሱስ ቍጣ፣ ጌታ የሆነው እርሱ፣ ጽድቅ አልባና ፍትሕ አልባ የሆነውን ሁሉ እንደሚጠላና እንደሚጸየፍ ያሳያል (ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)። ክርስቲያኖች፣ ጽድቅ አልባ ከሆነው ቍጣ መራቅ ቢኖርባቸውም (ገላ 5፥20፤ ቈላ 3፥8)፣ ክፉ በሆነው ነገር ላይ ቍጣ ማሳየታቸው፣ ክርስቶስን መምሰል ነው (ዘፀ 32፥19፤ 1ሳሙ 11፥6፤ 2ሳሙ 12፥5፤ ነህ 5፥6)። ትውልድ በሚሠራው ኀጢአት ላይ አማኞች ቍጣን መግለጻቸው፣ ከእግዚአብሔር ጐን ሆነው ክፋትን ለመዋጋታቸው ማስረጃ ነው (ዘፀ 32፥19፤ 1ሳሙ 11፥6፤ መዝ 94፥16፤ ኤር 6፥11፤ ሐሥ 17፥16)።

እርሱ መጡ። [9]የተሰበሰበውም ሕዝብ
እንዳያጨናንቀው አነስተኛ የሆነ ጀልባ
እንዲያዘጋጁለት ደቀ መዛሙርቱን
አዘዛቸው። [10]ብዙዎችን ፈውሶ ስለ ነበር፣
በሕመም የሚሠቃዩ ሁሉ ሊዳስሱት
ይሽቀዳደሙ ነበር። [11]ርኩሳን* መናፍስትም
ባዩት ቍጥር፣ ከፊቱ እየወደቁ፣ "አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!" በማለት ይጮኹ
ነበር። [12]እርሱ ግን ማንነቱን እንዳይገልጹ
አጥብቆ ይገሥጻቸው ነበር።

## የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መሾም

*3፥16-19 ተጓ ምብ — ማቴ 10፥2-4፤
ሉቃ 6፥14-16፤ ሐሥ 1፥13*

[13]ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጥቶ
የሚፈልጋቸውን ወደ እርሱ እንዲመጡ
ጠራቸው፤ እነርሱም ወደ እርሱ መጡ።
[14]ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከትም
ይልካቸው ዘንድ ዐሥራ ሁለቱን ሾማቸው፤
ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው*፤ [15]አጋንንትን
እንዲያስወጡም ሥልጣን ሰጣቸው።
[16]የሾማቸውም ዐሥራ ሁለቱ እነዚህ
ናቸው፤ ጴጥሮስ ብሎ የጠራው ስምዖን፣
[17]ቦአኔርጌስ ይኸውም፣ 'የነጐድጓድ
ልጆች' ብሎ የጠራቸው የዘብዴዎስ ልጆች
ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ፤ [18]እንድርያስ፣
ፊልጶስ፣ በርቶሎሜዎስ፣ ማቴዎስ፣ ቶማስ፣
የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ታዴዎስ፣
ቀናተኛው ስምዖን፣ [19]እንዲሁም አሳልፎ
የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ።

## ኢየሱስና ብዔል ዜቡል

*3፥23-27 ተጓ ምብ — ማቴ 12፥25-29፤
ሉቃ 11፥17-22*

[20]ከዚያም ኢየሱስ ወደ አንድ ቤት ገባ፤
እርሱና ደቀ መዛሙርቱ ምግብ መብላት
እንኳ እስኪሳናቸው ድረስ ሕዝቡ እንደ
ገና በብዛት ተሰበሰበ። [21]ሁኔታውን የሰሙ
ዘመዶቹም፣ "አእምሮውን ስቶአል" በማለት
ይዘውት ለመሄድ ወዳለበት መጡ።

3፥10 ማቴ4፥23፤ 9፥20
3፥11 ማቴ1፥23:24፤ 4፥3
3፥12 ማቴ8፥4፤ ማር1፥24:25:34፤ ሐሥ16፥17:18
3፥13 ማቴ5፥1
3፥14 ማር6፥30
3፥15 ማቴ10፥1
3፥16 ዮሐ1፥24
3፥20 ቍ 7፤ ማር6፥31
3፥21 ዮሐ10፥20፤ ሐሥ26፥24
3፥22 ማቴ9፥34፤ 10፥25፤ 11፥18፤ 12፥24፤ 15፥1፤ ዮሐ7፥20፤ 8፥48:52፤ 10፥20
3፥23 ማር4፥2:10
3፥27 ኢሳ49፥24:25
3፥29 ማቴ12፥31:32፤ ሉቃ12፥10
3፥31 ቍ 21

[22]ከኢየሩሳሌም የመጡ ጸሐፍትም፣
"ብዔል ዜቡል* አድሮበታል፤ አጋንንትን
የሚያወጣው በአጋንንት አለቃ ነው" አሉ።
[23]እርሱም ጠራቸውና በምሳሌ እንዲህ
አላቸው፤ "ሰይጣን ሰይጣንን እንዴት
ሊያስወጣ ይችላል? [24]እርስ በርሱ
የሚከፋፈል መንግሥት ሊጸና አይችልም፤
[25]ቤትም እርስ በርሱ ከተለያየ ሊቆም
አይችልም። [26]እንደዚሁም ሰይጣን እርስ
በርሱ የሚቃረርና የሚከፋፈል ከሆነ ሊቆም
አይችልም፤ ያበቃለታል። [27]ከዚህም የተነሣ
አንድ ሰው አስቀድሞ ኀይለኛውን ሰው
ሳያስር ወደ ኀይለኛው ሰው ቤት ሊገባና
ንብረቱን ሊዘርፍ አይችልም፤ ቤቱን
መዝረፍ የሚቻለው ኀይለኛውን ሰው ማር
ሲያስር ብቻ ነው። [28]እውነት እላችኋለሁ፤ 5፥1-16
የሰው ልጆች ኀጢአትና የሚሳደቡት ስድብ
ሁሉ ይሰረይላቸዋል፤ [29]ነገር ግን በመንፈስ
ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ
የዘላለም ኀጢአት ዕዳ ይሆንበታል እንጂ
ለዘላለም አይሰረይለትም።"
[30]ይህንንም ያለው፣ "ርኩስ መንፈስ
አለበት" ስላሉት ነበር።

## የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ

*3፥31-35 ተጓ ምብ — ማቴ 12፥46-50፤
ሉቃ 8፥19-21*

[31]ከዚህ በኋላ እናቱና ወንድሞቹ
መጡ፤ በውጭ ቆመውም ሰው ልከው በት
አስጠሩት። [32]በዙሪያው የተቀመጡ ብዙ
ሰዎችም፣ "እነሆ፤ እናትህና ወንድሞችህ
ውጭ ይፈልጉሃል" አሉት።
[33]እርሱም መልሶ፣ "እናቴ ማን ናት
ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?" አላቸው።
[34]በዙሪያው ወደ ተቀመጡትም
በመመልከት፣ እንዲህ አለ፤ "እናቴና

*3፥11 ወይም ክፉ፤ እንዲሁም ቍ 30 ይመ
*3፥14 አንዳንድ ቅጆች ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው የሚለው ሐረግ የላቸውም
*3፥22 ግሪኩ ብኤዜቡል ወይም ብኤልዜቡል ይላል

**3፥10 ብዙዎችን ፈውሶ፤** በገጽ 1433 ላይ፣ *"መለኮታዊ ፈውስ"* የሚለውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**3፥15 አጋንንትን እንዲያስወጡም ሥልጣን ሰጣቸው፤** ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ ዐላማው የዲያብሎስን ሥራ በማፍረስ (1፥27፤ 1ዮሐ 3፥8)፣ በሰይጣንና በኀጢአት የተገዙትን ነጻ ለማውጣት ነው (ሉቃ 4፥18 ይመ፤ በገጽ 1499 ላይ፣ *"በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ኢየሱስ ከጨለማ ኀይላት ጋር ያለውን ጦርነት ይገፉበት ዘንድ ለደቀ መዛሙርቱ ኀይልንና ሥልጣንን ሰጣቸው። ይህም እውነት በሚከተሉት አስተውሎቶች ተረጋግጦአል፤
(1) ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ከሾመ በኋላ፣ "አጋንንትን እንዲያስወጡ" ሥልጣን እንደ ሰጣቸው ተጽፎአል (ቍ 14፥15 ይመ፤ ከማቴ 10፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። ሰባ ሁለቱን ከሾመ በኋላም፣ "በጠላትም ኀይል ሁሉ ላይ ሥልጣን" ሰጣቸው (ሉቃ 10፥1፡17-19 ይመ፤ ከማቴ 10፥1-8፤ ከማር 6፥7፡13 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ደቀ መዛሙርቱ ሄደው ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን (ቍ 14፤ ማቴ 10፥7)፣ ከሰይጣን ጋር በመዋጋት፣ አጋንንትን በማስወጣት፣ የታመሙትን ከማንኛውም በሽታና ደዌ በመፈወስ (ማቴ 10፥1፡7-8 እና ማብ ይመ)፣ የመንግሥቱን አገዛዝ፣ ኀይልና ሥልጣን ይፉ ማድረግ ነበረባቸው።

(3) ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ወንጌልን የመስበክ ሥራቸውን፣ በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጣቸውንም ሥልጣን ለደቀ መዛሙርቱ ዳግም ያጸናላቸው ስለ መሆኑ ማርቆስ ያስተምራል (በገጽ 1527 ላይ፣ *"አማኞች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች"* የሚለውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥27 ኀይለኛውን ሰው ሳያስር፤** በገጽ 1499 ላይ፣ *"በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**3፥29 በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር፤** ማቴ 12፥31 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው!" [35]የእግዚአብሔርን
ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ፣
እኅቴ፣ እናቴም ነውና።"

## የዘሪው ምሳሌ

*4፥1-12 ተጓ ምብ — ማቴ 13፥1-15፤*
*ሉቃ 8፥4-10*
*4፥13-20 ተጓ ምብ — ማቴ 13፥18-23፤*
*ሉቃ 8፥11-15*

**4** በሌላ ጊዜ ደግሞ በባሕሩ አጠገብ
ያስተምር ጀመር። እርሱ ባለበት አካባቢ
እጅግ ብዙ ሕዝብ ስለ ተሰበሰበ፣ በባሕሩ
ላይ ወዳለች ጀልባ ገብቶ ተቀመጠ፤
ሕዝቡም ሁሉ በባሕሩ ዳርቻ ባለው
ስፍራ ላይ ተሰብስቦ ነበር። [2]እርሱም
ብዙ ነገሮችን በምሳሌ አስተማራቸው፤
እንዲህም አላቸው፤ [3]"ስሙ፤ አንድ ዘሪ
ዘር ሊዘራ ወጣ። [4]ዘሩን በሚዘራበትም ጊዜ
አንዳንዱ መንገድ ላይ ወደቀ፤ ወፎችም
መጥተው ለቀሙት። [5]ሌላው በቂ
ዐፈር በሌለበት በጭንጫ ቦታ ላይ ወደቀ፤
ዐፈሩ ጥልቀት ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤
[6]ፀሓይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፤ ሥር
ስላልነበረውም ደረቀ። [7]ሌላው ዘር ደግሞ
በእሾኽ መካከል ወደቀ፤ እሾኹም አድጎ
የዘሩን ተክል ስላነቀው ፍሬ አላፈራም።
[8]ሌላው ዘር ደግሞ በመልካም መሬት ላይ
ስለ ወደቀ በቅሎ አደገ፤ ፍሬም ሰጠ፤ አንዱ
ሠላሳ፣ አንዱ ሥልሳ፣ ሌላውም መቶ ፍሬ
አፈራ።" [9]ቀጥሎም ኢየሱስ፣ "የሚሰማ ጆሮ
ያለው ይስማ" አለ።
[10]ብቻውን በሆነ ጊዜ፣ ዐሥራ
ሁለቱና አብረውት የነበሩት ሌሎች
ስለ ምሳሌዎቹ ጠየቁት። [11]እርሱም፤
"ለእናንተ የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር
ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ ላሉት ግን ነገር
ሁሉ በምሳሌ ይነገራቸዋል፤ [12]ይኸውም፣
" 'ማየቱን እንዲያዩ እንዳያስተውሉትም፣
መስማቱን እንዲሰሙ ልብ እንዳይሉትም፣
እንዳይመለሱና ኀጢአታቸው
እንዳይሰረይላቸው ነው' " አላቸው።
[13]ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤
"ይህን ምሳሌ አልተረዳችሁትምን? ታዲያ
ሌሎቹን ምሳሌዎች ሁሉ እንዴት ልትረዱ
ትችላላችሁ? [14]ዘሪው ቃሉን ይዘራል።
[15]አንዳንድ ሰዎች በመንገድ ላይ የወደቀውን
ዘር ይመስላሉ፤ ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ
ሰይጣን ወዲያውኑ መጥቶ በውስጣቸው
የተዘራውን ቃል ይወስደዋል። [16]እንዲሁም
ሌሎች በጭንጫ ቦታ ላይ የተዘራውን
ዘር ይመስላሉ፤ ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ
ወዲያው በደስታ ይቀበሉታል፤ [17]ነገር
ግን ሥር የሌላቸው ስለሆኑ የሚቈዩት
ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፤ በቃሉ ምክንያት
መከራ ወይም ስደት በመጣ ጊዜ ወዲያውኑ
ይሰናከላሉ። [18]ሌሎቹ ደግሞ በእሾኽ
መካከል የተዘራውን ዘር ይመስላሉ፤ ቃሉን
መስማት ይሰማሉ፤ [19]ነገር ግን የዚህ ዓለም
ሐሳብ፣ የሀብት አንጓላ (ሉሪነት) እንዲሁም
የሌሎች ነገሮች ምኞት ቃሉን አንቀው
በመያዝ ፍሬ እንዳያፈራ ያደርጉታል።
[20]ሌሎቹ በመልካም መሬት ላይ የተዘራውን
ዘር ይመስላሉ፤ እነዚህም ቃሉን ሰምተው
የሚቀበሉና ሠላሳ፣ ሥልሳ፣ መቶም ፍሬ

4፥1 ማር2፥13፤ 3፥7
4፥2 ቍ 11፤ ማር3፥23
4፥3 ቍ 26
4፥8 ዮሐ15፥5፤ ቈላ1፥6
4፥9 ቍ 23፤ ማቴ11፥15
4፥11 ማቴ3፥2፤ 1ቆሮ5፥12፡13፤ ቈላ4፥5፤ 1ተሰ4፥12፤ 1ጢሞ3፥7
4፥12 ኢሳ6፥9፡10፤ ማቴ13፥13-15
4፥14 ማር16፥9፤ ሉቃ1፥2፤ ሐሥ4፥31፤ 8፥4፤ 16፥6፤ 17፥11፤ ፊል1፥14
4፥15 ማቴ4፥10
4፥19 ማቴ19፥23፤ 1ጢሞ6፥9፡10፡17፤ 1ዮሐ2፥15-17

**4፥2 በምሳሌ፤** ጌታ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ያስተማረው በምሳሌ ነው። ምሳሌ ከዘወትሩ ነባራዊ ሕይወት ላይ ተቀንጭቦ በቀላሉ ግንዛቤ የሚገኝበት ታሪክ ነው፤ ይህም ምሳሌ ልባቸው ለመስማት ዝግጁ ለሆነው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እውነትን ይገልጣል፤ ልባቸው ላልተዘጋጀው ግን ይህንኑ እውነት ይደብቅባቸዋል (ከኢሳ 6፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 13፥3 እና ማብ ይመ)።

**4፥3 አንድ ዘሪ ዘር ሊዘራ ወጣ፤** ኢየሱስ ይህን ምሳሌ በትምህርቱ ያስገባው በዓለም ዙሪያ የወንጌል አቀባበል እንዴት እንደሚሆን ለመንገር ነው። ሦስት እውነቶችን ልብ ማለት ይቻላል፤ (1) መለወጥና ፍሬያማነት እውን ሊሆኑ የሚችሉት፣ አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ቃል በሚሰጠው ምላሽ ልክ ነው (ቍ 14 ይመ፤ ከዮሐ 15፥1-10 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) በዓለም ዙሪያ ለወንጌል የሚሰጠው ምላሽ ልዩ ልዩ ነው፤ ይኸውም ከሚሰሙት አንዳንዶቹ አያስተውሉትም (ቍ 15)፤ በአንድ በኩል ሌሎች ድነትን እስከ ማግኘት ድረስ ያምናሉ፤ ቈይተው ግን ይሰናከላሉ (ቍ 16-19)፤ የተወሰኑት ደግሞ ድነትን እስከሚያገኙ ድረስ ያምናሉ፤ ይጸናሉ፤ በተለያየ መጠንም ፍሬ ያፈራሉ (ቍ 20)። (3) የእግዚአብሔር ቃል ጠላቶችም፣ ሰይጣን፤ ዓለማዊ ጭንቀት፣ ሀብት፤ ተድላና ደስታ ናቸው (ቍ 15፡19)።

**4፥15-17 ቃል ይወስደዋል፤** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ላይ የሚናገረው በጅምር ስለ ቀረው መለወጥ ነው፤ ይኸውም ኀጢአቶች ይቅር መባልን ፈልገው ሳለ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ እውን የሚሆነውን ዳግም ልደት ሳያገኙ ሲቀሩ ነው (በገጽ 1606 ላይ፣ "ዳግም ልደት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ድነትንና አዲስ ልደትን አይቀበሉም፤ ከአማኞችም ጋር ልባዊ ኅብረት የላቸውም፤ ወይም የቤተ ክርስቲያን አባላት ቢሆኑም እንኳ፣ ለክርስቶስ ከልብ የሆነ መሰጠት አይታይባቸውም፤ ቍርጠኛ በሆነ ሁኔታም ከዓለም ተለይተው አይታዩም።

በግማሽ ልብ እውን የሆነ መለወጥ የሚመነጨው ከሚከተሉት የተነሣ ነው፤ (1) ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን በሚገባ ሳታስረዳና ወንጌል የሚጠይቀውን ግዴታ ሳተስተምር፣ በፍሊጋ ላይ የሚገኙትን በቀላሉ በማቀፏ ነው። (2) ቤተ ክርስቲያን በሰይጣን እስራት ውስጥ ለሚገኙት ሰዎች መፍትሔ ሳትፈልግ ስትቀር ነው (16፥15-17፤ ማቴ 10፥1፡8፤ 12፥22-29)። (3) በፍሊጋ ላይ ያሉት ክርስቶስን የሚያምኑት በአእምሯቸው እንጂ ከልባቸው አይደለም፤ ስለዚህ ከውስጣቸው በሆነ እምነትና በሁለንተናቸው ስለማያምኑት ነው (ከሐሥ 2፥37፤ ከ2ቆሮ 4፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። (4) ከልብ የሆነ ንስሓ ሳይገቡ ወይም ከኀጢአት ሳይመለሱ ሲቀሩ ነው (ከማቴ 3፥2፤ ከሐሥ 8፥18-23 ጋር ያነጻጽሩ)። (5) ከልብ የሆነ ፍሊጋ የማያደርጉት ክርስቶስን መቀበል የሚፈልጉት ጌታቸው አድርገው ሳይሆን፣ አዳኛቸው በማድረግ ብቻ ስለ ሆነ ነው (ማቴ 13፥20-21)። (6) እምነታቸው የተመሠረተው ማራኪ በሆነው በሰው አንደበት ላይ እንጂ መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ኀይል በሚያሳዩት ጉዳይ ላይ አይደለም (1ቆሮ 2፥4-5)።

# በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን

*ማር 3፥27 “ … አንድ ሰው አስቀድሞ ኀይለኛውን ሰው ሳያስር ወደ ኀይለኛው ሰው ቤት ሊገባ ንብረቱን ሊዘርፍ አይችልም፤ ቤቱን መዝረፍ የሚቻለው ኀይለኛውን ሰው ሲያስር ብቻ ነው።”*

በማርቆስ ወንጌል ላይ ቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ፣ ኢየሱስ የሰይጣንንና የአጋንንቱን ኀይል ድል ለመንሣት ዐቢይ ጉዳይ አድርጎ የያዘው መሆኑ ነው፤ በ3፥27 ላይ ይህ ሐሳብ፣ “ኀይለኛውን ሰው ሳያስር” (ይኸውም ሰይጣን ተብሎአል) እና “ቤቱን መዝረፍ” (ይኸውም ለሰይጣን ባርነት ያደሩትን ነጻ ማውጣት ማለት ነው) በመባል ተገልጾአል። ሰይጣንን በማሸነፍ የሚገኝ ይህ ኀይል፣ በተለይ አጋንንትን ወይም ክፉ መናፍስትን በማስወጣት (በግሪክ፣ ‘ዳይሞኒየሰን’ ይባላል) እውን ሆኖ ይገኛል።

**አጋንንት፤** (1) ክፉ መንፈስ በሰው ውስጥ በማደሩ፣ የሰይጣን ጭቈናና ተጽዕኖ ባመጣው ጦስም፣ ሰዎች እንደሚሠቃዩ፣ ጌታችን ኢየሱስም አጋንንትን ይቃወምና ያስወጣ እንደ ነበር አዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ ያወሳል፤ ለምሳሌ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ በሰዎች ላይ የአጋንንትን ሥልጣን ለመሻር የተደረገው ሥራ ምን እንደ ሆነ ተገልጾ እናገኛለን፤ 1፥23-28፡32-34፤ 3፥10-12፡14-15፤ 5፥1-20፤ 6፥7፡13፤ 7፥24-30፤ 9፥14-29፤ 16፥17።

(2) አጋንንት ማንነትና የማሰብ ችሎታ ያላቸው መንፈሳውያን ፍጥረታት ናቸው፤ የሰይጣን መንግሥት አባላት፣ የእግዚአብሔርና የሰው ዘር ጠላቶች እንደ መሆናቸው መጠን (ማቴ 12፥43-45)፣ ክፉዎች፣ ተንኰለኞችና በሰይጣን ሥልጣን ሥር የሚገኙ ናቸው (ማቴ 4፥10 እና ማብ ይመ)።

(3) አጋንንት ከጣዖት አምልኮት በስተጀርባ የሚገኙ ኀይላት ናቸው፤ እንግዲህ ሐሰተኛ አማልክትን ማምለክ በመሠረቱ አጋንንትን ማምለክ ማለት ነው (1ቆሮ 10፥20 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 428 ላይ፣ “የጣዖት አምልኮ ባሕርይ” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(4) አዲስ ኪዳን፣ ዓለም ከእግዚአብሔር ርቆ በሰይጣን አገዛዝ ሥር መሆኑን ያሳያል (ዮሐ 12፥31 እና ማብ፤ 2ቆሮ 4፥4፤ ኤፌ 6፥10-12 ይመ፤ በገጽ 2022 ላይ፣ “ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። አጋንንት በዚህ ዘመን ባሉት ገዦች የሥልጣን ተዋረድ ውስጥ ይገኛሉ፤ ክርስቲያኖችም ያለማቋረጥ ከእነርሱ ጋር መዋጋት አለባቸው (ኤፌ 6፥12 እና ማብ ይመ)።

(5) አጋንንት በማያምኑ ሰዎች አካል ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ፤ ብዙ ጊዜም በእነርሱ ላይ ሰፍረው ይገኛሉ (ማር 5፥15፤ ሉቃ 4፥41፤ 8፥27-28፤ ሐሥ 16፥18 ይመ)፤ የሚናገሩትም በእነዚሁ ሰዎች አንደበት ነው። እነዚህኑ ግለሰቦች ባሪያ አድርገው ይገዟቸዋል፤ ወደ ክፋት፣ ወደ ኢግብረገባዊነትና ወደ ጥፋትም ይመሯቸዋል።

(6) ሁሉም ዐይነት ሕመምና በሽታ የክፉ መናፍስት ውጤት ባይሆኑም (ማቴ 4፥24፤ ሉቃ 5፥12-13)፣ አጋንንት በሰው አካል ላይ ሕመምን ሊያመጡ ይችላሉ (ማቴ 9፥32-33፤ 12፥22፤ 17፥14-18፤ ማር 9፥20-22፤ ሉቃ 13፥11፡16)።

(7) መናፍስትን በመጥራትና አስማት በማድረግ (ይኸውም በመተት) ክፉ ሥራ የሚሠሩ ከክፉ መናፍስት ጋር ኅብረት አላቸው፤ ይህም የአጋንንት ቍራኛ ወደ መሆን ያመራል (ከሐሥ 13፥8-10፤ 19፥19፤ ከገላ 5፥20፤ ከራእ 9፥20 ጋር ያነጻጽሩ)።

(8) ክፉ መናፍስት ለመተት መዳረግን፣ ኢግብረገባዊነትን፣ ዐመፅንና ክፋትን በማራመድ በዚህ ዘመን የመጨረሻ ቀናት ይበልጥ ይንቀሳቀሳሉ፤ የእግዚአብሔርን ቃልና መልካም አስተምህሮ፣ በብርቱ ይቃወማሉ፤ (ማቴ 24፥24፤ 2ቆሮ 11፥14-15፤ 1ጢሞ 4፥1 ይመ)። ጋኔናዊ ሥራ በዚህ ምድር ላይ በእጅጉ የሚስፋፋው በሐሰተኛው ክርስቶስና በተከታዮቹ አማካይነት ነው (2ተሰ 2፥9፤ ራእ 13፥2-8፤ 16፥13-14)።

**ኢየሱስ የአጋንንትን ኀይል መስበሩ፤** (1) ኢየሱስ በታምራቱ የሰይጣንንና የአጋንንትን ኀይል ብዙ ጊዜ እንዳልነበረ ያደርጋል (ለምሳሌ 1፥26፡34፡39፤ 3፥10-11፤ 5፥1-20፤ 9፥17-29 ይመ፤ ከሉቃ 13፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ ለምን እንደ ተመላለሰ በግልጽ ከተመለከቱት ዐላማዎች መካከል፣ ሰይጣንን ለማሰርና በሰይጣን የታሰሩትን ነጻ ለማውጣት

የመጣ መሆኑ አንዱ ነው (ማቴ 12፥29፤ ማር 1፥27፤ ሉቃ 4፥18)።

(2) ኢየሱስ ሰይጣንን ማሰሩ በከፊል እውን የሆነው አጋንንትን በማስወጣቱ ሲሆን፣ ፈጽሞ ያሰረውም በሞቱና በትንሣኤው ነው (ዮሐ 12፥31)፤ የጌታ ሞትና ትንሣኤ የሰይጣንን ግዛት መና አስቀርቶ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት መልሶ በስፍራው አስቀምጦአል (በገጽ 1443 ላይ፣ "የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) ገሀነመ እሳት (በግሪክ 'ገሀና') የሥቃይ ቦታ ሲሆን፣ ጌታችን ለዲያብሎስና ለአጋንንት እንዲሆን ብሎ አዘጋጅው (ማቴ 8፥29፤ 25፥41)።

**አማኞችና አጋንንት፤** (1) የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነ እውነተኛ አማኝ የአጋንንት ማደሪያ እንደማይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፤ መንፈስ ቅዱስና አጋንንት በአንድ አካል ውስጥ አብረው ኩሶ ሊኖሩ አይችሉም (2ቆሮ 6፥15-16 እና ማብ ይመ)። ይሁን እንጂ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት መከተል ባቆሙ ክርስቲያኖች፣ ስሜትና ተግባር ላይ አጋንንት ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይችላል (ማቴ 16፥23፤ 2ቆሮ 11፥3፡14)።

(2) ጌታ ኢየሱስ በሰይጣንና በጭፍራዎቹ ላይ ሥልጣን እንደሚኖራቸው ለእውነተኛ አማኞች ተስፋን ሰጣቸው። እኛ ከእነርሱ ጋር በተጋፈጥን ቍጥር በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ርዳታ ብርቱ የሆነ መንፈሳዊ ጦርነት በማካሄድ በእኛና በሌሎች ላይ ለመሠልጠን የሚሞክሩበትን ኀይል መስበር አለብን (ሉቃ 4፥14-19 ይመ)። በዚህ መንገድ ከጨለማ ኀይላት ነጻ መሆን እንችላለን።

(3) በማርቆስ ወንጌል 3፥27 ላይ ባለው ምሳሌ መሠረት፣ ከሰይጣን ጋር የሚደረገው መንፈሳዊ ትግል ሦስት ገጽታዎችን ያካተተ ነው፤ (ሀ) በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት በሰይጣን ላይ ጦርነት ማወጅን (ሉቃ 4፥14-19)፤ (ለ) ሰይጣንን ቤት ሰብሮ መግባት (መሸጎ ወደሚገኝበት ማንኛውም ስፍራ ሁሉ መግባት ማለት ነው)፣ በጸሎትና ቃሉን በማወጅ እርሱን መምታት እንዲሁም በእርሱ ላይ ድል መቀዳጀትና ርኩስ ማታለሉንና ፈተናውን ማምከንን (ከሉቃ 11፥20-22 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (ሐ) ይዞታውን መውረስ፣ ይኸውም በሰይጣን ኀይል የተያዙት ትድግናን እንዲያገኙ በማድረግ፣ ትድግናን ያገኙት እነዚሁም በክርስቶስ አምነው ምሕረትንና ቅድስናን ያገኙ ዘንድ ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት (ሉቃ 11፥22፤ ሐሥ 26፥18)።

(4) በዚህ ሂደት ውስጥ አንድ ባንድ መውሰድ ያለብን የየቅል እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው፤ (ሀ) የምንዋጋው ከሥጋና ከደም ሳይሆን ከመንፈሳዊ ኀይላትና ከክፉ ሥልጣናት ጋር መሆኑን ልብ ማድረግ (ኤፌ 6፥12)። (ለ) በሙሉ ልብና ኀይል ለእውነቱና ለጽድቁ በመሰጠት (ሮሜ 12፥1-2፤ ኤፌ 6፥14)፤ በእግዚአብሔር ፊት መኖር። (ሐ) በየትኛውም ስፍራ የሰይጣን ኀይሉ ሊሰበር እንደሚችል እምነት ማሳደር (ሐሥ 26፥18፤ ኤፌ 6፥16፤ 1ተሰ 5፥8)፤ የሰይጣንን ምሽግ መደምሰስ የሚችል ከእግዚአብሔር የተሰጠ መንፈሳዊ መሣሪያ አማኙ እንዳለውም መገንዘብ (2ቆሮ 10፥4-5)። (መ) በመንፈስ ቅዱስ ሙላት የመንግሥቱን የምሥራች ማወጅ (ማቴ 4፥23፤ ሉቃ 1፥15-17፤ ሐሥ 1፥8፤ 2፥4፤ 8፥12፤ ሮሜ 1፥16፤ ኤፌ 6፥15)። (ሠ) በኢየሱስ ስም በማመን (ሐሥ 16፥16-18)፣ የእግዚአብሔርን ቃል መሣሪያ በማድረግ (ኤፌ 6፥17)፣ በመንፈስ በመጸለይ (ሐሥ 6፥4፤ ኤፌ 6፥18)፣ በመጾም (ማቴ 6፥16 እና ማብ ይመ)፣ አጋንንትን በማስወጣት ሰይጣንንና ኀይሉን በቀጥታ መቋቋም (ማቴ 10፥1 እና ማብ ይመ፤ 12፥28፤ 17፥17-21፤ ማር 16፥17፤ ሉቃ 10፥17፤ ሐሥ 5፥16፤ 8፥7፤ 16፥18፤ 19፥12 ይመ፤ በገጽ 1527 ላይ፣ "አማኞች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (ሠ) መንፈስ ቅዱስ የጠፉትን በተለይ ስለ ኀጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለሚመጣው ፍርድ ይወቅሳቸው ዘንድ በመጸለይ (ዮሐ 16፥7-11)። (ረ) በመፈወስ፣ በልሳን፣ በታምራት፣ በምልክቶችና በድንቆች መንፈስ ቅዱስ እንዲገለጽ መጸለይ፤ በታላቅ ጕጕትም መሻት (ሐሥ 4፥29-33፤ 10፥38፤ 1ቆሮ 12፥7-11)።

የሚያፈሩ ናቸው።"

## የመቅረዙ መብራት ምሳሌ

21እንዲህም አላቸው፤ "መብራት
አምጥታችሁ ከዕንቅብ ወይም ከዐልጋ
ሥር ታስቀምጣላችሁን? የምታስቀምጡት
በመቅረዙ ላይ አይደለምን? 22ስለዚህ ተደብቆ
የማይገለጥ፣ ተሸሽጎ ወደ ብርሃን የማይወጣ
የለም፤ 23ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።"
24በመቀጠልም፣ "ስለምትሰሙት
ነገር ጥንቃቄ አድርጉ፤ በምትሰፍሩበት
መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል፤ እንዲያውም
ከዚያ የበለጠ ይጨመርላችኋል። 25ላለው
ይጨመርለታል፤ ከሌለው ላይ ግን፣ ያው
ያለው እንኳ ይወሰድበታል" አላቸው።

## የአዳጊው ዘር ምሳሌ

26ከዚያም፣ እንዲህ አለ፤ "የእግዚአብሔር
መንግሥት ይህን ትመስላለች፤ አንድ ሰው
መሬት ላይ ዘር ይዘራል። 27ሰውየው ሌሊት
ይተኛል፤ ቀን ይነሣል፤ ነገር ግን እርሱ
ሳያውቅ ያ ዘር በቅሎ ያድጋል፤ 28ምድርም
ራስዋ በመጀመሪያ ቡቃያውን፣ ቀጥሎ
ዛላውን፣ ከዚያም በዛላው ላይ የጐመራ ፍሬ
ታስገኛለች፤ 29ፍሬው እንደ በሰለም መከር
በመድረሱ፣ ሰውየው ወዲያው ማጭዱን
አንሥቶ አጨዳ ይጀምራል።"

## የሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ

*4፥30-32፤ ተጓ ምብ — ማቴ 13፥31፡32፤*
*ሉቃ 13፥18፡19*

30ደግሞም እንዲህ አለ፤ "የእግዚአብሔርን
መንግሥት ከምን ጋር እናነጻጽራታለን?
በምንስ ምሳሌ እንገልጻታለን? 31በምድር
ላይ ከሚዘራው ዘር ሁሉ እጅግ ያነሰችውን
የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤ 32ተዘርታ
ካደገች በኋላ ግን፣ በአትክልቱ ቦታ
ከሚገኙት ዕፀዋት ሁሉ ትበልጣለች፤
የሰማይ ወፎችም በትላልቅ ቅርንጫፎቿ
ጥላ ሥር ያርፋሉ።"
33ኢየሱስም ሰዎች መረዳት በሚችሉበት
መጠን፣ እነዚህን በመሳሰሉ ብዙ ምሳሌዎች
ነገራቸው። 34ምንም ነገር ያለ ምሳሌ
አይነግራቸውም ነበር። እርሱና ደቀ
መዛሙርቱ ብቻ በሚሆኑበት ጊዜ ግን
ሁሉንም ነገር በዝርዝር ያስረዳቸው ነበር።

4፥21 ማቴ5፥15
4፥22 ኤር16፥17፤
ማቴ10፥26፤
ሉቃ8፥17፤ 12፥2
4፥23 ቍ9፤
ማቴ11፥15
4፥24 ማቴ7፥2
4፥25 ማቴ25፥29
4፥26 ማቴ13፥24
4፥29 ራእ14፥15
4፥30 ማቴ13፥24
4፥33 ዮሐ16፥12
4፥34 ዮሐ16፥12
4፥36 ቍ1፤
ማር3፥9፤
5፥2፡21፤
6፥32፡45
4፥40
ማቴ14፥31፤
ማር16፥14
5፥2 ማር1፥23፤
4፥1

## ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ

*4፥35-41 ተጓ ምብ — ማቴ 8፥18፡23-27፤*
*ሉቃ 8፥22-25*

35ያ ቀን በመሸ ጊዜ፣ "ወደ ማዶ እንሻገር"
አላቸው። 36እነርሱ ሕዝቡን ትተው
በጀልባዋ ውስጥ እንዳለ በዚያው ይዘውት
ሄዱ፤ ሌሎች ጀልባዎችም አብረውት ነበሩ።
37በዚህ ጊዜ ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ ተነሣ፤
ማዕበሉም ውሃ እስኪሞላት ድረስ ጀልባዋን
ያናውጣት ነበር። 38ኢየሱስ ግን ትራስ
ተንተርሶ ከጀልባዋ በስተ ኋላ በኩል ተኝቶ
ነበር። እነርሱም ቀስቅሰውት፣ "መምህር
ሆይ፤ ስናልቅ አይገድህምን?" አሉት።
39እርሱም ተነሥቶ ነፋሱን ገሠጸው፤
ባሕሩንም፣ "ጸጥ፣ ረጭ በል!" አለው። ነፋሱም
ጸጥ፣ ረጭ አለ፤ ፍጹምም ጸጥታ ሆነ።
40ደቀ መዛሙርቱንም፣ "ስለ ምን እንዲህ
ፈራችሁ? እስከ ዛሬ እምነት የላችሁምን?" ማር 9፡23
አላቸው። 24
41እነርሱም በፍርሀት ተውጠው እርስ
በርሳቸው፣ "ነፋሱም ሞገዱም የሚታዘዙለት
ይህ ማን ነው?" ተባባሉ።

## አጋንንት ያደረበት ሰው መፈወሱ

*5፥1-17 ተጓ ምብ — ማቴ 8፥28-34፤*
*ሉቃ 8፥26-37*
*5፥18-20 ተጓ ምብ — ሉቃ 8፥38፡39*

5 ባሕሩን ተሻግረው ጌርሴኖንᵃ ወደ
ተባለ አገር መጡ። 2ኢየሱስ ከጀልባ
እንደ ወረደ፣ ርኩስᵇ መንፈስ ያደረበት
ሰው ከመቃብር ቦታ ወጥቶ ሊገናኘው
ወደ እርሱ መጣ። 3ይህ ሰው በመቃብር
ቦታ ውስጥ የሚኖርና ማንም በሰንሰለት
እንኳ ሊያስረው የማይችል ነበር። 4ብዙ
ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር
ነበር፤ ነገር ግን የእጅ ሰንሰለቱን ይበጥስ፣
የእግር ብረቱንም ይሰብር ነበር። ማንም ይዞ
ሊያቈየው የሚችል አልነበረም።
5በመቃብሮቹና በተራራዎቹ መካከል
ቀንና ሌሊት እየተዘዋወረ በመጮኽ
ሰውነቱን በድንጋይ ይቈራርጥ ነበር።

*ᵃ5፥1 አንዳንድ ቅጆች ጌራሴኖን፣ ሌሎች ደግሞ ጌ
ርጌሴኖን ይላሉ።*
*ᵇ5፥2 ወይም ክፉ፤ እንዲሁም ቍ 8እና 13 ይመ።*

**4፥25 ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል፤** ኢየሱስ ከዚህ ላይ የገለጸው የመንግሥቱን መርሕ ነው፤ አማኞች እውነትንና ጸጋን በማግኘት ሂደት መቀጠል አለባቸው፤ አለበለዚያ የያዙትን እንኳ ያጣሉ። በጸጋ ማደግ ወይም በመንፈሳዊ ሕይወት እያሽቆለቆለ መሄድ በብዙዎች ሕይወት ዘንድ ጐልቶ ሆኖ ላይታይ ይችላል። ይሁን እንጂ አንድ ክርስቲያን እያደገ መሄዱ ወይም እየዘቀጠ መሄዱ ሀቅ ነው (2ጴጥ 3፥17-18)። ከሕደት ውስጥ የመግባት አደጋ የሚከሠተው አንድ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ እየዘቀጠ በተጓዘበት መጠን ነው (ዕብ 3፥12-15፤ 4፥11፤ 6፥11-12፤ 10፥23-39፤ 12፥15 ይመ፤ በገጽ 1962 ላይ፣ «*ክሕደት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**4፥31 የሰናፍጭ ቅንጣት፤** ሉቃ 13፥19 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**5፥2 ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው፤** አጋንንት የያዛቸው ሰዎች፣ ክፉ መንፈስ በእነርሱ ውስጥ ከማደሩ የተነሣ (ሉቃ 13፥11 እና ማብ ይመ)፣ በሰይጣን ጭቈና (ሐሥ 10፥38) ወይም ተጽዕኖ (ማቴ 12፥45፤ ሐሥ 16፥16-18) ይሠቃያሉ። ጌታ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ አጋንንትን ስለ ማስወጣቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፎ ይገኛል (ስለ አጋንንትና አንድ ክርስቲያንም በእነርሱ ላይ ስላለው ኀይል በሰፊው ተብራርቶ የሚገኘውን ለማስተዋል፣ በገጽ 1499 ላይ፣ «*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

[12]እነርሱም ከዚያ ወጥተው፣ ሰዎች
ማር 7፥32-37 ንስሓ እንዲገቡ ሰበኩ፤ [13]ብዙ አጋንንት
አስወጡ፤ ብዙ ሕመምተኞችንም ዘይት
እየቀቡ ፈወሱ።

### የመጥምቁ ዮሐንስ መሰየፍ

*6፥14-29 ተጓ ምብ — ማቴ 14፥1-12*
*6፥14-16 ተጓ ምብ — ሉቃ 9፥7-9*

[14]የኢየሱስ ስም እየታወቀ በመምጣቱ፣ ንጉሥ ሄሮድስ ይህንኑ ሰማ። አንዳንዶችም፣ "የዚህ ዐይነት ታምር በእርሱ የሚሠራው መጥምቁ ዮሐንስ ከሙታን ቢነሣ ነው" ይሉ ነበር[*]። [15]ሌሎቹም፣ "ኤልያስ ነው" አሉ።

አንዳንዶች ደግሞ፣ "ከቀደምት ነቢያት እንደ አንዱ ነቢይ ነው" ይሉ ነበር።

[16]ሄሮድስ ነገሩን ሲሰማ ግን፣ "እኔ ራሱን ያስቈረጥሁት ዮሐንስ ከሙታን ተነሥቶ አለ!" አለ።

[17]ሄሮድስ ራሱ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮድያዳን በማግባቱ ምክንያት፣ ተይዞ እንዲታሰር ትእዛዝ በመስጠት ዮሐንን ስን ወህኒ ቤት አስገብቶት ነበር [18]ዮሐንስ ሄሮድስን፣ "የወንድምህን ሚስት ታገባት ዘንድ ሕግ ይከለክልሃል" ይለው ነበርና። [19]ሄሮድያዳም በዚህ ቂም ይዛበት ልታስገድለው ፈለገች፤ ነገር ግን አልሆንላትም። [20]ምክንያቱም ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው መሆኑን ሄሮድስ በማወቁ ይፈራውና ይጠብቀው ነበር። ዮሐንስ የሚናገረውን ሲሰማ ሄሮድስ ቢታወክም[†] በደስታ ያደምጠው ነበር።

[21]በመጨረሻም አመቺ ቀን መጣ። ሄሮድስ በተወለደበት ዕለት ለከፍተኛ ሹማምቱ፣ ለጦር አዛዦቹና በገሊላ ለታወቁ ታላላቅ ሰዎች ግብዣ አደረገ። [22]የሄሮድያዳም ልጅ ገብታ በዘፈነች ጊዜ ሄሮድስንና ተጋባዦቹን ደስ አሰኘቻቸው። ንጉሡም ብላቴናዪቱን፣ "የምትፈልጊውን ሁሉ ጠይቂኝ እሰጥሻለሁ" አላት። [23]ደግሞም "እስከ መንግሥቱ እኩሌታ ድረስ እንኳ ቢሆን፣ የምትጠይቂኝን ሁሉ እሰጥሻለሁ" ሲል በመሐላ ቃል ገባላት።

[24]እርሷም ወጥታ እናቷን፣ "ምን ልለምን ነው?" አለቻት።

እናቷም፣ "የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ" አለቻት።

[25]ብላቴናዪቱም ወዲያው ፈጥና ወደ ንጉሡ በመመለስ፣ "የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ አሁን በሳሕን እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ" አለችው።

[26]ንጉሡ በነገሩ እጅግ አዘነ፤ በተጋበዙት እንግዶች ፊት የመሐላ ቃሉን ለማጠፍ አልፈለገም። [27]ስለዚህ አንዱን ወታደር በፍጥነት ልኮ፣ የዮሐንስን ራስ ቈርጦ እንዲያመጣ አዘዘው፤ እርሱም ሄዶ በወህኒ ቤቱ ውስጥ ራሱን ቈረጠ፤ [28]በሳሕን አምጥቶ ለብላቴናዪቱ ሰጣት፤ ብላቴናዪቱም ለእናትዋ ሰጠች። [29]የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም ይህን እንደ ሰሙ መጡ፤ ሬሳውንም ወስደው ቀበሩት፤

### ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎች መገበ

*6፥32-44 ተጓ ምብ — ማቴ 14፥13-21፤ ሉቃ 9፥10-17፤ ዮሐ 6፥5-13*
*6፥32-44 ተጓ ምብ — ማር 8፥2-9*

[30]ሐዋርያትም በኢየሱስ ዙሪያ ተሰብስበው የሠሩትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት። [31]ብዙ ሰዎች ይመጡና ይሄዱ ስለ ነበር ምግብ እንኳ ለመብላት ጊዜ ስላልነበራቸው፣ "እስቲ ብቻችሁን ከእኔ ጋር ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራ እንሂድና ጥቂት ዕረፉ" አላቸው።

[32]ስለዚህ ብቻቸውን ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራ በጀልባ ሄዱ። [33]እነርሱም ሲሄዱ ብዙ ሰዎች አይተው ዐወቋቸው፤ ከከተሞችም ሁሉ በእግር እየሮጡ ቀድመዋቸው ደረሱ። [34]ኢየሱስ ከጀልባዋ በሚወርድበት ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ አየ፤ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ስለነበሩም አዘነላቸው፤ ብዙ ነገርም ያስተምራቸው ጀመር።

[35]በዚህ ጊዜ ቀኑ እየመሸ በመሄዱ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው እንዲህ አሉት፤ "ይህ ቦታ ምድረ በዳ ነው፤ ቀኑም መሽቶአል፤ [36]በአካባቢው ስላሉ ወዳለበት መንደር ሄደው የሚበላ ነገር ገዝተው እንዲመገቡ ሕዝቡን አሰናብታቸው።"

[37]እርሱ ግን መልሶ፣ "የሚበሉትን እናንተው ስጡአቸው" አላቸው።

እነርሱም፣ "ሄደን በሁለት መቶ ዲናር እንጀራ ገዝተን የሚበሉትን እንስጣቸውን?" አሉት።

[*]6፥14 አንዳንድ ቅጆች ይል ነበር ይላሉ
[†]6፥20 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ብዙ ነገር ያደርግ ነበር ይላሉ

6፥12 ሉቃ9፥6
6፥13 ያዕ5፥14
6፥14 ማቴ3፥1፤
6፥15 ሚል4፥5፤ ማቴ16፥14፤ 21፥11፤ ማር8፥28
6፥17 ማቴ4፥12፤ 11፥2፤ ሉቃ3፥19:20
6፥18 ዘሌ18፥16፤ 20፥21
6፥20 ማቴ11፥9
6፥21 አስ1፥3፤ 2፥18፤ ሉቃ3፥1
6፥23 አስ5፥3:6፤ 7፥2
6፥30 ማቴ10፥2፤ ሉቃ9፥10፤ 17፥5፤ 22፥14፤ 24፥10፤ ሐሥ1፥2:26
6፥31 ማር3፥20
6፥32 ቍ45፤ ማር4፥36
6፥34 ማቴ9፥36
6፥37 2ነገ4፥42-44

**6፥13 ዘይት እየቀቡ፤** ዘይት እየቀቡ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ፈውስን እውን ማድረግ ተጠቅሶ የሚገኘው በዚህና በያዕቆብ 5፥14 ላይ ነው። ዘይት፣ የመንፈስ ቅዱስን ህልዎትና ኀይል ለማመልከት የቀረበ ትእምርት ከመሆኑም በላይ (ዘካ 4፥3-6 እና ማብ ይመ)፣ እምነትን ለማበረታታት ሲባል የቀረበ የግንኙነት መሥመር ሊሆን ይችላል።

**6፥17 ዮሐንስን ወህኒ ቤት አስገብቶት፤** ማቴ 11፥7 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**6፥22 በዘፈነች ጊዜ፤** ማቴ 14፥6 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**6፥34 አዘነላቸው፤** አዘኔታ ሰዎችን ከውስጣቸው የሚፈንቅል ስሜት ነው፤ በችግር ላይ ለሚገኝ ሰው ርኅራኄን ከማለገስ ጋር የሚያያዝ ሲሆን፣ ሌላ ሰው ስለ ደረሰበት ሥቃይና መከራ መቸገርንም ይመለከታል። ይህም የእግዚአብሔርና (ዘዳ 30፥3፤ 2ነገ 13፥23፤ መዝ 78፥38፤ 111፥4) የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርይ ነው (1፥41፤ 8፥2 እና ማብ፤ ማቴ 9፥36፤ 14፥14፤ 15፥32፤ ሉቃ 7፥13)። በየትኛውም ዘመን በተለይ ደግሞ ሌሎች የአካልና የመንፈስ ሥቃይ ሲደርስባቸው ደንታ ቢስ በተሆነበት በአሁኑ ዘመን፣ ኢየሱስ ይህ የርኅራኄ ስሜት የተከታዮቹ ዐይነተኛ መለዮ እንዲሆን ይጠብቅባቸዋል፤ ይፈልጋልም (ማቴ 18፥33፤ ሉቃ 10፥33)።

38እርሱም፣ "ስንት እንጀራ አላችሁ?
እስቲ ሄዳችሁ እዩ" አላቸው።
አይተውም፣ "አምስት እንጀራና ሁለት
ዓሣ" አሉት።
39ከዚያም፣ ሕዝቡን በለመለመ ሣር
ላይ በቡድን በቡድን እንዲያስቀምጡ
አዘዛቸው። 40ሕዝቡም መቶ መቶና አምሳ
አምሳ ሆነው በቡድን በቡድን ተቀመጡ።
41እርሱም አምስቱን እንጀራና ሁለቱን
ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ በማየት ባረከ፤
እንጀራውንም ቈርሶ እንዲያቀርቡላቸው
ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፤ ሁለቱንም ዓሣ
ለሁሉም አካፈለ። 42ሁሉም በልተው ጠገቡ፤
43ደቀ መዛሙርቱም ከተበላው እንጀራና
ዓሣ፣ ዐሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ ፍርፋሪ
አነሡ። 44እንጀራውንም የበሉት አምስት
ሺህ ወንዶች ነበሩ።

## ኢየሱስ በባሕር ላይ በእግሩ ሄደ

*6፥45-51 ተጓ ምብ — ማቴ 14፥22-32፤*
*ዮሐ 6፥15-21*
*6፥53-56 ተጓ ምብ — ማቴ 14፥34-36*

45ወዲያውም እርሱ ሕዝቡን እያሰናበተ
ሳለ፣ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ወደ ቤተ
ሳይዳ ቀድመውት እንዲሻገሩ አዘዛቸው፤
46ከዚ ያምትቶአቸው ሊጸልይ ወደ ተራራ
ወጣ።
47በመሸም ጊዜ ጀልባዋ ባሕሩ መካከል
ነበረች፤ እርሱም ብቻውን በምድር ላይ
ነበር። 48ነፋስ በርትቶባቸው ስለ ነበር፣ ደቀ
መዛሙርቱ ከመቅዘፊያው ጋር ሲታገሉ
አያቸው፤ በአራተኛውም ክፍለ ሌሊት
ገደማ፣ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ
መጣ፤ በአጠገባቸውም ዐልፎ ሊሄድ ነበር።
49ነገር ግን በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ
ምትሐት መስሎአቸው ጮኹ፤ 50ሁሉም
እርሱን ባዩት ጊዜ ደንግጠው ነበርና።
እርሱም ወዲያውኑ አነጋገራቸውና፣
"አይዞአችሁ እኔ ነኝ፤ አትፍሩ!" አላቸው።

6፥38
ማቴ15፥34፤
ማር8፥5
6፥41 ማቴ14፥19
6፥45 ቍ32፤
ማቴ11፥21
6፥46 ሉቃ3፥21
6፥49 ሉቃ24፥37
6፥50 ማቴ14፥27
6፥51 ቍ32፤
ማር4፥39
6፥52 ማር8፥17-21
6፥53
ዮሐ6፥24-25
6፥56 ማቴ9፥20
7፥2
ሐሥ10፥14፡28፤
11፥8፤
ሮሜ14፥14
7፥3 ቍ5፡8፡9፡13፤
ሉቃ11፥38
7፥4 ማቴ23፥25፤
ሉቃ11፥39
7፥5 ቍ3፤
ገላ1፥14፤ ቈላ2፥8

51እርሱም በጀልባዋ ላይ ወጥቶ አብሮአቸው
ሆነ፤ ነፋሱም ተወ፤ እነርሱም እጅግ ተደነቁ፤
52የእንጀራውን ታምር አላስተዋሉም ነበርና፤
ልባቸውም ደንድኖ ነበር።
53በተሻገሩም ጊዜ፣ ጌንሴሬጥ ደርሰው
ወረዱ፤ ጀልባዋንም እዚያው አቆሙ።
54ወዲያው እንደ ወረዱም፣ ሕዝቡ ኢየሱስን
ዐወቁት፤ 55ወደ አካባቢውም ሁሉ በመሮጥ
ሕመምተኞችን በዐልጋ ላይ እየተሸከሙ
እርሱ ወደሚገኝበት ስፍራ ሁሉ ያመጡ
ነበር። 56በየደረሰበት መንደር ወይም ከተማ
ወይም ገጠር ሁሉ ሕመምተኞችን በየአደ
ባባዩ እያስቀመጡ የልብሱን ጫፍ እንኳ
ለመንካት ይለምኑት ነበር፤ የነኩትም ሁሉ
ይድኑ ነበር።

## ኢየሱስ የአይሁድን ውጫዊ ሥርዐት ተቃወመ

*7፥1-23 ተጓ ምብ — ማቴ 15፥1-20*

7 ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያንና ከኢየሩሳሌም
የመጡ አንዳንድ ጸሐፍት በኢየሱስ ዙሪያ
ተሰበሰቡ፤ 2ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ
ባልነጻ ማለት ባልታጠበ እጅ እንጀራ
ሲበሉ አዩ፤ 3ፈሪሳውያንና አይሁድ ሁሉ
የአባቶችን ወግ ለመጠበቅ ሲሉ፣ በሥርዐቱ
መሠረት እጃቸውን በጥንቃቄ ሳይታጠቡ
አይበሉም ነበርና። 4ከገበያ ሲመለሱም
ታጥበው ራሳቸውን ካላነጹ በስተቀር
አይበሉም ነበር። እንዲሁም ዋንጫን፣
ማሰሮን፣ ሳሕንና ዐልጋን[a] እንደ ማጠብ
ያሉትን ሌሎችን ወጎች ይጠብቁ ነበር።
5ፈሪሳውያንና ጸሐፍትም፣ "ደቀ
መዛሙርትህ እንደ አባቶች ወግ በመኖር
ፈንታ ባልታጠበ እጃቸው ለምን እንጀራ
ይበላሉ?" ብለው ጠየቁት።
6እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ኢሳይያስ
ስለ እናንተ፣ ስለ ግብዞች በትክክል

*[a]7፥4 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የማእድ ዐልጋ ይላሉ*


**6፥41 አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ፤** ማቴ 14፥19 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**6፥41 በምግብ ሰዓት ምስጋና ማቅረብ፤** ይህ ሐረግ በዋናው ጽሑፍ ላይ ባይገኝም፣ አጠቃላይ ሐሳቡ እንደሚከተለው ነው፤ ምግብ ከመበላቱ በፊት ክርስቶስ ስለ ምግቡ ለሰማይ አባቱ ምስጋና አቀረበ። አማኞችም ምግብ በቀረበላቸው ቍጥር ምስጋና በማቅረብ የጌታን አርአያነት መከተል አለባቸው። ምስጋና በማቅረብ መመገብ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን እንክብካቤና ችሮታ በጥሞና ማስተዋል ማለት ነው። እያንዳንዱ ምግብ ለእግዚአብሔር ክብር ሲባል የተከናወነ አምልኮ ሆኖ መቈጠር አለበት። ምግብ ከመቅረቡ በፊት ምስጋናን ስለ ማቅረብ፣ 1ሳሙ 9፥13፤ ማቴ 14፥19፤ 15፥36፤ 26፥26፤ ሮሜ 14፥6፤ 1ቆሮ 10፥31፤ 1ጢሞ 4፥4-5 ይመልከቱ።

**7፥6 ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤** ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ሕግን አክርሮ የማየት ኀጢአት በደለኞች ነበሩ። ሕግ አክራሪ የሆነ ሰው ከእግዚአብሔርና ከመንፈስ መወለድ የሚገኘውን መልካም የውስጥ ሁኔታ፣ ውጫዊ በሆነ ተግባር ወይም አፍአዊ ቃል የሚተካ ነው (ማቴ 5፥20 እና ማብ፤ 5፥27-28፤ 6፥1-7፤ ዮሐ 1፥13፤ 3፥3-6 ይመ፤ ኢሳ 1፥11 እና ማብ፤ አሞ 4፥4-5 እና ማብ ይመ)። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ልባቸው ከእግዚአብሔር ርቆ ሳለ እግዚአብሔርን የሚያከብሩት በከንፈራቸው ነው፤ በውጫዊ ሕይወታቸው ጻድቃን ይመስላሉ፤ በውስጣቸው ግን እውነተኛ የሆነ ፍቅር ለእግዚአብሔር የላቸውም። (1) ሕግ አክራሪነት ሲባል የሕግ ወይም የብቃት መለኪያ በክርስቲያን ማኅበረሰብ ዘንድ እንዲሁ መኖሩን የሚያመለክት አይደለም። ይልቁንስ ከአነሣሽ ምክንያት ጋር ግንኙነት አለው፤ ይህ አነሣሽ ምክንያትም በቃሉ በተገለጸው መሠረት እንደ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚቀርብበት መንገድ ነው። በክርስቶስ በኩል የሚገኝ ሕያው እምነት ላይ ያልተመሠረተ ሕግ ወይም ሥርዐት አክራሪነት፣ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውንም ጸጋም ልደት ግምት ውስጥ ያላስገባ አነሣሽ ምክንያት፣ እግዚአብሔርን ለመታዘዝና ደስ ለማሰኘት ቅን የሆነ ፍላጎት የሌለው አነሣሽነትም ሕግ አክራሪነት ነው (ማቴ 6፥1-7፤ ዮሐ 14፥21)።

(2) በዚህ በጸጋ ዘመን እንኳ፣ ክርስቲያኖች

# አስሩ ከተማና ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ አገሮች




© 1989 The Zondervan Corporation

ተንብዮአል፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤
'ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ
ግን ከእኔ የራቀ ነው፤
7በከንቱ ያመልከኛል፤ ትምህርታቸውም
ሰው ሠራሽ ሥርዐት ብቻ ነው።'
8የእግዚአብሔርን ትእዛዛዝ ትታችሁ
የሰዎችን ወግና ሥርዐት ታጠብቃላችሁ።"
9ደግሞም፣ እንዲህ አላቸው፤ "የራሳችሁን
ወግ ለመጠበቅ[ሀ] ስትሉ፣ የእግዚአብሔርን
ትእዛዝ የምትተውበት ዘዴ አላችሁ።
10ሙሴ፣ 'አባትህንና እናትህን አክብር፤
አባቱን ወይም እናቱን የሚሳደብ ፈጽሞ
ይሙት ብሎ ነበርና፤ 11እናንተ ግን አንድ
ሰው አባቱን ወይም እናቱን፣ 'ከእኔ ማግኘት
የሚገባች ሁን ርዳታ ሁሉ ቍርባን ይኸውም
መባ አድርጌአለሁ ቢላቸው፣ 12እናንተም
ይህ ሰው ለአባቱም ሆነ ለእናቱ ከዚህ በኋላ
ምንም ነገር እንዲያደርግ አትፈቅዱለትም።
13ስለ ዚህ ለትውልድ በምታስተላልፉት
ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፤ ይህን
የመሰለም ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ"።
14ደግሞም ኢየሱስ ሕዝቡን ወደ
እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ "ስሙኝ፤
ሁላችሁም አስተውሉ፤ 15ከውጭ ወደ ውስጥ
ገብቶ ሰውን የሚያረክሰው አንዳች ነገር
የለም፤ ይልቁን ሰውን የሚያረክሰው ከራሱ
ወደ ውጭ የሚወጣው ነገር ነው፤ 16ሰሚ
ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ[ለ]።"
17ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ከገባ በኋላ
ደቀ መዛሙርቱ ስለ ምሳሌው ጠየቁት።
18እርሱም፣ "እናንተም ነገሩ አይገባችሁምን?
ከውጭ ወደ ሰው ገብቶ ሊያረክሰው የሚችል
አንዳች ነገር የለም፤ 19ወደ ልቡ ሳይሆን
ወደ ሆዱ ይገባል፤ ከዚያም ከሰውነቱ
ይወጣልና።" ኢየሱስ ይህን በማለቱ ምግብ
ሁሉ ንጹሕ መሆኑን ገለጠ።
20ቀጥሎም፣ እንዲህ አለ፤ "ከሰው የሚወጣ
ያ ሰውን ያረክሰዋል፤ 21ከውስጥ፣ ከሰው ልብ
የሚወጡት ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝር፤ ስርቆት፤
ሰው መግደል፣ ዝሙት፣ 22መስገብገብ፣
ክፋት፣ ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣
ስም ማጥፋት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው።
23እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሰው ይወጣሉ
ሰውንም ያረክሱታል።"

## ሲሮፊኒቃዊቷ ሴት

*7፥24-30 ተጓ ምብ — ማቴ 15፥21-28*

24ከዚያ ተነሥቶ ወደ ጢሮስ[ሐ] አገር
ሄደ፤ ወደ አንድ ቤት ገብቶ እዚያ መኖሩን
ማንም እንዳያውቅበት ፈለገ፤ ሆኖም እዚያ
መኖሩ ሊሸሸግ አልቻለም። 25ወዲያው
ግን ትንሺቱ ልጇ በርኩስኽ መንፈስ
የተያዘችባት አንዲት ሴት ስለ እርሱ ሰምታ
መጣችና በእግሩ ላይ ወደቀች። 26ሴትየዋም
ግሪካዊት፣ በትውልዷም ሲሮፊኒቃዊት
ነበረች። እርሷም ኢየሱስ ጋኔኑን ከልጇ
እንዲያስወጣላት ለመነችው።
27እርሱ ግን፣ "የልጆችን እንጀራ ወስዶ
ለውሾች መጣል ተገቢ ስላልሆነ፣ መጀመሪያ
ልጆቹ ጠግበው ይብሉ" አላት።

7፥7 ኢሳ29፥13
7፥8 ቍ3
7፥9 ቍ3
7፥10 ዘፀ20፥12፤ 21፥17፤ ዘሌ20፥9፣ ዘዳ5፥16
7፥11 ማቴ23፥16፡18
7፥13 ቍ3፤ ዕብ4፥12
7፥17 ማር9፥28
7፥19 ሐሥ10፥15፤ ሮሜ14፥1-2፤ ቈላ2፥16፤ 1ጢሞ4፥3-5
7፥22 ማቴ20፥15
7፥24 ማቴ11፥21
7፥25 ማቴ4፥24

[ሀ]7፥9 አንዳንድ ቅጆች ለማቆም ይላሉ
[ለ]7፥15 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሰሚ ጆሮ ያለው ቢኖር፣ ይስማ የሚለው የላቸውም።
[ሐ]7፥24 አያሌ የጥንት ቅጆች ጢሮስና ሲዶና የሚለው አላቸው
[መ]7፥25 ወይም ክፉ

የክርስቶስን ሕግና የእርሱን ቃል፣ ትምህርት፣ ሥርዐትና ግዴታ ማክበር አለባቸው። አዲስ ኪዳን፣ "ነጻ" ስለሚያወጣው፣ "ፍጹም ሕግ" (ያዕ 1፥25)፣ "ክቡር ሕግ" (ያዕ 2፥8)፣ "የክርስቶስ ሕግ" (ገላ 6፥2)፣ እና "የ ... መንፈስ ሕግ" (ሮሜ 8፥2) ይናገራል። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የሚከተሉትን እናገኛለን፦ (ሀ) አዎንታዊ ትእዛዞችን (1ተሰ 5፥16-18)፣ (ለ) አሉታዊ ትእዛዞችን (ሮሜ 12፥2)፣ (ሐ) መሠረታዊ መርሖችን (1ቆሮ 8፥13) እንዲሁም በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ የማስተዳደር ኀላፊነት እንዲኖራቸው ሥልጣን ከተሰጣቸው መሪዎች ዘንድ ቃልን እናገኛለን (ኤፌ 4፥11-12፤ 1ጢሞ 3፥5፤ ዕብ 13፥7፡17)።

**7፥8 የሰዎችን ወግና ሥርዐት፤** ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን የሰውን ወግና ሥርዐት ከመለኮታዊ መገለጥ በላይ በማስቀመጣቸው በደለኞች ነበሩ። ከዚህ ላይ ጌታ ኢየሱስ ወግንና ሥርዐትን ሁሉ ማውገዙ ሳይሆን፣ ያወገዘው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጨውን ወግና ሥርዐት ብቻ ነበር። ወግና ሥርዐት ወይም ደንቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ትይዩ ሆነው በሚገኙት እውነቶች ላይ መመሥረት አለባቸው (ከ2ተሰ 2፥15 ጋር ያነጻጽሩ)። አብያተ ክርስቲያናት ሃይማኖታዊ ሥርዐትንና ወግን፣ ሰብአዊ ጥበብን፣ ወይም ዘመን አመጣሽ ልማድን ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ አክብሮ የመያዝ አዝማሚያን መቃወም አለባቸው። ስሕተት አልባ የሆነው የእምነትና የተግባር መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፤ በሰው ሐሳብ ይሻር ዘንድ ከቶ አይገባም (ቍ 13፤ ማቴ 15፥6 እና ማብ ይመ)።

**7፥18 ሊያረክሰው የሚችል፤** ጌታ ኢየሱስ ከዚህ ላይ የሚናገረው ወደ ሰው ሆድ ስለሚገባው ግን ስለማያረክሰው ምግብ ነው (ቍ 19)። ይህ ጥቅስ ጐጂ ዕፅ እንዲወሰድ ወይም የአልኮል መጠጥ እንዲጠጣ ለመደገፍ ሲባል ሊጠቀስ አይችልም፤ እንደነዚህ ያሉትን መውሰድ ውጤቱ በቍ 21-22 ላይ ለተዘረዘረው ኀጢአት ሁሉ ባሪያ መሆን ነውና (ምሳ 23፥31 እና ማብ ይመ)።

**7፥20-23 ከሰው ልብ፤** በዚህ ምንባብ ላይ፣ "ሰውን ያረክሰዋል" (ቍ 20) ማለት ከሰው ልብ ከሚወጣ ኀጢአት የተነሣ ከሕይወት፣ ከድነትና ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት መለየት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ፣ "ልብ" ሲባል የአእምሮ፣ የስሜት፣ የፍላጎትንና የፈቃድን መቀመጫ የሆነውን አጠቃላዩን አካል ያመለክታል፤ (በገጽ 932 ላይ፣ ***"ልብ"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ንጹሕ ያልሆነ ልብ የአንድን ሰው ሐሳብ፣ ስሜት፣ ቃልና ተግባር ያጐድፋል (ምሳ 4፥23፤ ማቴ 12፥34፤ 15፥19)። የሚያስፈልገው አዲስ የሆነ፣ የተቀደሰና በክርስቶስ አምሳል የተቀረጸ ልብ ነው (ሉቃ 6፥45 ይመ፤ በገጽ 1606 ላይ፣ ***"ዳግም ልደት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**7፥27 የልጆችን እንጀራ፤** "ልጆች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤልን ነው። ወንጌል በመጀመሪያ ወደ እስራኤል መድረስ እንዳለበት ኢየሱስ ጕልሕ አድርጎ ያሳያል። ሲሮፊኒቃዊቷ ሴት ይህንኑ ተረድታለች፤ ይሁን እንጂ ለጌታ ኢየሱስ

28እርሷም መልሳ፣ "አዎን፣ ጌታ ሆይ፤
ውሾችም ከገበታ በታች ሆነው የልጆችን
ትራፊ ይበላሉ አለችው።
29እርሱም፣ "ስለዚህ ይህን ስላልሽ ሂጂ፤
ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቶአል" አላት።
30እርሷም ወደ ቤቷ ስትመለስ ልጂ ዐልጋ
ላይ ተኝታ፣ ጋኔኑም ለቆአት አገኘቻት።

## የደንቈሮውና የድዳው መፈወስ

*7፥31-37 ተዓ ምብ — ማቴ 15፥29-31*

31ከዚያም ኢየሱስ ከጢሮስ አገር
ተነሥቶ፣ በሲዶና በኩል አድርጎ ዐሥር
ከተማ[a] በተባለው አገር በማለፍ ወደ ገሊላ
ባሕር መጣ። 32በዚያም ሰዎች ደንቈሮና
ዲዳ የሆነ አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ፤
እጁንም እንዲጭንበት ለመኑት።
33ኢየሱስም ሰውየውን ከሕዝቡ ለይቶ
ከወሰደው በኋላ፣ ጣቶቹን በጆሮው
አስገባ፤ ከዚያም እንትፍ ብሎ የሰውየውን
ምላስ ዳሰሰ። 34ወደ ሰማይም ተመልክቶ
ቃተተና፣ "ኤፍታህ!" አለው፤ ይኸውም፣
"ተከፈት" ማለት ነው። 35ወዲያውም
ጆሮዎቹ ተከፈቱ፤ ምላሱም ተፈቶ አጥርቶ
መናገር ጀመረ።
36ኢየሱስ ይህን ለማንም እንዳይናገሩ
አዘዛቸው፤ ሆኖም እርሱ እንዳይናገሩ
ባዘዛቸው መጠን፣ ነገሩን አስፋፍተው አወሩት።
37ሕዝቡም ከመጠን በላይ በመደነቅ፣
"ያደረገው ሁሉ ጥሩ ነው፤ ደንቈሮዎች
ሉቃ 6፥17-19 እንዲሰሙ፣ ድዳዎች እንዲናገሩ እንኳ
አድርጎአል" አሉ።

## ኢየሱስ አራት ሺህ ሰዎች መገበ

*8፥1-9 ተዓ ምብ — ማቴ 15፥32-39*
*8፥1-9 ማመ — ማር 6፥32-44*
*8፥11-21 ተዓ ምብ — ማቴ 16፥1-12*

8 በዚያን ጊዜ፣ እንደ ገና ብዙ ሕዝብ
ተሰበሰበ። የሚበሉት ምንም ምግብ
ስላልነበራቸው ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ
ጠርቶ፣ እንዲህ አላቸው፤ 2"ከእኔ ጋር ሦስት

7፥31 ቍ 24፤ ማቴ4፥18:25፤ 11፥21፤ ማር5፥20
7፥32 ማቴ9፥32፤ ማር5፥23፤ ሉቃ11፥14
7፥33 ማር8፥23
7፥34 ማር6፥41፤ 8፥12፤ ዮሐ11፥41
7፥35 ኢሳ35፥5:6
7፥36 ማቴ8፥4
8፥2 ማቴ9፥36
8፥7 ማቴ14፥19
8፥8 ቍ 20
8፥11 ማቴ12፥38
8፥12 ማር7፥34
8፥15 ማቴ14፥1፤ ማር12፥13፤ ሉቃ12፥1፤ 1ቆሮ5፥6-8

ቀን ስለቈዩና የሚበሉትም ስለሌላቸው
እነዚህ ሰዎች ያሳዝኑኛል፤ 3እንዲህ እንደ
ተራቡ ወደ ቤታቸው ብሰዳቸው አንዳንዶቹ
ከሩቅ የመጡ ስለ ሆኑ በመንገድ ላይ ዝለው
ይወድቃሉ።"
4ደቀ መዛሙርቱም መልሰው፣ "በዚህ
ምድረ በዳ እነዚህን ለመመገብ የሚያስችል
እንጀራ ከወዴት ይገኛል?" አሉት።
5እርሱም፣ "ስንት እንጀራ አላችሁ?"
ብሎ ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ "ሰባት" አሉት።
6እርሱም፣ መሬት ላይ እንዲቀመጡ
ሕዝቡን አዘዘ፤ ሰባቱን እንጀራ ይዞ ካመሰገነ
በኋላ ቈርሶ ለሰዎቹ እንዲያድሉ ለደቀ
መዛሙርቱ ሰጣቸው፤ እነርሱም ለሕዝቡ
አደሉት። 7እንዲሁም ትንንሽ ዓሣዎች
ነበሯቸው፤ እርሱም ዓሣዎቹን ባርኮ
እንዲያድሏቸው አዘዘ። 8ሕዝቡም በልተው
ጠገቡ፤ ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ የተረፈውን
ቍርስራሽ ሰባት መሶብ ሙሉ አነሡ።
9በዚያም አራት ሺህ ያህል ሰዎች ነበሩ፤
ካሰናበታቸውም በኋላ፣ 10ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ዳልማ ኑታ ወደ ተባለ ስፍራ ሄደ።
11ፈሪሳውያንም ወጥተው ከኢየሱስ ጋር
ይከራከሩ ጀመር። ሊፈትኑትም ፈልገው
ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት።
12እርሱም በመንፈሱ እጅግ በመቃተት፣
"ይህ ትውልድ ምልክት የሚፈልገው
ለምንድን ነው? እውነት እላችኋለሁ፤ ለዚህ
ትውልድ ምንም ምልክት አይሰጠውም!"
አለ። 13ከዚያም ትቶአቸው በጀልባ ወደ
ማዶ ተሻገረ።

## የፈሪሳውያንና የሄሮድስ እርሾ

14ደቀ መዛሙርቱ እንጀራ መያዝ ስለ
ረሱ፣ ከአንድ እንጀራ በቀር በጀልባ ውስጥ
ምንም አልነበራቸውም። 15ኢየሱስም፣
"ተጠንቀቁ፤ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ

*[a]7፥31 የግሪኩ ዴካፖሊስ ይለዋል*

ምላሽ የሰጠችው በጥበብ፣ በጽናትና በእምነት ነው:: እግዚአብሔር እስራኤልን ሲባርክ፣ አሕዛብ ኢ-ርቱዕ በሆነ መንገድ በረከቱን እንዲቀበሉ መደረጉ የእግዚአብሔር ዕላማ መሆኑን በመግለጽ ይህች ሴት ሐሳቧን በጥሞና አቅርባለች:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ልጇን በመፈወስ ጽኑ እምነቷን አሞግሶአል (ቍ 28-30):: አማኞች ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች በጸሎት ላይ ሳሉ በጽናት መጸለይ አለባቸው፤ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት የክርክር ሐሳብ ሊሰነዝሩ ይችላሉ (ማቴ 15፥28 እና ማብ ይመ)::

**8፥2 ያሳዝኑኛል፤** ኢየሱስ ስለ ሰው ዘር ችግርና ሥቃይ ዐዝኖአል (1፥41 ይመ):: ዛሬም ቢሆን ጌታ ኢየሱስ ስለ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ችግርና ጕዳት ጥልቅ ርኅርኄ በተሞላበት ስሜት ልቡ ይነካል:: ለእኛም ችግር ሲያጋጥመን ጸጋውን፣ ምሕረቱንና ርዳታውን ለማግኘት በጸሎት ወደ እርሱ መቅረብ እንደምንችል ያረጋግጥልናል (ማቴ 6፥31-32፤ ዕብ 4፥14-16፤ 7፥25)::

**8፥15 እርሾ፤** በአዲስ ኪዳን፣ "እርሾ" ብዙውን ጊዜ የክፋት ወይም የብክለት ትእምርት ነው (ማቴ 13፥33፤ 16፥6:11፤ ሉቃ 12፥1፤ 1ቆሮ 5፥6-8፤ ገላ 5፥9 ይመ፤ ዘፀ 13፥7 እና ማብ ይመ):: ትንሽ እርሾ ብዙው እንዲቦካ ወይም እንዲለወጥ ያደርጋል:: (1) የፈሪሳውያን እርሾ ሲባል እነዚህ በስም የተጠቀሱት የእግዚአብሔርን ጻድቅ ትእዛዛት ወደ ጐን የሚተዉበትን፣ ከቃሉና ከፈቃዱም የተወሰነውን ዋጋ ቢስ የሚያደርጉበትን ሃይማኖታዊ ወጋቸውን ያመለክታል (7፥5-8 እና ማብ ይመ):: (2) የሄሮድስ እርሾ ከሰዱቃውያን እርሾ ጋር አንድ ነው፤ ይህም ለዚህ ዓለም ነገር መጨነቅንና የምቾት ሕይወትን የሙጥኝ ማለትን ያመለክታል (ማቴ 3፥7 እና ማብ ይመ):: የክርስቶስ ተከታዮች የሰውን ሐሳብ፣ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ወግ ወይም የዚህን ዓለም ጕዳይንና ሰው ሠራሽ የሆነውን ነገር ከሚሰብኩ ቡድኖች ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው:: "የሄሮድስን እርሾ" መቀበል ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስና ለቃሉ ጀርባዋን እንድትሰጥ ያደርጋታል::

ተጠበቁ" ብሎ አዘዛቸው።
[16]እነርሱም እርስ በርሳቸው፣ "እንዲህ
የሚለን እኮ እንጀራ ስለሌለን ነው"
ተባባሉ።
[17]ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ፣
እንዲህ አላቸው፤ "እንጀራ ስለሌለን ነው
በማለት ምን ያነጋግራችኋል? አሁንም
አታስተውሉምን? ልብስ አትሉምን? ወይስ
ልባችሁ ደንድኖአል? [18]ዐይን እያላችሁ
አታዩምን? ጆሮ እያላችሁ አትሰሙምን?
አታስታውሱምን? [19]አምስቱን እንጀራ
ለአምስት ሺህ ሰው በቈረስሁ ጊዜ ስንት
መሶብ ሙሉ ትርፍራፊ አነሣችሁ?"
እነርሱም፣ "ዐሥራ ሁለት" አሉት።
[20]"ሰባቱንስ እንጀራ ለአራት ሺህ
በቈረስሁ ጊዜ ስንት መሶብ ሙሉ ትርፍራፊ
አነሣችሁ?" አላቸው።
እነርሱም፣ "ሰባት" አሉት።
[21]እርሱም፣"እስከ አሁን አላስተዋላችሁም
ማለት ነውን?" አላቸው።

## በቤተ ሳይዳ የተፈወሰው ዐይነ ስውር

[22]ከዚያም ወደ ቤተ ሳይዳ መጡ፤
ጥቂት ሰዎችም አንድ ዐይነ ስውር ወደ
ኢየሱስ አምጥተው እንዲዳስሰው ለመኑት።
[23]እርሱም የዐይነ ስውሩን እጅ ይዞ ከሰፈር
ውጭ አወጣው፤ በዐይኖቹም ላይ እንትፍ
ብሎበት፣ እጁንም በላዩ ጭኖ፣ "ምን
የሚታይህ ነገር አለ?" ሲል ጠየቀው።
[24]እርሱም ቀና ብሎ አይቶ፣ "ሰዎች
እንደ ዛፍ ሲንቀሳቀሱ አያለሁ" አለ።
[25]ኢየሱስም እንደ ገና እጆቹን በሰውየው
ዐይኖች ላይ ጫነ፤ በዚህ ጊዜ ዐይኖቹ
በሩ፤ ብርሃኑም ተመለሰለት፤ ሁሉንም ነገር
አጥርቶ ማየት ቻለ። [26]ከዚያም፣ "ወደ
መንደሩ አትግባ! በመንደሩም ለማንም
አትናገር[ሀ]" ብሎ ወደ ቤቱ ሰደደው።

8፥17
ኢሳ6፥9፡10፤
ማር6፥52
8፥19
ማቴ14፥20፤
ማር6፥41-44፤
ሉቃ9፥17፤
ዮሐ6፥13
8፥20 ቍ6-9፤
ማቴ15፥37
8፥21 ማር6፥52
8፥22
ማቴ11፥21፤
ማር10፥46፤
ዮሐ9፥1
8፥23 ማር5፥23፤
7፥33
8፥28 ማቴ3፥1፤
ሚል4፥5
8፥29 ዮሐ6፥69፤
11፥27
8፥30 ማቴ8፥4፤
16፥20፤ 17፥9፤
ማር9፥9፤
ሉቃ9፥21
8፥31 ማቴ8፥20፤
16፥21፤
ማቴ27፥1፡2፤
ሐሥ2፥23፤ 3፥13
8፥32 ዮሐ18፥20
8፥33 ማቴ4፥10
8፥34
ማቴ10፥38፤
ሉቃ14፥27

## ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ የነበረው ግንዛቤ

*8፥27-29 ተጓ ምብ — ማቴ 16፥13-16፤ ሉቃ 9፥18-20*

[27]ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ
ፊልጶስ ቂሳርያ መንደሮች ሄደ፤ በመንገድ
ላይ ሳሉም ደቀ መዛሙርቱን፣ "ሰዎች እኔን
ማን ይሉኛል?" ብሎ ጠየቃቸው።
[28]እነርሱም፣ "መጥምቁ ዮሐንስ የሚሉህ
አሉ፤ ሌሎች ኤልያስ ነው ይሉሃል፤ ሌሎች
ደግሞ ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ" ብለው
ነገሩት።
[29]ቀጥሎም፣ "እናንተሳ ማን
ትሉኛላችሁ?" ሲል ጠየቃቸው።
ጴጥሮስም፤ "አንተ ክርስቶስ[ለ] ነህ"
አለው።
[30]ኢየሱስም ስለ እርሱ ለማንም
እንዳይናገሩ አስጠነቀቃቸው።

## ኢየሱስ ስለ ሞቱ አስቀድሞ ተናገረ

*8፥31—9፥1 ተጓ ምብ — ማቴ 16፥21-28፤ ሉቃ 9፥22-27*

[31]ከዚያም የሰው ልጅ ብዙ መከራ
እንደ ሚቀበል፣ በሽማግሌዎች፣ በካህናት
አለቆችና በጸሐፍት እንደሚናቅ፣
እንደሚገደል፣ ከሦስት ቀንም በኋላ
እንደሚነሣ ያስተምራቸው ጀመር።
[32]እርሱም ይህን በግልጽ ነገራቸው።
በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ኢየሱስን ለብቻው ወስዶ
ይገሥጸው ጀመር።
[33]ኢየሱስ ግን ዞወር ብሎ ደቀ
መዛሙርቱን እያየ ጴጥሮስን፣ "አንተ
ሰይጣን፣ ወደ ኋላዬ ሂድ! አንተ የሰውን
እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብምና"
በማለት ገሠጸው።
[34]ከዚህ በኋላ፣ ሕዝቡን ከደቀ መዛሙርቱ

*ሀ8፥26 አንዳንድ ቅጆች በመንደሩም፡ ለማንም አትናገር የሚለው የላቸውም።*
*ለ8፥29 በግሪኩ ክርስቶስ፣ በዕብራይስጡ መሲሕ የሚለው ቃል ትርጕም የተቀባ ማለት ነው*

**8፥25 ዐይኖቹ በሩ፤** ኢየሱስ በቤተ ሳይዳ ያደረገው ፈውስ፣ ቀስ በቀስ ያከናወነው ብቸኛ ፈውስ ነው፤ ይህም ፈውስ ሁሉ የግድ ከመቅጽበት መከናወን እንደሌለበት ያስተምራል፤ በአንዳንድ ሁናቴ መለኮታዊ ኀይል በሕመም ላይ የሚኖረው አሸናፊነት ቀስ በቀስ የሚሆን ነውና።
**8፥34 መስቀሉንም ተሸክሞ፤** የክርስቶስ መስቀል **የሥቃይ** (1ጴጥ 2፥21፤ 4፥13)፤ **የሞት** (ሐሥ 10፥39)፣ **የኀፍረት** (ዕብ 12፥2)፣ **የመንቋሸሽ** (ማቴ 27፥39)፣ **የመጠላት** (1ጴጥ 2፥4) እና ራስን የመካድ (ማቴ 16፥24) ትእምርት ነው። አማኞች ሆነን መስቀላችንን ተሸክመን ክርስቶስን ስንከተል፣ ራሳችንን እንክዳለን (ሉቃ 14፥26-27)፤ በአራት አቅጣጫ ለሚካሄደው ትግልና ሥቃይም ራሳችንን አሳልፈን እንሰጣለን፦

(1) ኀጢአተኛ ፍላጎታችንን በመስቀል (ሮሜ 6፤ 8፥13፤ ገላ 2፥20፤ 6፥14፤ ቲቶ 2፥12፤ 1ጴጥ 2፥11፡21-24)፣ ከኀጢአት ጋር የዕድሜ ልክ ጦርነት እናካሂዳለን (ሮሜ 6፤ 1ጴጥ 4፥1-2)።

(2) የእግዚአብሔርን መንግሥት ስናስፋፋ (2ቆሮ 10፥4-5፤ 6፥7፤ ኤፌ 6፥12፤ 1ጢሞ 6፥12) ከሰይጣንና ከጨለማ ኀይላት ጋር ጦርነት እናካሂዳለን። በዚህ ከሚገኘው ጋኔናዊ ስራዊትና (2ቆሮ 6፥3-7፤ 11፥23-29፤ 1ጴጥ 5፥8-10) እውነተኛውን ወንጌል ከሚያጣምሙ ሐሰተኛ መምህራን አቋም በሚመጣ ስደት (2ቆሮ 6፥3-7፤ 11፥23-29፤ 1ጴጥ 5፥8-10)፣ በሚደርስብንም የጦርነትና የጠላትነት ተመክሮ ሁሉ ውስጥ እናልፋለን (ማቴ 23፥1-36፤ ገላ 1፥9፤ ፊል 1፥15-17)።

(3) የዓለም ሥራ ክፉ መሆኑን በፍቅር በመመስከራችን (ዮሐ 7፥7)፣ በግብረገባዊነትም ሆነ በመንፈሳዊ ረገድ ራሳችንን ከዓለም በማግለላችን (በገጽ 1826 ላይ፣ *"የአማኞች መለየት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ የዓለምን መስፈርት ወይም ፍልስፍና የራሳችን አድርገን ለመቀበል እምቢተኞች በመሆናችን (1ቆሮ 1፥21-27) የዓለም ጥላቻና መንቋሸሽ ይደርስብናል (ዮሐ 15፥18-25፤ ዕብ 11፥25-26)።

(4) ሃይማኖተኛ ከሆነው ዓለምም እንደ ጌታ ኢየሱስ መንቋሸሽና ስደት ሊደርስብን ይችላል (ቍ 31፤ ቍ 15 እና ማብ ይመ)።

ጋር ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤
"ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤
መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፤ 35ነፍሱን″
ለማዳን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ
እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋት ሁሉ
ግን ያድናታል። 36ሰው ዓለሙ ሁሉ የእርሱ
ቢሆ ንና ነፍሱን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል?
37ለመሆኑ፣ ሰው ለነፍሱ ምን መተኪያ
አለው? 38በዚህ ዘማዊና ኀጢአተኛ ትውልድ
መካ ከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፣
የሰው ልጅም በአባቱ ግርማ፣ ከቅዱሳን
መላእክት ጋር ሲመጣ ያፍርበታል።"

9 ቀጥሎም፣ "እውነት እላችኋለሁ፤
እዚህ ከቆሙት መካከል የእግዚአብሔር
መንግሥት በኀይል ስትመጣ እስኪያዩ
ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ"
አላቸው።

## የኢየሱስ መልክ አበራ

*9፥2-8 ተጓ ምብ — ሉቃ 9፥28-36*
*9፥2-13 ተጓ ምብ — ማቴ 17፥1-13*

2ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን፣
ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከትሎ ወደ
አንድ ረጅም ተራራ ይዞአቸው ወጣ፤
ብቻቸውንም ነበሩ፤ በፊታቸውም ተለወጠ፤
3ልብሱም በምድር ላይ ማንም አጣቢ አጥቦ
ሊያነጣው በማይችልበት ሁናቴ እጅግ ነጭ
ሆነ። 4ኤልያስና ሙሴም ከኢየሱስ ጋር
ሲነጋገሩ ታዩአቸው።
5ጴጥሮስም ኢየሱስን፣ "መምህር ሆይ፣
እዚህ ብንኖር ለእኛ መልካም ነው፤ አንድ
ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ ለኤልያስ የሚ
ሆኑ ሦስት ዳሶች እንሥራ" አለው። 6እጅግ
ስለ ፈሩ የሚናገረውን አያውቅም ነበር።
7ከዚያም ደመና መጥቶ ጋረዳቸው፤
ከደመናውም ውስጥ፣ "ይህ የምወደው
ልጄ ነው፤ እርሱን ስሙት!" የሚል ድምፅ
መጣ።
8ወዲያውም ዙሪያቸውን ሲመለከቱ
ከኢየሱስ በቀር ማንም አብሮአቸው
አልነበረም።
9ከተራራው ላይ በሚወርዱበትም ጊዜ፣
የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያዩትን
ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው። 10እነርሱም
የተናገራቸውን ቃል በልባቸው አሳደሩት፤
ነገር ግን፣ "ከሙታን መነሣት" ምን ማለት
እንደ ሆነ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።
11ከዚያም፣ "ጸሐፍት አስቀድሞ መምጣት

8፥35 ዮሐ12፥25
8፥38 ማቴ8፥20፤ 10፥33፤ ሉቃ12፥9፤ 1ተሰ2፥19
9፥1 ማቴ24፥30፤ 25፥31፤ ማር13፥30፤ ሉቃ22፥18
9፥2 ማቴ4፥21
9፥3 ማቴ28፥3
9፥5 ማቴ23፥7
9፥7 ዘዐ24፥16፤ ማቴ3፥17
9፥9 ማቴ8፥20፡30
9፥12 ማቴ8፥20፤ 16፥21፤ ሉቃ23፥11
9፥13 ማቴ11፥14
9፥20 ማር1፥26
9፥23 ማቴ21፥21፤ ማር11፥23፤ ዮሐ11፥40

ያለበት ኤልያስ ነው ለምን ይላሉ?" ሲሉ
ጠየቁት።
12ኢየሱስም፣ እንዲህ አላቸው፤ "ኤልያስ
በርግጥ አስቀድሞ መጥቶ ሁሉን ነገር
እንደ ነበረ ያደርጋል፤ ታዲያ፣ የሰው ልጅ
ብዙ መከራ መቀበልና መናቅ እንዳለበት
የተጻፈው ለምን ይመስላችኋል? 13ነገር
ግን እላችኋለሁ፤ ኤልያስማ መጥቶ ነበር፤
እነር ሱም ስለ እርሱ በተጻፈው መሠረት
ያሻቸውን ሁሉ አድርገውበታል።"

## ርኩስ መንፈስ ያለበት ልጅ ተፈወሰ

*9፥14-28፤ 30፥32 ተጓ ምብ — ማቴ 17፥14-*
*19፤ 22:23፤ ሉቃ 9፥37-45*

14ወደ ቀሩት ደቀ መዛሙርት ተመልሰው
ሲመጡ፣ ብዙ ሕዝብ ከበዋቸው፣ ጸሐፍት
ከእነርሱ ጋር ሲከራከሩ አዩ። 15ሕዝቡ ሁሉ
ሲያዩት ወዲያው ተደንቀው እጅ ሊነሡት
ወደ እርሱ ሮጡ።
16እርሱም፣ "ከእነርሱ ጋር የምትከራከሩት
ስለምን ጉዳይ ነበር" ሲል ጠየቃቸው።
17ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው
እንዲህ አለው፤ "መምህር ሆይ፤ ርኩስ
መንፈስ እድሮበት ድዳ የሆነውን ልጄን
ወደ አንተ አምጥቼዋለሁ፤ 18በተነሣበት
ጊዜ ሁሉ ይጥለዋል፤ አረፋ ይደፍቃል፤
ጥርሱንም ያፋጫል፤ ሰውነቱም ይደርቃል፤
ርኩስ መንፈሱን እንዲያስወጡት ደቀ
መዛሙርትህን ጠየቅኋቸው፤ እነርሱ ግን
አልቻሉም።"
19ኢየሱስም መልሶ፣ "የማታምን
ትውልድ ሆይ፤ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር
እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ?
ልጁን ወደ እኔ አምጡት!" አላቸው።
20ስዎቹም ወደ እርሱ አመጡት፤ ርኩስ
መንፈሱም ኢየሱስን ባየው ጊዜ ልጁን
ወዲያውኑ አንዘፈዘፈው፤ እርሱም መሬት
ላይ ወድቆ በመንፈራገጥም አረፋ ይደፍቅ
ጀመር።
21ኢየሱስም የልጁን አባት፣ "ከያዘው
ስንት ጊዜው ነው?" ብሎ ጠየቀው።
እርሱም እንዲህ አለው፤ "ከሕፃንነቱ
ጀምሮ ነው፤ 22ሊገድለው ፈልጎ ብዙ ጊዜ
እሳትም ውስጥ ውሃም ውስጥ፣ ይጥለዋል፤
የሚቻልህ ከሆነ ራራልን፤ ርዳንም።"
23ኢየሱስም፣ "የሚቻልህ ከሆነ አልህ?

*″8፥35 የግሪኩ ቃል ሕይወት ወይም ነፍስ ማለት ይሆናል።*

**8፥38 በእኔና በቃሌ የሚያፍር፤** ጌታ ኢየሱስ እኛ የምንኖርበትን ዓለምና ኅብረተሰብ፣ «ዘማዊና ኀጢአተኛ ትውልድ» መሆኑን ገልጾአል። ክርስቶስንና ጻድቅ መንገዱን ከመከተል ይልቅ፣ አሁን በሚገኙበት ዓለም ዘንድ ዝናን ለማትረፍ ወይም ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ የሚሯሯጡ ሁሉ፣ ክርስቶስ ሲመለስ፣ «ከቶ አላውቃችሁም» ይባላሉ (ከማቴ 7፥23፤ 25፥41-46 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሉቃ 9፥26 እና ማብ፤ 13፥27 ይመ)።

**9፥1 የእግዚአብሔር መንግሥት በኀይል፤** ማቴ 16፥28 እና ማብራሪውን ይመልከቱ።

**9፥2 ተለወጠ፤** ሉቃ 9፥29 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**9፥19 የማታምን ትውልድ፤** የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በአጋንንት ላይ ውጤታማ የሆነ ጦርነት ባለማካሄዳቸው፣ በመንፈሳዊ ረገድ ደካማ መሆናቸው ከዚህ ላይ ይታያል (ማቴ 17፥17 እና ማብ ይመ)።

**9፥23 ሁሉም ነገር ይቻላል፤** ጌታ ኢየሱስ ከዚህ ላይ የሰጠው ሐሳብ ገደብ የለሽ ተስፋ ተደርጎ መቈጠር የለበትም፤ (1) «ሁሉም ነገር» ሲባል ከአእምሮአችን ላይ ያቃጨለው ነገሩ ሁሉ ማለት አይደለም። ከእምነት

ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል"
አለው።
24ወዲያውኑ የልጁ አባት፣ "አምናለሁ፤
አለማመኔን ርዳው!" በማለት ጮኸ።
25ኢየሱስም ሕዝቡ ወደዚያ እየተንጋጋ
በሩጫ መምጣቱን ባየ ጊዜ፣ "አንተ ደንቈሮና
ድዳ መንፈስ ከእርሱ ውጣ! ከእንግዲህም
ተመልሰህ እንዳትገባበት አዝሃለሁ" ብሎ
ርኩሱን[ሀ] መንፈስ ገሠጸው።
26ርኩሱም መንፈስ እየጮኸ ክፉኛ
ካንፈራገጠው በኋላ ከልጁ ወጣ፤ ብዙዎቹ
"ሞቶአል" እስኪሉ ድረስ ልጁ እንደ በድን
ሆነ። 27ኢየሱስ ግን እጁን ይዞ አስነሣው፤
ልጁም ተነሥቶ ቆመ።
28ኢየሱስ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ
መዛሙርቱ ለብቻቸው፣ "እኛ ልናስወጣው
ያልቻል ነው ለምንድን ነው?" ብለው
ጠየቁት።
29እርሱም፣ "የዚህ ዐይነቱ ሊወጣ
የሚችለው በጸሎትና በጾም[ለ] ብቻ ነው"
አላቸው።
30ከዚያም ተነሥተው በገሊላ በኩል
አለፉ፤ ኢየሱስም ያሉበትን ስፍራ
ማንም እንዲያውቅ አልፈለገም፤ 31ለደቀ
መዛሙርቱ፣ "የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ዐልፎ
ይሰጣል፤ እነርሱም ይገድሉታል፤ ከሦስት
ቀንም በኋላ ይነሣል" እያለ ያስተምራቸው
ነበር። 32እነርሱ ግን የሚላቸው
አልገባቸውም፤ እንዳይጠይቁትም ፈሩ።

### ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?

*9፥33-37 ተጓ ምብ — ማቴ 18፥1-5፤ ሉቃ 9፥46-48*

33ከዚህ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም መጡ።
ቤት ከገባ በኋላም፣ "በመንገድ ላይ
የምትከራከሩት ስለ ምን ነበር?" ብሎ
ጠየቃቸው። 34እነርሱ ግን በመንገድ ላይ
የተከራከሩት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው
በሚል ስለ ነበር ዝም አሉ።
35ከተቀመጠ በኋላ ዐሥራ ሁለቱን
ጠርቶ፣ "መጀመሪያ ለመሆን የሚፈልግ፣
ከሁሉ መጨ ረሻና የሁሉም አገልጋይ
ይሁን" አላቸው።
36ትንሽ ልጅ አምጥቶም በመካከላቸው
አቆመ፤ አቅፎትም፣ 37"ከእነዚህ ሕፃናት
አንዱን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን
ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበለኝ ሁሉ
የሚቀበለው እኔን ሳይሆን የላከኝን ነው"
አላቸው።

### የማይቃወመን ሁሉ ከእኛ ጋር ነው

*9፥38-40 ተጓ ምብ — ሉቃ 9፥49:50*

38ዮሐንስም፣ "መምህር ሆይ፤ አንድ
ሰው በስምህ አጋንንት ሲያወጣ አየን፣ እኛን
ስለ ማይከተልም ከለከልነው" አለው።
39ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ፤
"አትከልክሉት፤ ማንም በስሜ ታምር
ሠርቶ ወዲያውኑ በእኔ ላይ ክፉ መናገር
አይችልም፤ 40የማይቃወመን ሁሉ ከእኛ
ጋር ነውና፤ 41እውነት እላችኋለሁ፣
የክርስቶስ በመሆናችሁ በስሜ አንድ ኩባያ
ውሃ የሚሰጣችሁ ሁሉ ዋጋውን አያጣም።"

### ለሌላው መሰናክል መሆን

42"በእኔከሚያምኑትከእነዚህከታናናሾቹ
አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ ከባድ የወፍጮ
ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል
ይሻለዋል። 43ስለዚህ እጅህ ብታሰናክልህ
ቍረጣት፤ ሁለት እጅ ኖሮህ ወደ ገሃነም
ከመሄድ፣ ጕንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት

9፥25 ቊ15
9፥28 ማር7፥17
9፥31 ቊ12፤ ማቴ8፥20፤ 16፥21፤ ሐሥ2፥23፤ 3፥13
9፥32 ሉቃ2፥50፤ 9፥45፤ 18፥34፤ ዮሐ12፥16
9፥33 ማቴ4፥13፤ ማር1፥29
9፥34 ሉቃ22፥24
9፥35 ማቴ18፥4፤ ማር10፥43፤ ሉቃ22፥26
9፥36 ማር10፥16
9፥37 ማቴ10፥40
9፥38 ዘኍ11፥27:29
9፥40 ማቴ12፥30፤ ሉቃ11፥23
9፥41 ማቴ10፥42
9፥42 ማቴ5፥29፤ 18፥6፤ ሉቃ17፥2
9፥43 ማቴ5፥29:30፤ 18፥8፤ 25፥41

*ሀ9፥25 ወይም ክፉ*
*ለ9፥29 አንዳንድ ቅጆች በጾም የሚለው የላቸውም*

---

የሆነ ጸሎት በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ መመሥረት አለበት፤ በዚህ ዐይነቱ ጸሎት ርባናቢስ የሆነው ወይም ትክክል ያልሆነው ነገር አይጠየቅም (ያዕ 4፥3):: (2) ከዚህ የሚፈለገውን እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ተደርጎ እንዲቀበሉት ያስፈልጋል:: እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ በታማኝነት በሚመላለሰው አማኝ ልብ ይህንኑ እምነት ያሳድራል (ማቴ 17፥20 እና ማብ ይመ)::

**9፥24 አለማመኔን ርዳው፤** በዚህ ዓለም ስንኖር፣ በእምንታችን ላይ ጥርጣሬ ይገባል፤ ይሁን እንጂ ይህ ድካም ስላለብን ክርስቶስ ለልመናችን መልስ አይሰጥም ማለት አይደለም፤ እርሱ ድካማችንን ያውቃል፤ ስለ ድካማችንም ያዝንልናልና (ዕብ 4፥15):: ብርቱ እምነት የሌለን መሆናችንን ዐውቀን ንስሓ በመግባት፣ አስፈላጊ የሆነውን እምነት እግዚአብሔር እንዲሰጠን መጸለይ ይኖርብናል (ማቴ 17፥20 እና ማብ ይመ)::

**9፥29 በጸሎትና ... ብቻ ነው፤** ኢየሱስ ይህ ዐይነቱ ክፉ መንፈስ እንዲወጣ ከመደረጉ በፊት የጸሎት ጊዜ አስፈላጊ ነው ማለቱ አይደለም፤ ይልቁንስ ከዚህ ላይ አንድ ቋሚ መርሕ ተሰተውሎአል፤ ይህ ነው የማይባል እምነት ባለበት ሕይወት ውስጥ፣ ግምት ውስጥ የማይገባ ጸሎት ይኖራል:: እግዚአብሔርን በመታመንና በቃሉ ላይ በመመሥረት በሚቀርብ ብርቱ ጸሎት ላይ ጠንካራ እምነት አለ:: ኢየሱስ እንዳደረገው ሁሉ፣ ደቀ መዛሙርቱ ዘላቂ የጸሎት ሕይወት ቢኖራቸው ኖሮ፣ የተከሠተውን ይህን ችግር ስኬታማ በሆነ መልክ ይወጡት ነበር::

**9፥34 ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?** ሉቃ 22፥24-30 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**9፥42 ከታናናሾቹ ... የሚያሰናክል፤** አማኞች በከፍተኛ ደረጃ ቅድሚያ ሰጥተው ከሚያከናውኗቸው ነገሮች አንዱ ለልጆች በአካሄድና በትምህርት አርአያ ሆኖ መገኘት ነው:: ይህን ሲያደርጉም ለእነርሱ ያላቸውን ልባዊ ፍቅር ይገልጻሉ:: ክርስቲያን ወላጆች ልጆቻቸውን ፈሪሀ እግዚአብሔር ከሌለው የዚህ ዓለም ተጽዕኖ ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው (ማቴ 18፥6 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1894 ላይ፣ *"ወላጆችና ልጆች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

**9፥43 ገሃነም፤** የተጠቀሰው ቦታ እሳት ምንጊዜም የማይጠፋበት በመሆኑ፣ የቱንም ያህል ዋጋ የሚያስከፍል ይሁን፣ ማንኛውንም ዐይነት የኀጢአት ተጽዕኖ መቋቋምና መጥላት ግዴታ ነው:: በኀጢአት ላይ የሞት ፍርድ ይፈረድበት ዘንድ አስፈላጊ ነው (ቈላ 3፥5)፤ በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት በእርሱ ላይ የምናካሂደውን ጦርነት ከቶ ማቋረጥ የለብንም (ሮሜ 8፥13፤ ኤፌ 6፥10)::

መግባት ይሻልሃል፤ 44በገሃነም ትሉ አይሞ
ትም፤ እሳቱ አይጠፋምና[*]። 45እግርህ
ብታሰናክልህ ቍረጣት፤ ሁለት እግር ኖሮህ
ወደ ገሃነም ከመጣል፣ አንካሳ ሆነህ ወደ
ሕይወት መግባት ይሻልሃል፤ 46በገሃነም ትሉ
አይሞትም እሳቱ አይጠፋምና[*]። 47ዐይንህ
ብታሰናክልህ ጐልጕለህ አውጣት፤ ሁለት
ዐይን ኖሮህ ወደ ገሃነም ከመጣል፣ አንድ
ዐይን ኖሮህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
መግባት ይሻልሃል፤

ሉቃ 6፥46-49

48በገሃነም ትሉ አይሞትም፤
እሳቱ አይጠፋምና፤
49ሰው ሁሉ በእሳት ይቀመማልና።
50"ጨው መልካም ነው፤ ነገር ግን ጨው
ጨውነቱን ቢያጣ እንዴት መልሳችሁ
ጣዕም እንዲኖረው ታደርጉታላችሁ? ጨው
በውስጣችሁ ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም
ተስማሙ።"

## የባልና የሚስት ፍች

*10፥1-12 ተጓ ምብ — ማቴ 19፥1-9*

10 ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ወደ ይሁዳ
አገርና በዮርዳኖስ ማዶ ወዳለው
አካባቢ ሄደ፤ ሕዝቡም እንደ ገና በዙሪያው
ተሰበሰበ፤ ከዚህ ቀደም ያደርገው እንደ
ነበረውም አስተማራቸው።
2አንዳንድ ፈሪሳውያንም መጥተው፣
"ሰው ሚስቱን መፍታት ይገባዋልን?"
ብለው ሊፈትኑት ጠየቁት።
3እርሱም መልሶ፣ "ሙሴ ምን ብሎ
አዘዛችሁ?" አላቸው።
4እነርሱም፣ "ሙሴማ የፍች ወረቀት
ጽፎ እንዲፈታት ፈቅዶአል" አሉ።
5ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"ሙሴ ይህን ሕግ የጻፈላችሁ ልባችሁ
ደንዳና በመሆኑ ነው። 6ነገር ግን በፍጥረት
መጀመሪያ እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ

9፥45 ማቴ5፥29፤ 18፥8
9፥47 ማቴ5፥29፤ 18፥9
9፥48 ኢሳ66፥24፤ ማቴ25፥41
9፥49 ዘሌ2፥13
9፥50 ማቴ5፥13፤ ሉቃ14፥34፡35፤ ሮሜ12፥18፤ 2ቆሮ13፥11፤ ቈላ4፥6፤ 1ተሰ5፥13
10፥1 ማቴ4፥23፤ ማር1፥15፤ 2፥13፤ 4፥2፤ 6፥6፡34፤ ዮሐ10፥40፤ 11፥7
10፥2 ማር2፥16
10፥4 ዘዳ24፥1-4፤ ማቴ5፥31
10፥5 መዝ95፥8፤ ዕብ3፥15
10፥6 ዘፍ1፥27፤ 5፥2
10፥8 ዘፍ2፥24፤ 1ቆሮ6፥16
10፥11 ሉቃ16፥18
10፥12 ሮሜ7፥3፤ 1ቆሮ7፥10፡11
10፥14 ማቴ25፥34
10፥15 ማቴ18፥3
10፥16 ማር9፥36
10፥17 ማር1፥40፤ ሉቃ10፥25፤ ሐሥ20፥32

ፈጠራቸው። 7ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን
ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣመራል[†]፤
8ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ከእንግዲህ
አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም፤
9ስለዚህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ማንም
አይለየው።"
10እንደ ገና ወደ ቤት በገቡ ጊዜ፣
ደቀ መዛሙርቱ ይህንኑ እንሥተው
ጠየቁት። 11እርሱም፣ "ማንም ሚስቱን
ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ በእርሷ ላይ
ያመነዝራል፤ 12እርሷም ባሏን ፈትታ ሌላ
ብታገባ ታመነዝራለች" አላቸው።

## ኢየሱስ ሕፃናትን ባረከ

*10፥13-16 ተጓ ምብ — ማቴ 19፥13-15፤ ሉቃ 18፥15-17*

13ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው፣ ሰዎች
ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱ
ግን ገሠጿቸው። 14ኢየሱስም ይህን ሲያይ
ተቈጥቶ እንዲህ አላቸው፤ "ሕፃናት ወደ
እኔ ይምጡ፤ አትከልክሏቸው፤ የእግዚአብሔር
መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና።
15እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መን
ግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበል ሁሉ ከቶ
አይገባባትም። 16ሕፃናቱንም ሀቀፋቸው፤
እጁንም ጭኖ ባረካቸው።

## ሀብታሙ ወጣት

*10፥17-31 ተጓ ምብ — ማቴ 19፥16-30፤ ሉቃ 18፥18-30*

17ከዚያ ተነሥቶ መንገዱን ሲጀምር፣
አንድ ሰው ወደ እርሱ እየሮጠ መጣ፤ በፊቱም
በጕልበቱ ተንበርክኮ፣ "ቸር መምህር ሆይ፤
የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ
ይገባኛል" አለው።

[*]9፥44 እና 46 እነዚህ ጥቅሶች በአንዳንድ ቅጆች አይገኙም።

[†]10፥7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ከሚስቱ ጋር ይጣመራል የሚለው የላቸውም።

9፥49 **በእሳት ይቀመማልና፤** እያንዳንዱ ከሁለቱ መንገዶች በአንዱ እሳት ይቀመማል፤ (1) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከልብ በሚከተሉት ላይ በሚደርሰው እንደ እሳት በሚለበልብ ፈተና (ሉቃ 14፥33-34፤ ዮሐ 15፥18-21) ወይም (2) በዚህ ዓለም ሳሉ ክርስቶስን አንቀበልም ያሉትን በሚያሠቃየው ገሃነም እሳት መሠቃየት ማለት ነው (ከ47-48 ጋር ያነጻጽሩ)።

9፥50 **ጨው፤** ማቴ 5፥13 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

10፥11 ***ያመነዝራል፤*** በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጸው በቀር የትዳር ጓደኛውን ፈትቶ ሌላ የሚያገባ ሁሉ በማመንዘር በእግዚአብሔር ላይ በደል ይፈጽማል (ሚል 2፥14 እና ማብ፤ ማቴ 19፥9 እና ማብ፤ 1ቆሮ 7፥15 ይመ)። በሌላ አባባል አንድን ፍች መንግሥት ወይም ማንኛውም ማኅበራዊ ተቋም ስለ ፈቀደው በእግዚአብሔር ፊት ትክክል ነው ወይም ሕጋዊ ነው ማለት አይደለም።

10፥14 **የእግዚአብሔር መንግሥት፤** ማቴዎስ አይሁድ የሚወዱትን፣ *"መንግሥተ ሰማይ"* የሚለውን አገላለጽ ጽፎት ይገኛል፤ ማርቆስ ግን፣ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* የሚለውን አባባል ጽፎአል። ይሁን እንጂ ትርጒሙ አንድ ነው። የሚከተሉትን ተጓዳኝ ምንባቦች ያነጻጽሩ፤ ማቴ 4፥17 ከማር 1፥15፤ ማቴ 5፥3 ከሉቃ 6፥20፤ ማቴ 11፥11 ከሉቃ 7፥28፤ ማቴ 10፥7 ከሉቃ 10፥9 ጋር ያነጻጽሩ (በገጽ 1443 ላይ፣ ***"የእግዚአብሔር መንግሥት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

10፥15 **እንደ ሕፃን፤** የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን መቀበል ማለት ገርና ትሑት በሆነ፣ እምነት በተሞላበትና በሙሉ ልብ መቀበል ማለት ሲሆን፣ ይኸውም ከኀጢአት ተመልሶ ክርስቶስን ጌታና አዳኝ፣ እግዚአብሔርንም የሰማይ አባት አድርጎ መቀበል ማለት ነው (ማቴ 18፥3 እና ማብ ይመ)።

10፥16 **ባረካቸው፤** ክርስቶስ፣ ስለ ልጆች ድነትና በመንፈሳዊ ሕይወት ረገድ ተኰትኩቶ የማደግ ጕዳይ ግድ ይለዋል። ክርስቲያን ወላጆች፣ ልጆቻቸውን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ማንኛውንም የጸጋ መሣሪያ ሁሉ መጠቀም አለባቸው፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀበላቸው፣ ሊወዳቸውና ሊባርካቸው ይናፍቃልና (ቍ 13-16፤ በገጽ 1894 ላይ፣ ***"ወላጆችና ልጆች"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

18ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
"ለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር
በስተቀር ቸር የለም፤ 19ትእዛዛትን
ታውቃለህ፤ አትግደል፤ አታመንዝር፤
አትስረቅ፤በሐሰትአትመስክር፤አታታልል፤
አባትህንና እናትህን አክብር።"
20ሰውየውም፣ "መምህር ሆይ፤ እነዚህን
ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄአለሁ"
አለው።
21ኢየሱስም ተመለከተውና ወደደው፤
"አንግዲያው አንድ ነገር ይጐድልሃል፤
ሂድና ያለህን ሁሉ ሽጥ፤ ለድኾችም ስጥ፤
በሰማይ የተከማቸ ሀብት ታገኛለህ፤ ከዚያ
በኋላ ና፤ ተከተለኝም" አለው።
22ሰውየው ይህን ሲሰማ ክፉኛ አዘነ፤ ብዙ
ሀብት ስለ ነበረውም እየተከዘ ሄደ።
23ኢየሱስ ዙሪያውን በመመልከት ደቀ
መዛሙርቱን፣ "ለሀብታሞች ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት መግባት እንዴት ከባድ ነገር
ነው!" አላቸው።
24ደቀ መዛሙርቱም በንግግሩ ተገረሙ፤
ኢየሱስ ግን እንደ ገና መልሶ እንዲህ
አላቸው፤ "ልጆች ሆይ[a]፤ ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት መግባት እንዴት ከባድ ነገር
ነው! 25ሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ
ቢያልፍ ይቀለዋል።"
26ደቀ መዛሙርቱም ይበልጥ በመገረም፣
"ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?" ተባባሉ።
27ኢየሱስም አያቸውና፣ "ይህ በሰው
ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን
እንዲህ አይደለም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ
ይቻላል" አላቸው።
28ጴጥሮስም፣ "እነሆ እኛ ሁሉን ትተን
ተከተልንህ" አለው።
29ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ሲል
ቤቱን ወይም ወንድሞቹን ወይም እኅቶቹን
ወይም እናቱን ወይም አባቱን ወይም ልጆ
ቹን ወይም ዕርሻውን የተወ ሁሉ፣ 30አሁን
በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን፣ ወንድሞ
ችን፣ እኅቶችን፣ እናቶችን፣ ልጆችንና ዕር
ሻን መቶ ዕጥፍ የማይቀበል፣ በሚመጣውም
ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይወርስ የለም።
31ነገር ግን ብዙ ፊተኞች የሆኑ ኋለኞች፣
ኋለኞች የሆኑም ፊተኞች ይሆናሉ።

10፥19
ዘጸ20፥12-16፤
ዘዳ5፥16-20
10፥21
ማቴ4፥19፤ 6፥20፤
ሉቃ12፥33፤
ሐሥ2፥45
10፥23
መዝ52፥7፤
62፥10፤
ማር4፥19፤
1ጢሞ6፥9፡10፡17
10፥24
ማቴ7፥13፤
ዮሐ3፥5
10፥25
ሉቃ12፥16-20፤
16፥19-31
10፥27
ማቴ19፥26
10፥28 ማቴ4፥19
10፥30
ማቴ6፥33፤
12፥32፤ 25፥46
10፥31
ማቴ19፥30
10፥32
ማር3፥16-19
10፥33
ማቴ8፥20፤
27፥1፡2፤
ሉቃ9፥51
10፥34
ማቴ16፥21፤
ሐሥ2፥23፤ 3፥13
10፥37
ማቴ19፥28
10፥38 ኢዩ38፥2፤
ማቴ20፥22፤
ሉቃ12፥50
10፥39
ሐሥ12፥2፤
ራእ1፥9
10፥43 ማር9፥35

## ኢየሱስ ዳግም ስለ ሞቱ አስቀድሞ ተናገረ

*10፥32-34 ተጓ ምብ — ማቴ 20፥17-19፤ ሉቃ 18፥31-33*

32ወደ ኢየሩሳሌም ለመውጣት በመንገድ
ላይ ሳሉ፣ ኢየሱስ ፊት ፊታቸው ይሄድ
ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ ተገረሙ፣ ሌሎች
የተከተሉት ደግሞ ፈርተው ነበር። ደግሞም
ዐሥራ ሁለቱን ከሕዝቡ ለይቶ ምን
እንደሚደርስበት ነገራቸው፤ 33እንዲህም
አላቸው፤ "ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፤
የሰው ልጅ ለካህናት አለቆችና ለጸሐፍት
ዐልፎ ይሰጣል፤ እነርሱም የሞት ፍርድ
ይፈርዱበታል፤ አሳልፈው ለአሕዛብ
ይሰጡታል፤ 34ያፌዙበታል፤ ይተፉበታል፣
ይገርፉታል፣ ከዚያም ይገድሉታል፤ እርሱ
ግን ከሦስት ቀን በኋላ ይነሣል።"

## የያዕቆብና የዮሐንስ ጥያቄ

*10፥35-45 ተጓ ምብ — ማቴ 20፥20-28*

35ከዚያም የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና
ዮሐንስ ወደ እርሱ ቀርበው፣ "መምህር
ሆይ፤ የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን
እንፈልጋለን" አሉት።
36እርሱም፣ "ምን እንዳደርግላችሁ
ትፈል ጋላችሁ?" አላቸው።
37እነርሱም፣ "በክብርህ ጊዜ አንዳችን
በቀኝህ፣ አንዳችን በግራህ እንድንቀመጥ
ፍቀድልን" አሉት።
38ኢየሱስም፣ "የምትለምኑትን
አታውቁም፤ እኔ የምጠጣውን ጽዋ
ልትጠጡ፣ የምጠመቀውንስ ጥምቀት
ልትጠመቁ ትችላላችሁን?" አላቸው።
39እነርሱም፣ "አዎን እንችላለን"
አሉት።
ኢየሱስም፣ "እኔ የምጠጣውን ጽዋ
ትጠጣላችሁ፤እኔየምጠመቀውንምጥምቀት
ትጠ መቃላችሁ፤ 40ነገር ግን በቀኜ ወይም
በግ ራዬ መቀመጥ ለተዘጋጀላቸው የሚሆን
እንጂ እኔ የምሰጠው ነገር አይደለም"
አላቸው።
41ዐሥሩ ይህን ሲሰሙ፣ ያዕቆብንና
ዮሐንስን መቈጣት ጀመሩ። 42ኢየሱስም
በአንድነት ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፤
"የአሕዛብ አለቆች ተብለው የሚታሰቡት
እንደሚገዟቸው፤ ሹሞቻቸውም በእነርሱ
ላይ ሥልጣናቸውን እንደሚያሳዩ
ታውቃላችሁ፤ 43በእ ናንተ ዘንድ ግን

[a]*10፥24 አንዳንድ ቅጆች በሀብት ለሚታመኑ የሚል ሐረግ አላቸው::*

**10፥23 ለሀብታሞች፤** በገጽ 1577 ላይ፣ "*ብልጽግናና ድህነት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**10፥30 መቶ ዕጥፍ፤** ከዚህ ላይ ተስፋ የተገባው ሽልማት፣ በጥሬ ትርጒሙ መታየት የለበትም:: ይልቁንስ ከግንኙነቱ ጋር ትስስር ያላቸውና ከዚህ ላይ የተዘረዘሩት በረከቶችና የሐሤት ምንጮች ለክርስቶስ ሲል መሥዋዕት በሚሆን ደቀ መዝሙር ሕይወት ተመክሮዎች ይሆናሉ::

**10፥31 ፊተኞች የሆኑ ኋለኞች፤** ማቴ 19፥30 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**10፥43 ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ፤** እውነተኛው ታላቅነት፣ የመሪነት፣ የሥልጣን ወይም የግል ውጤታማነት ጉዳይ ሳይሆን (ቍ 42)፣

እንዲህ አይደለም፤ ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤ 44ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፣ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ 45የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣምና።"

## ኢየሱስ ዐይነ ስውሩን በርጤሜዎስን ፈወሰ

*10፥46-52 ተጓ ምብ — ማቴ 20፥29-34፤ ሉቃ 18፥35-43*

46ከዚህ በኋላ ወደ ኢያሪኮ መጡ። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከብዙ ሕዝብ ጋር ከኢያሪኮ ሲወጡ ዐይነ ስውሩ የጤሜዎስ ልጅ በርጤሜዎስ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለምን ነበር። 47እርሱም የናዝሬቱ ኢየሱስ መሆኑን በሰማ ጊዜ፣ "የዳዊት ልጅ፣ ኢየሱስ ሆይ፤ ማረኝ!" እያለ ይጮኽ ጀመር።

48ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ ግን፣ "የዳዊት ልጅ ሆይ፤ ማረኝ!" እያለ የባሰ ጮኸ።

49ኢየሱስም ቆም ብሎ፣ "ጥሩት" አላቸው።

እነርሱም ዐይነ ስውሩን፣ "አይዞህ፤ ተነሥ፤ ይጠራሃል!" አሉት። 50እርሱም ልብሱን ጥሎ ብድግ በማለት፣ ተነሥቶ ወደ ኢየሱስ መጣ።

51ኢየሱስም፣ "ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?" አለው።

ዐይነ ስውሩም፣ "መምህር ሆይ፤ እንዳይ እፈልጋለሁ" አለው።

ማር 11፥22-24

52ኢየሱስም፣ "ሂድ፣ እምነትህ አድኖሃል" አለው፤ ወዲያውም ዐይኑ በራለት፤ በመንገድም ኢየሱስን ተከትሎት ሄደ።

## ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም ገባ

*11፥1-10 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥1-9፤ ሉቃ 19፥29-38*
*11፥7-10 ተጓ ምብ — ዮሐ 12፥12-15*

**11** ወደ ኢየሩሳሌም በደብረ ዘይት ተራራ አጠገብ ወዳሉት ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረቡ ጊዜ፣ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ በማለት ላካቸው፤ 2"በፊታችሁ ወዳለው መንደር ሂዱ፣ ሰው ተቀምጦበት የማያውቅ የአህያ ውርንጫ እዚያ ታስሮ ታገኛላችሁ፤ ፈታችሁ አምጡት፤ 3ማንም፣ 'ምን ማድረጋችሁ ነው?' ቢላችሁ፣ 'ለጌታ ያስፈልገዋል፤ በቶሎም መልሶ ይልከዋል' ብላችሁ ንገሩት።"

4እነርሱም ሄዱ፤ በአንድ ቤት በራፍ አመንገድ ላይ የአህያ ውርንጫ ታስሮ አገኙት፤ ፈቱትም። 5በዚያ ከቆሙት አንዳንድ ሰዎች፣ "ውርንጫውን የምትፈቱት ለምንድን ነው?" አሏቸው። 6ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ ያላቸውን ለሰዎቹ በነገሯቸው ጊዜ ፈቀዱላቸው። 7ውርንጫውንም ወደ ኢየሱስ አምጥተው ልብሳቸውን በጀርባው ላይ አደረጉ፤ እርሱም ተቀመጠበት። 8ብዙ ሰዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፤ ሌሎች ደግሞ ለምለም የዛፍ ቅርንጫፍ እየቈረጡ ያነጥፉ ነበር። 9ከፊቱ የቀደሙትና ከኋላው የተከተሉትም በታላቅ ድምፅ፤ እንዲህ ይሉ ነበር፤

"ሆሣዕና![ш]

*በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው!*
*10የምትመጣው የአባታችን የዳዊት*
*መንግሥት የተባረከች ናት!*
*ሆሣዕና በአርያም!"።*

11ኢየሱስም ኢየሩሳሌም ደረሰ፤ ከዚያም ወደ ቤተ መቅደስ ገባ፤ በዙሪያው ያለውንም ሁሉ ተመለከተ፤ ቀኑም ስለመሸ ከዐሥራ ሁለቱ ጋር ወደ ቢታንያ ወጣ።

## ኢየሱስ ቤተ መቅደስን አጸዳ

*11፥12-14 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥18-22*
*11፥15-18 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥12-16፤ ሉቃ 19፥45-47፤ ዮሐ 2፥13-16*

12በማግሥቱ ከቢታንያ ሲወጡ ኢየሱስ ተራበ።

13እርሱም ቅጠል ያላት የበለስ ዛፍ ከሩቅ አየ፤ ምናልባት ፍሬ ይገኝባት እንደ ሆነ ብሎ ወደ እርሷ መጣ፤ ነገር ግን የበለስ ወራት አልነበረምና ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም። 14ከዚያም ዛፏን፣ "ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ማንም ፍሬ ከአንቺ አይብላ" አላት። ደቀ መዛሙርቱም ይህን ሲናገር ሰሙ።

10፥45 ማቴ20፥28
10፥47 ማቴ9፥27፤ ማር1፥24
10፥51 ማቴ23፥7
10፥52 ማቴ4፥19፤ 9፥22
11፥1 ማቴ21፥1፡17
11፥2 ዘኍ19፥2፤ ዘዳ21፥3፤ 1ሳሙ6፥7
11፥4 ማር14፥16
11፥9 መዝ118፥25፡26፤ ማቴ23፥39
11፥10 ሉቃ2፥14
11፥11 ማቴ21፥12፡17
11፥13 ሉቃ13፥6-9

ш11፥9 በዕብራይስጡ "አድን" ማለት ሲሆን ምስጋናን የሚገልጽ አባባል ነው፤ እንዲሁም ቍ 10 ይመ::

ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ሲል በቅንነት ለመኖር የሚሻ ልብ ሁኔታ ነው:: ክብርን፣ ማዕረግን ወይም የዚህን ዓለም ሽልማት ባለማሻት ራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ሰጥተን፣ በዚህ ምድር ላይ ከእርሱ ፈቃድ ጋር ልባችንን ማስማማት አለብን:: በእውነት ትልቅ የሆን ሰው ሽልማቶች የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም፣ ሌሎችን በክርስቶስ በኩል እውን ወደ ሆነው ድነት ማምጣትና እግዚአብሔርን ማስደሰት ናቸው (ሉቃ 22፥24-30 እና ስለ ታላቅነት የቀረበውን ማብ ይመ)::

**10፥45 ቤዛ፤** ማቴ 20፥28 ይመልከቱ፤ ሮሜ 3፥25፣ የክርስቶስ ሞት ለሰው ዘር ምን ትርጒም እንዳለው የሚያሳየውን ማብራሪያ በዚሁ ክፍል ላይ ይመልከቱ::

**11፥1 የሕማማት ሳምንት፤** በማርቆስ ወንጌል እዚህ ላይ፣ የሕማማት ሳምንት የሚጀምር ሲሆን (11-15)፣ ከዚህ ቀጥሎ የትንሣኤ ትረካ ይከተላል (ምዕ 16)::

**11፥9 የሚመጣ የተባረከ ነው፤** ሕዝቡ፣ እስራኤልን መሲሑ በመንግሥትነት ወደ ክብሯ በመመለስ በፖለቲካ ረገድ የሚያስተዳድራት መስሏቸው ነበር:: ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዐላማ በተመለከተ ያደረገውን ገለጻ መገንዘብ አቃታቸው:: ከጊዜ በኋላም እነርሱ የፈለጉት ዐይነት መሲሕ አለመሆኑን ሲገነዘቡ፣ "'ስቀለው' እያሉ ጮኹ" (15፥13)::

[15]ወደ ኢየሩሳሌምም መጡ፤ ከዚያም
ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ፣ የሚሸጡትንና
የሚገዙትን ያስወጣ ጀመር። የገንዘብ
መንዛሪዎ ችን ጠረጴዛና የርግብ ሻጮችን
መቀመጫ ገለባበጠ፤ [16]ማንም ዕቃ ተሸክሞ
በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳያልፍ
ከለከለ። [17]ሲያስተምራቸውም፣
"'ቤቴ ለሕዝቦች ሁሉ የጸሎት ቤት
ይባላል' ተብሎ አልተጻፈምን?
እናንተ ግን የሌቦች ዋሻ አደረጋችሁት!"
አላቸው።
[18]የካህናት አለቆችና ጸሐፍትም፣ ይህን
ሲሰሙ እንዴት እንደሚያጠፉት መንገድ
ይፈልጉ ጀመር፤ ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ
በመገረማቸው ፈርተውታልና።
[19]በመሸም ጊዜ ከከተማዪቱ ወጥተው
ሄዱ[ሀ]።

## የበለሷ ዛፍ ደረቀች

*11፥20-24 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥19-22*

[20]በማግስቱ ጠዋት በመንገድ ሲያልፉ፣
በለሲቱ ከነሥሯ ደርቃ አዩ። [21]ጴጥሮስ ነገሩ
ትዝ አለውና ኢየሱስን፣ "መምህር ሆይ፤
እነሆ፤ የረገምሃት በለስ ደርቃለች" አለው።
[22]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"በእግዚአብሔር እመኑ[ለ]፤ [23]እውነት
እላችኋለሁ፤ ማንም ይህን ተራራ፣ 'ተነቅለህ
ወደ ባሕር ተወርወር' ቢለውና ይህንንም
በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን ይሆንለታል።
[24]ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ
እንደ ተቀበላች ሁት አድርጋችሁ ብታምኑ
ይሆንላችኋል። [25]እንዲሁም ለጸሎት
በምትቆሙበት ጊዜ፣ የሰማዩ አባታችሁ
ኀጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ፣
እናንተም በሰው ላይ ያላችሁን ሁሉ ይቅር
በሉ። [26]ይቅር ባትሉ ግን የሰማዩ አባታችሁ
ኀጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም[ሐ]።"

11፥17 ኢሳ56፥7፣ ኤር7፥11
11፥18 ማቴ7፥28፤ 12፥12፤ 21፥46፤ ሉቃ20፥19
11፥19 ሉቃ21፥37
11፥21 ማቴ23፥7
11፥23 ማቴ21፥21
11፥24 ማቴ7፥7
11፥25 ማቴ6፥14

## በኢየሱስ ሥልጣን ላይ ጥያቄ ተነሣ

*11፥27-33 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥23-27፤ ሉቃ 20፥1-8*

[27]እንደ ገና ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፤
ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ
በሚዘዋወርበት ጊዜ፣ የካህናት አለቆች፣
ጸሐፍ ትና የሕዝብ ሽማግሌዎች ወደ እርሱ
ቀርበው፣ [28]"እነዚህን ነገሮች የምታደርገው
በምን ሥልጣን ነው? እነዚህን እንድታደርግስ
ይህን ሥልጣን የሰጠህ ማን ነው" አሉት።
[29]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"እስቲ እኔም አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤
መልሱልኝ፤ እኔም እነዚህን ነገሮች በምን
ሥልጣን እንደማደርግ እነግራችኋለሁ።
[30]የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረችን ወይስ
ከሰው? መልሱልኝ።"
[31]እነርሱም እርስ በርሳቸው እንዲህ
ተባባሉ፤ "'ከሰማይ ነው' ብንል፣ 'ታዲያ
ለምን አላመናችሁትም?' ይለናል፤
[32]'ታዲያ፣ ከሰው ነው' እንበልን?" ሕዝቡ
ሁሉ ዮሐንስ እውነተኛ ነቢይ መሆኑን
ያምኑ ስለ ነበር ፈሩ።
[33]ስለዚህ ለኢየሱስ "አናውቅም" ብለው
መለሱለት።
ኢየሱስም፣ "እንግዲያው እኔም እነዚህን
ነገሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ
አልነግራችሁም" አላቸው።

## የወይን ስፍራ የተከራዩ ገበሬዎች ምሳሌ

*12፥1-12 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥33-46፤ ሉቃ 20፥9-19*

**12** ከዚያም እንዲህ እያለ በምሳሌ
ይነግራቸው ጀመር፤ "አንድ
ሰው ወይን ተከለ፤ ዙሪያውን ዐጠረ፤

11፥32 ማቴ11፥9
12፥1 ኢሳ5፥1-7

*[ሀ]11፥19 አንዳንድ ቅጆች ወጥቶ ሄደ ይላሉ።*
*[ለ]11፥22 አንዳንድ የጥንት ቅጆች በእግዚአብሔር ላይ እምነት ካላችሁ ይላሉ።*
*[ሐ]11፥26 አንዳንድ ቅጆች ቍ 26 የላቸውም።*

**11፥15 ከዚያም ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ፤** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሰዎች ማስወጣቱ፣ እግዚአብሔርን እናመልካለን በሚሉት ወገኖች ሕይወት እውነተኛ የቅድስናና የጸሎት ሕይወት እንዲኖር ያለውን ቅናት ያሳያል (ኢሳ 56፥7 እና ማብ፤ ሉቃ 19፥45 እና ማብ ይመ)።

**11፥17 የጸሎት ቤት፤** ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቤት፣ «የጸሎት ቤት» መሆን እንዳለበት ግልጽ አደረገ፤ ይህም ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ መሰጠት፣ በጸሎትና በአምልኮ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ስፍራ ነው (ሉቃ 19፥45 እና ማብ ይመ)። ይህ የእግዚአብሔር ቤት ለማኅበራዊ ግንኙነት፣ ገንዘብ ለማግኘት፣ ለመዝናናት፣ ለታይታ ወይም ለማስታወቂያ ሲባል መርከስ የለበትም። የእግዚአብሔር ቤት ለሥጋቸው ላደሩ ሰዎች መገልገያ ወይም መጠቀሚያ በሆነ ቍጥር፣ «የሌቦች ዋሻ» ይሆናል።

**11፥24 እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ፤** እንደ ተቀበለ አድርጎ የሚቈጥር እምነት በሰው ብልኀት የሚገኝ ጒዳይ አይደለም፤ ይልቁንስ እግዚአብሔር በአማኙ ልብ ያስቀመጠው ልባዊ እምነት ነው እንጂ (9፥23 እና ማብ ይመ)። በእውነተኛ እምነት ልመና ያቀረበ ክርስቲያን እንዲፈጸምለት የሚመኘው ነገር አንዳንድ ጊዜ ወዲያውኑ ሊሰጠው ይችላል፤ አንዳንድ ጊዜ ግን እንዲህ ላይሆን ይችላል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ልመናው የተሰማ መሆኑን፣ የቀረበው ልመናም መልስ እንደሚያገኝ የሚቈጥርን እምነት ይሰጣል። ርግጠኛ ያለመሆኑ ጒዳይ የሚመለከተው፣ ልመናው መልስ የማግኘቱን ጥያቄ ሳይሆን፣ የቀረበው ጥያቄ መቼ እንደሚፈጸም የማወቁ ጒዳይ ነው።

**11፥25 ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ ... ይቅር በሉ፤** ክርስቲያኖች በማንም ላይ ጠላትነትን ወይም ጥላቻን በልባቸው ቋጥረው ከሆነ፣ የጸሎት መልስ ያስገኝ እምነት በእጃችን ነው ብለው አይታለሉ (ማቴ 18፥35 እና ማብ ይመ)።

**12፥1 የተከራዩ ገበሬዎች ምሳሌ፤** ይህ ሐረግ በዋናው ጽሑፍ ላይ ባይገኝም፣ አጠቃላይ ሐሳቡ እንደሚከተለው ነው፤ ምሳሌው የአይሁድ ሕዝብ በደል

ለመጭመቂያው ጕድጓድ ቈፈረ፤
የመጠበቂያም ማማ ሠራለት፤ ከዚያም
ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ።
2በመከር ጊዜም ከወይኑ ፍሬ እንዲያመጣለት
ከአገልጋዮቹ አንዱን ወደ ገበሬዎቹ
ላከ። 3እነርሱ ግን ይዘው ደበደቡት፤
ባዶ እጁንም ሰደዱት። 4እንደገናም ሌላ
አገልጋይ ላከ፤ እነርሱም ራሱን ፈንክተውና
አዋርደው መለሱት"፤ 5አሁንም እንደ
ገና ሌላ ላከ፤ ይህኛውንም ገደሉት፤
ከሌሎች ከብዙዎቹ መካከል አንዳንዶቹን
ደበደቡ፤ አንዳንዶቹንም ገደሉ።
6"አሁንም የሚላክ ሌላ ነበረው፤
እርሱም የሚወደው ልጁ ነበረ፤ "ልጄንስ
ያከብሩታል" በማለት ከሁሉ በኋላ ላከው።
7"ገበሬዎቹ ግን እርስ በርሳቸው፣ 'ይህማ
ዋናው ወራሽ ነው፤ ኑ እንግደለው፤ ርስቱ የእኛ
ይሆናል' ተባባሉ፤ 8ከዚያም ይዘው ገደሉት፤
ከወይኑ ስፍራም አውጥተው ጣሉት።
9"እንግዲህ የወይኑ አትክልት ባለቤት
ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል? ይመጣል፤
ገበሬዎቹን ይገድላል፤ የወይኑንም አትክልት
ለሌሎች ይሰጣል። 10እንዲህ የሚለውን
የመጽሐፍ ቃል አላነበባችሁምን፤
" 'ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
እርሱ የማእዘን ራስ[ሀ] ሆነ፤
11ጌታ ይህን አድርጎአል፣
ይህም ለዐይናችን ድንቅ ነው'?"
12ምሳሌውን የተናገረው ስለ እነርሱ
መሆኑን ስላወቁ፣ ሊይዙት ፈለጉ፤ ነገር ግን
ሕዝቡን ስለፈሩ ትተውት ሄዱ።

## ለቄሳር ግብር ስለ መክፈል

*12፥13-17 ተጓ ምብ - ማቴ 22፥15-22፤*
*ሉቃ 20፥20-26*

13ከዚያም በነገር እንዲያጠምዱት
ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ ወገን ሰዎች ወደ
እርሱ ላኩ። 14እነርሱም መጥተው እንዲህ
አሉት፤ "መምህር ሆይ፤ አንተ ትክክለኛ
ሰው መሆንህን እናውቃለን፤ የሰዎች ማንነት
ስለማይገድህም አታዳላም፤ የእግዚአብሔርን
መንገድ ብቻ በእውነት ታስተምራለህ፤
ለመሆኑ ለቄሳር ግብር መክፈል ይገባል
ወይስ አይገባም? 15እኛስ እንክፈል ወይስ
አንክፈል?"
ኢየሱስ ግን ግብዝነታቸውን ዐውቆ፣
"ለምን ልታጠምዱኝ ትፈልጋላችሁ? እስቲ
አንድ ዲናር አምጡልኝና ልየው" አላቸው።
16እነርሱም አመጡለት፣ "ይህ የማን መልክ
ነው? ጽሕፈቱስ የማን ነው?" አላቸው፤
እነርሱም፣ "የቄሳር ነው" አሉት።
17ኢየሱስም፣ "የቄሳርን ለቄሳር፣
የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ" አላቸው።
እነርሱም በእርሱ ተደነቁ።

## ጋብቻና ትንሣኤ

*12፥18-27 ተጓ ምብ - ማቴ 22፥23-33፤*
*ሉቃ 20፥27-38*

18ከዚህ በኋላ የሙታን ትንሣኤ የለም
የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ መጥተው
እንዲህ ሲሉ ጠየቁት፤ 19"መምህር ሆይ፤
የአንድ ሰው ወንድም ሚስት አግብቶ ልጅ
ሳይወልድ ቢሞት፣ ይህ ሰው ሴትየዋን
አግብቶ ለወንድሙ ዘር እንዲተካ ሙሴ
ጽፎልናል። 20ታዲያ ሰባት ወንድማማቾች
ነበሩ፤ የመጀመሪያው አግብቷት ዘር ሳይተካ
ሞተ፤ 21ሁለተኛውም ሴትየዋን አገባት፤
እርሱም ዘር ሳይተካ ሞተ፤ ሦስተኛውም
እንዲሁ፤ 22ሰባቱም አገቧት፤ ዘር ግን
አልተኩም፤ በመጨረሻም ሴትየዋ ሞተች።
23እንግዲህ፣ ሰባቱም አግብተዋታልና
በትንሣኤ[ለ] ለማናቸው ሚስት ልትሆን
ነው?" አሉት።
24ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"የምትስቱት እኮ ቅዱሳት መጻሕፍትንና
የእግዚአብሔርን ኀይል ስለማታውቁ ነው!
25ሙታን በሚነሡበት ጊዜ እንደ ሰማይ
መላእክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም፤
አይጋቡም። 26ስለ ሙታን መነሣት ግን፤
በሙሴ መጽሐፍ ይኸውም ስለ ቍጥቋጦው
በተነገረው ክፍል፣ እግዚአብሔር 'እኔ የአብርሃም
አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ
ነኝ' ያለውን አላነበባችሁምን? 27እግዚአብሔር
የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ
አይደለም፤ ስለዚህ እጅግ ተሳስታችኋል።"

## ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ

*12፥28-34 ተጓ ምብ - ማቴ 22፥34-40*

28ከጸሐፍትም አንዱ መጥቶ ሲከራከሩ
ሰማቸው፤ ኢየሱስ ለቀረበለት ጥያቄ
ተገቢውን መልስ መስጠቱን አስተውሎ፣
"ለመሆኑ ከትእዛዛት ሁሉ የሚበልጠው
የትኛው ነው?" ሲል ጠየቀው።
29ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
"ከሁሉ የሚበልጠው ይህ ነው፤ 'እስራኤል
ሆይ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤
30አንተም ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣
በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህና በፍጹም

12፥6 ዕብ1፥1-3
12፥10 ሐሥ4፥11
12፥11 መዝ118፥22፡23
12፥12 ማቴ22፥22፤ ማር11፥18
12፥13 ማቴ12፥10፤ 22፥16፤ ማር3፥6
12፥17 ሮሜ13፥7
12፥18 ሐሥ4፥1፤ 23፥8፤ 1ቆሮ15፥12
12፥19 ዘዳ25፥5
12፥24 2ጢሞ3፥15-17
12፥25 1ቆሮ15፥42፡49፡52
12፥26 ዘፀ3፥6
12፥28 ሉቃ10፥25-28፤ 20፥39
12፥30 ዘዳ6፥4፡5

[ሀ] 12፥10 ወይም *የማእዘን ድንጋይ*
[ለ] 12፥23 አንዳንድ ቅጆች *በትንሣኤ ሰዎች ከሙታን ሲነሡ* የሚል አላቸው

ምን እንደ ሆነ አጕልቶ ያሳያል፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት የግል ርስት አደረጉት፤ ቃሉን አቃለሉት፤ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስንም አንታዘዝም አሉ። ዛሬም ቢሆን አብያተ ክርስቲያናት የክርስቶስን ቃልና ሐቀኛ መልእክተኞችን አንቀበልም ብለው እንዳሻቸውና እንደ ሐሳባቸው ቤተ ክርስቲያን ሲቈረቁሩ በመታየታቸው የዚያን ክፉ ባለመሬት ባሕርይ ያንጸባርቃሉ።

**12፥10 የማእዘን ራስ ሆነ፤** ክርስቶስ በእስራኤል ዘንድ የተተወና የተናቀ ድንጋይ ሆነ፤ ሆኖም በዚያን ጊዜ ብዙ ሳይቈይ የአዲሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ማለትም የቤተ ክርስቲያን መደምደሚያ ወይም የማእዘን ድንጋይ ይሆናል (ሐሥ 4፥11-12፤ መዝ 118፥22 እና ማብ ይመ)። ጌታ ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር በመገንባት ላይ ያለው አዲስ መዋቅር (ሕንጻ) ዐቢይ ድንጋይ ነው።

**12፥30 ጌታ አምላክህን፤** ማቴ 22፥37 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

ኀይልህ ውደድ፡፡' 31ሁለተኛውም ይህ
ነው፤ 'ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ።'
ከእነዚህም የሚበልጥ ትእዛዝ የለም።"
32ጸሐፊውም እንዲህ አለው፤ "መምህር
ሆይ፤ መልካም ብለሃል፤ እርሱ አንድ
መሆኑን፣ ከእርሱም ሌላ አለመኖሩን
መናገርህ ትክክል ነው፤ 33እርሱን በፍጹም
ልብህ፣ በፍጹም አእምሮህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣
በፍጹም ኀይልህ መውደድ፣ እንዲሁም
ባልንጀራህን እንደ ራስህ መውደድ
ከሚቃጠል መሥዋዕት ሁሉና ከሌሎችም
መሥዋዕቶች ይበልጣል።"
34ኢየሱስም በማስተዋል እንደ መለሰለት
አይቶ፣ "አንተ ከእግዚአብሔር መንግሥት
የራቅህ አይደለህም" አለው። ከዚህ በኋላ
ሊጠይቀው የደፈረ ማንም አልነበረም።

## ክርስቶስ የማን ልጅ ነው?

*12፥35-37 ተጓ ምብ - ማቴ24፥41-46፤*
*ሉቃ 20፥41-44*
*12፥38-40 ተጓ ምብ - ማቴ23፥1-7፤*
*ሉቃ 20፥45-47*

35ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ አደባባይ
በሚያስተምርበት ጊዜ እንዲህ ሲል ጥያቄ
አቀረበ፤ "ጸሐፍት እንዴት ክርስቶስ
የዳዊት ልጅ ነው ይላሉ? 36ዳዊት በመንፈስ
ቅዱስ ሲናገር፣
"ጌታ ጌታዬን፣ 'ጠላቶችህን ከእግርህ
በታች እስካደርጋቸው ድረስ በቀኜ ተቀመጥ'
አለው።" ይላል፤
37ታዲያ ዳዊት ራሱ 'ጌታ' ካለው፣
እንዴት ተመልሶ ልጁ ይሆናል?"።
ብዙ ሕዝብም በደስታ ይሰማው ነበር።
38በሚያስተምርበትም ጊዜ እንዲህ አለ፤
"ከጸሐፍት ተጠንቀቁ፤ የተንዘረፈፈ ቀሚስ
ለብሰው መዞርን ይወዳሉ፤ በየአደባባዩም
የአክብሮት ሰላምታ ይሻሉ፤ 39በምኵራብ
ከፍተኛውን ወንበር፣ በግብዣም ቦታ
የከበሬታን ስፍራ ይፈልጋሉ፤ 40በረጅም
ጸሎታቸው እያሳበቡ የመበለቶችን

12፥31
ዘሌ19፥18፤
ማቴ5፥43
12፥32
ዘዳ4፥35፡39፤
ኢሳ45፥6፡14፤
46፥9
12፥33
1ሳሙ15፥22፤
ሆሴ6፥6፤
ሚክ6፥6-8፤
ዕብ10፥8
12፥34 ማቴ3፥2፤
22፥46፤
ሉቃ20፥24
12፥35
ማቴ9፥27፤
26፥55
12፥36
2ሳሙ23፥2፤
መዝ110፥1፤
ማቴ22፥44
12፥37 ዮሐ12፥9
12፥39
ሉቃ11፥43
12፥41 2ነገ12፥9፤
ዮሐ8፥20
12፥44 2ቆሮ8፥12
13፥2 ሉቃ19፥44
13፥3 ማቴ4፥21፤
21፥1
13፥5 ቍ 22፤
ኤር29፥8፤
ኤፌ5፥6፤
2ተሰ2፥3፡10-12፤
1ጢሞ4፥1፤
2ጢሞ3፥13፤
1ዮሐ4፥6

ቤት ያራቍታሉ፤እነዚህ የባሰ ፍርድ
ይቀበላሉ።"

## የመበለቲቱ ስጦታ

*12፥41-44 ተጓ ምብ — ሉቃ 21፥1-4*

41ኢየሱስ በገንዘብ ማስቀመጫው አንጻር
ተቀምጦ ብዙ ሰዎች ስጦታቸውን ወደ ቤተ
መቅደሱ ገንዘብ ማስቀመጫ ሣጥን ሲያስ
ገቡ ይመለከት ነበር። ብዙ ሀብታሞች ብዙ
ገንዘብ አስገቡ፤ 42አንዲት ምስኪን መበለት
ግን ከአንድ ሳንቲም የማይበልጡ ሁለት
የናስ ቤሳዎች አስገባች።
43ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ፣
እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፤
ይህቺ ድኻ መበለት ሣጥኑ ውስጥ ከጣሉት
ከሌሎቹ የበለጠ አስገባች። 44እነዚህ ሁሉ
ከተረፈው ሀብታቸው ሰጡ፤ እርሷ ግን
በድኽነት ዐቅሟ ያላትን ሁሉ አውጥታ
ለመኖሪያ የሚሆናትን እንዳለ ሰጠች።"

## የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች

*13፥1-37 ተጓ ምብ — ማቴ 24፥1-51፤*
*ሉቃ 21፥5-36*

13 ከቤተ መቅደስ ሲወጣ ከደቀ
መዛሙርቱ አንዱ፣ "መምህር ሆይ፤
ድንጋዮቹ እንዴት እንደ ሆኑ፣ ሕንጻውም
እንዴት ውብ እንደ ሆነ እይ" አለው።
2ኢየሱስም መልሶ፣ "እነዚህን ታላላቅ
ሕንጻዎች ታያለህ? አንዱ ድንጋይ
በሌላው ላይ እንደ ሆነ አይቀርም፤ ሁሉም
ፈራሽ ነው" አለው።
3ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ትይዩ፣ በደብረ
ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ሳለ ጴጥሮስ፣
ያዕቆብ፣ ዮሐንስና እንድርያስ እንዲህ ሲሉ
ጠየቁት፤ 4"ይህ መቼ እንደሚሆን ንገረን፤
የዚህስ ሁሉ ፍጻሜ ምልክቱ ምንድን ነው?"
5ኢየሱስም እንዲህ ይላቸው ጀመር፤
"ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤

---

**12፥31 ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፤** ማቴ 22፥39 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::
**12፥38-39 ... ይወዳሉ ... ከፍተኛውን ወንበር፤** ጌታ ኢየሱስ ከሰዎች ዝናንና ከበሬታን ከሚሹ የሃይማኖት መሪዎች ይጠበቁ ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን ያስጠነቅቃል:: እንደነዚህ ያሉትን መሪዎች ፈሪሳውያን ይላቸዋል (ማቴ 23፥13-15:23:25:29)፤ ዘወትር በሚያሳዩት የታይታ ጽድቅ ረገድም፣ “አጭበርባሪዎችና አታላዮች ናቸው” ይላቸዋል (ማቴ 23፥25-28 ጋር ያነጻጽሩ):: እንደነዚህ ያሉ ሰዎች በልብ ውስጥ የሚያድረው መንፈስ ቅዱስና ዳግም ልደትን የሚያስገኝ ጸጋው የሏቸውም (ከሮሜ 8፥5-14 ጋር ያነጻጽሩ):: እነዚህ ሰዎች በዚህ ሁኔታ እስካሉ ድረስ፣ ከገሃነም ፍርድ ሊያመልጡ አይችሉም (ማቴ 23፥33፤ ማቴ 23፥13 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1519 ላይ፣ “*የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::
**12፥40 የመበለቶችን ቤት ያራቍታሉ፤** አንዳንድ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች የማይጠረጥሩትንና ብቸኛ የሆኑትን መበለቶች መጠቀሚያ አድርገዋቸው ነበር:: ከእነዚሁ ልክ የለሽ ስጦታን ለመቀበል ይፈልጋሉ፤ ይቀበላሉም:: ይህን የሚያደርጉትም መበለቶቹ የእግዚአብሔርን ሰው ለመርዳት ያላቸውን ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ነው:: መሪዎቹ በማታለልና በማጭበርበር መበለቶቹን ከዐቅማቸው በላይ እንዲከፍሉ ያስገድዳሉ፤ ግራ በተጋቡ በእነዚህ መበለቶች ሀብትም ተንደላቀው ይኖራሉ:: ይህ ዐይነቱ አሠራር በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ እንዳለ አለ፤ እያንዳንዱ ዘመን በግል ባሕርዩ የሚታወቅበት፣ እጅን ጠምዝዞ ገንዘብን የሚዘርፍ ሃይማኖተኛ የሆነ ነጣቂ አለው::
**12፥42 ምስኪን መበለት፤** እግዚአብሔር ብቸኛ የሆኑትን፣ የተናቁትን ወይም መበለት የሆኑትን ሴቶች፣ ምን ያህል እንደሚንከባከብ ለመገንዘብ ሉቃ 7፥13 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::
**12፥42 ሁለት የናስ ቤሳዎች፤** እግዚአብሔር ስጦታን የሚመዝነው በስጦታው ብዛት ሳይሆን፣ በስጦታው አማካይነት በተገለጠው ፍቅር፣ ዐልፎ መስጠትና መሥዋዕት ልክ ነው (ሉቃ 21፥1-4 እና ማብ ይመ)::
**13፥5 ተጠንቀቁ፤** የጌታ ኢየሱስ የደብረ ዘይት ንግግር፣

6ብዙዎች፣ 'እኔ እርሱ ነኝ' እያሉ በስሜ
ይመጣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። 7ስለ
ጦርነትና ስለ ጦርነት ወሬ በምትሰሙበት
ጊዜ አትደንግጡ፤ ይህማ መሆን አለበት፤
ፍጻሜው ግን ገና ነው። 8ሕዝብ በሕዝብ
ላይ፣ መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣል፤
በብዙ ቦታም የመሬት መንቀጥቀጥና ራብ
ይሆናል፤ እነዚህ ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ
ናቸው።

9"ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ለአካባቢ
ሸንጎ አሳልፈው ይሰጧችኋል፤ በምኵራብ
ይገርፏችኋል፤ ምስክር ትሆኑም ዘንድ
በእኔ ምክንያት በገዦችና በነገሥታት
ፊት ትቆማላችሁ። 10አስቀድሞ ግን
ወንጌል ለሕዝብ ሁሉ መሰበክ አለበት።
11ተይዛችሁ ለፍርድ በምትቀርቡበት ጊዜ፣
በዚያች ሰዓት የሚሰጣችሁን ተናገሩ እንጂ
ምን እንናገራለን በማለት አስቀድማችሁ
አትጨነቁ፤ የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ
እንጂ እናንተ አይደላችሁምና።

12"ወንድም ወንድሙን፣ አባትም ልጁን
ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፤ ልጆች በወላጆቻቸው
ላይ ያምፃሉ፤ ይገድሏቸዋልም። 13በእኔ
ምክንያት በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ
ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻው የሚጸና ግን
ይድናል።

14" 'የጥፋት ርኵሰት' ስፍራው ባልሆነ
ቦታ ቆሞ በምታዩት ጊዜ አንባቢው
ያስተውል፤ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች
ይሽሹ፤ 15በቤቱ ጣራ ላይ ያለ አይውረድ፤
ንብረቱንም ለማውጣት ወደ ቤቱ አይግባ፤
16በእርሻ ቦታ ያለ ልብሱን ለመውሰድ
አይመለስ። 17በእነዚያ ቀናት ለነፍሰ
ጡሮችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው! 18ይህም
በክረምት እንዳይሆን ጸልዩ፤ 19በመጀመሪያ
እግዚአብሔር ፍጥረትን ከፈጠረበት ጊዜ
አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ፣ እንዲሁ
ደግሞም ወደ ፊት አቻ የሌለው ታላቅ መከራ
ይሆናልና። 20ጌታ ቀኖቹን ባያሳጥራቸው
ኖሮ ማንም ባልዳነ ነበር፤ ስለ መረጣቸው
ስለ ምርጦቹ ሲል ግን ቀኖቹን አሳጥሮአል።
21በዚያን ጊዜ ማንም፣ 'እነሆ፤ ክርስቶስ[a]
እዚህ ነው?' ቢላችሁ ወይም፣ 'እነሆ፤
እዚያ ነው' ቢላችሁ አትመኑ። 22ሐሰተኛ
ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ተነሥተው፤
ምልክቶችንና ድንቆችን በማድረግ፣
ቢቻላቸው የተመረጡትን እንኳ ያስታሉ።
23ስለዚህ ተጠንቀቁ፤ ጊዜው ሳይደርስ ሁሉን
ነግሬአችኋለሁ።

24"በዚያን ጊዜ፣ ከመከራው በኋላ 'ፀሓይ
ትጨልማለች፣
ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም፤
25ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤
የሰማይ ኀይላትም ይናወጣሉ።'

26"በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በታላቅ
ኀይልና ግርማ በደመና ሲመጣ ያዩታል።

[a]13፥21 ወይም መሲሑ

13፥9 ማቴ10፥17
13፥11
ማቴ10፥19፡20፤
ሉቃ12፥11፡12
13፥12 ሚክ7፥6፤
ማቴ10፥21፤
ሉቃ12፥51-53
13፥13
ማቴ10፥22፤
ዮሐ15፥21
13፥14 ዳን9፥27፤
11፥31፤ 12፥11
13፥17
ሉቃ23፥29
13፥19 ማር10፥6፤
ዳን9፥26፤ 12፥1፤
ኢዩ2፥2
13፥21
ሉቃ17፥23፤
21፥8
13፥22
ማቴ7፥15፤
ዮሐ4፥48፤
2ተሰ2፥9፡10
13፥23 2ጴጥ3፥17
13፥25
ኢሳ13፥10፤
34፥4፤
ማቴ24፥29
13፥26 ራእ1፥7

ሕዝቡ የመጨረሻው ቀን እየተቃረበ ሲመጣ ከሃይማኖታዊ ማታለያ ይድኑ ዘንድ ዘወትር ነቅተው መጠበቅ እንዳለባቸው ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያን ይዞ ይገኛል:: ጌታ ኢየሱስ እንዲህ በማለት በብርቱ ያሳስባል፡ “ተጠንቀቁ፡” (ቍ 5)፣ “ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡” (ቍ 9)፣ “ስለዚህ ተጠንቀቁ፡” (ቍ 23)፣ “ተጠንቀቁ፡ ትጉ፡” (ቍ 33)፣ “እንግዲህ ... ተግታችሁ ጠብቁ” (ቍ 35)፤ “ተግታችሁ ጠብቁ” (ቍ 37):: እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች አያሌ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሠርገው እንደ ገቡ ያሳያሉ፤ አማኙ የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ማወቅና መታዘዝ አለበት (ማቴ 24፥5 እና ማብ ይመ)::

**13፥6 ብዙዎች፣ ... ብዙዎችንም ያስታሉ፤** ማቴ 24፥11 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**13፥10 ወንጌል ለሕዝብ ሁሉ መሰበክ፤** ማቴ 24፥14 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**13፥13 እስከ መጨረሻው የሚጸና፤** ለመጨረሻው ወይም መደምደሚያ ለሆነው ድነት በእምነት መጽናትና በዘላቂነት ለክርስቶስ ያለን ታማኝነት ተፈላጊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሁኔታዎች ናቸው (ከዕብ 3፥14፤ 6፥11-12፤ 10፥36 ጋር ያነጻጽሩ):: የመጨረሻው ድነት ምን እንደ ሆነ በራእይ 2፥7፡17፡26-28፤ 3፥5፡12፡20-21፤ 7፥9-17፤ 14፥13፤ 21፥1-7 ላይ ተገልጾአል::

**13፥14 የጥፋት ርኵሰት፤** የጥፋት ርኵሰት የሚያመለክተው ቅዱስ የሆነውን የሚበክለውን ወይም የሚያበላሸውን ነው (ዳን 9፥25-27 ይመ)፤ (1) የክርስቶስ ንግግር ኢየሩሳሌም በወደመች ጊዜ (70 ዓ.ም.)፣ የሮማውያንን ወረራ በትንቢት ሊያመለክት ይችላል፤ እንዲሁም ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ትንሽ ቀደም ብሎ የሐሰተኛው ክርስቶስ ምስል በኢየሩሳሌም እንደሚቀመጥ የሚያመለክት ትንቢትም ሊሆን ይችላል (2ተሰ 2፥2-3፤ ራእ 13፥14-15፤ 19፥11-21 ይመ)::

(2)ይህም አንዳንድ ጊዜ፣ “ነቢያዊ የሆነ በጥላነት አመልካች” ይባላል፡ ይህ አባባል ጥቅም ላይ የሚውለው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮች እንደ አንድ ተቈጥረው ሲታዩ ነው:: የዚህንም ምሳሌ በኢሳ 11፥1-4፤ 61፥1-2፤ ዘካ 9፥9-10 ላይ ወንጌልን ለመስበክ የክርስቶስን የመጀመሪያ አመጣጥ ከዳግም ምጽአቱ ጋር አጣምሮ ማየት ነው:: ዳግመኛ የሚመጣውም በዓለም ላይ ለመፍረድ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል (በእነዚህ ምንባቦች ላይ የቀረቡትን ማብ ይመ፤ ማቴ 24፥44 እና ማብ ይመ):: በተመሳሳይ መንገድ ጰንጠቆስጤያዊ የመንፈስ ቅዱስ መውረድና፣ “የእግዚአብሔር ታላቅና አስፈሪ ቀን” በኢዩኤል 2፥28-31 ላይ በአንድ ላይ ተጣምረው እንደ አንድ ሁኔታ ተቈጥረው ተነግረዋል:: ከዚህ ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የኢየሩሳሌምን መውደም በዘመኑ መጨረሻ የሚከሠተው የታላቁ መከራ አምሳል አድርጎ ገልጾታል (በገጽ 1471 ላይ፣ *“ታላቁ መከራ”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

**13፥19-22 ታላቅ መከራ፤** በእነዚህ ጥቅሶች ላይ የተሰጠውን ትንታኔ ለመረዳት፣ በገጽ 1471 ላይ፣ *“ታላቁ መከራ”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**13፥22 ሐሰተኛ ነቢያት፤** በገጽ 1519 ላይ፣ *“የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**13፥24 ፀሓይ ትጨልማለች፤** ማቴ 24፥29 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**13፥26 የሰው ልጅ ... ሲመጣ፤** ማቴ 24፥30 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

# የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች

*ማር 13፥22 "ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ተነሥተው፣ ምልክቶችንና ድንቆችን በማድረግ፣ ቢቻላቸው የተመረጡትን እንኳ ያስታሉ።"*

ገለጻ፤ አማኞች በኢየሱስ ዘመን እንደ ነበሩት ያሉ፣ ተመሳሳይ መንፈስና ሕይወት ያላቸው ብልሹ የሆኑ የእግዚአብሔር ሕግ መምህራን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዛሬም ሊኖሩ እንደሚችሉ መገንዘብ አለባቸው (ማቴ 24፥11:24)። በክርስቶስ አምናለሁ የሚል ሁሉ ወይም ክርስቲያን ጸሐፊዎች፣ ሚስዮናውያን፣ መጋቢዎች፣ ወንጌላውያን፣ ዲያቆናትና ሠራተኞች ሁሉ፣ "ነን" እንደሚሉት ላይሆኑ እንደሚችሉ ጌታ ኢየሱስ ያስጠነቅቃል።

(1) እነዚህ አገልጋዮች፣ "በውጭ ለሰዎች ጻድቃን ይመስላሉ" (ማቴ 23፥28)፤ "የበግ ለምድ ለብሰው" ይመጣሉ (ማቴ 7፥15)፤ መልእክታቸውን ሙሉ በሙሉና በተጠናከረ ሁኔታ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሊመሠርቱ ይችላሉ፤ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝን ጽድቅም ሊያውጁ ይችላሉ። ለእግዚአብሔር ሥራና መንግሥት ከልባቸው የሚጨነቁ፣ ለሕዝብ ሁሉ ፍቅርን እየገለጹም የጠፉት ድነትን ያገኙ ዘንድ የሚያስቡ ሊመስሉ ይችላሉ። በመንፈስ ቅዱስ የተቀቡ፣ የሚደነቁ መንፈሳዊ መሪዎችና ታላቅ የእግዚአብሔር አገልጋዮችም መስለው ሊታዩ ይችላሉ። ታምራት ሊሠሩ፣ ታላቅ ስኬታማነት ሊኖራቸው፣ ብዙኃኑም ሊከተሏቸው ይችላሉ (ማቴ 7፥21-23 እና ማብ፤ 24፥11:24፤ 2ቆሮ 11፥13-15 ይመ)።

(2) ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች መንፈሳውያን ቀደምት አባቶቻቸውን ከብሉይ ኪዳን ሐሰተኛ ነቢያትና (ዘዳ 13፥3 እና ማብ፤ 1ነገ 18፥40 እና ማብ፤ ነህ 6፥12 እና ማብ፤ ኤር 14፥14 እና ማብ፤ ሆሴ 4፥15 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1009 ላይ፣ "ነቢይ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ከአዲስ ኪዳን ፈሪሳውያን ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ። ፈሪሳውያን ከብዙኀኑ ሕዝብ ተለይተው ሲታዩና የጓዳ ማንነታቸው ሲመረመር፣ "ቅሚያና ስስት" የሚታይባቸው (ማቴ 23፥25) "በሙታን ዐፅምና በብዙ ርኵሰት የተሞላ" ሕይወት ያላቸው (23፥27)፣ "በግብዝነትና በክፋት" የተሞሉ ናቸው (23፥28)። የጓዳ ሕይወታቸው በፍትወተ ሥጋ፣ በኢግብረገባዊነት፣ በምንዝር፣ በሥሥትና በራስ ወዳድነት ስሜት የተሞላ ነው።

(3) እነዚህ አስመሳዮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጽዕና የሚያሳድሩበት ስፍራ የሚያገኙት በሁለት መንገድ ነው፤ (ሀ) አንዳንድ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ወይም ሰባኪዎች አገልግሎታቸውን የሚጀምሩት በቅንነት፣ በእውነት፣ በንጽሕናና ከልብ በሆነ እምነት ክርስቶስን በመከተል ነው። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን ከትዕቢታቸውና ከኢግብረገባዊ ፍላጎታቸው የተነሣ የግል ዐልፎ መስጠታቸውና ለክርስቶስ ያላቸው ፍቅር ቀስ በቀስ ይሞታል። የዚህ ውጤትም እነርሱ ከእግዚአብሔር መንግሥት መወገዳቸው ነው (1ቆሮ 6፥9-10፤ ገላ 5፥19-21፤ ኤፌ 5፥5-6)፤ በጽድቅ አገልጋይነት ሽፋን ራሳቸውን በመደበቅም የሰይጣን መሣሪያዎች ይሆናሉ (2ቆሮ 11፥15 ይመ)። (ለ) ሌሎች የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ወይም ሰባኪዎች ደግሞ ከልብ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሆነው አያውቁም፤ በችሎታቸውና በማራኪነታቸው በመጠቀም፣ ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ ዕገዛ በማድረግ ሰይጣን ከአገልግሎታቸው ጅማሬ አንሥቶ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተክሎአቸዋል (ማቴ 13፥24-28:36-43)። የእርሱ ስልት እንደነዚህ ያሉትን ትክለኞች ወሳኝ በሆነ ቦታ ላይ ማስቀመጥ ነው፤ ሰይጣን እንደዚህ የሚያደርገው እውነት የሆነውን የጌታ ኢየሱስን ሥራ በዐጭሩ ያስቀሩ ዘንድ ነው። የእነዚህ ትክለኛ ሰዎች ትክክለኛ ማንነት ውሎ ዐድሮ ከታወቀና ከተጋለጠ፣ በወንጌል ሥርጭት ላይ ታላቅ ዕንቅፋት እንደሚፈጠር፣ የጌታ ኢየሱስ ስምም በአደባባይ መሣቂያ መሣለቂያ እንደሚሆን ሰይጣን ያውቃል።

መፈተን፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚያስቱ መሪዎች ደቀ መዛሙርቱ ብርቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በወንጌሎቹ ዐሥራ አራት ጊዜ አሳስቦአቸዋል (ማቴ 7፥15፤ 16፥6:11፤ 24፥4:24፤ ማር 4፥24፤ 8፥15፤ 12፥38-40፤ 13፥5፤ ሉቃ 12፥1፤ 17፥23፤ 20፥46፤ 21፥8)። በሌላ ክፍልም አማኞች በቤተ ክርስቲያን ያሉትን መምህራን፣ ሰባኪዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲመዝኑ ምክር ተሰጥቶአቸዋል (1ተሰ 5፥21፤ 1ዮሐ 4፥1)። የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ወይም ሰባኪዎች ምን ዐይነት ሰዎች እንደ ሆኑ ለመመዘን የሚከተሉትን መመዘኛዎች ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል፦

(1) ጠባይን መለየት፤ ትጋት ያለበት የጸሎት ሕይወት አላቸውን? ቅንነት ያለውና ንጹሕ

የሆነ መስጠት ለእግዚአብሔር አላቸውን? የመንፈስ ፍሬ ይታይባቸዋልን (ገላ 5፥22-23)? ኀጢአተኞችን ይወዳሉን (ዮሐ 3፥16)? ክፋትን ጠልተው ጽድቅን ይወዳሉን (ዕብ 1፥9 እና ማብ)? ኀጢአትንስ በመቃወም ይጮኻሉን (ማቴ 23፤ ሉቃ 3፥18-20)?

(2) አነሣሽ ምክንያትን መለየት፤ እውነተኛ ክርስቲያን መሪዎች አራት ነገሮችን ለማድረግ ይነሣሣሉ፤ (ሀ) ክርስቶስን ያከብራሉ (2ቆሮ 8፥23፤ ፊል 1፥20)፤ (ለ) ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቅድስና ይመራሉ (ሐሥ 26፥18፤ 1ቆሮ 6፥18፤ 2ቆሮ 6፥16-18)፤ (ሐ) የጠፉትን ያድናሉ (1ቆሮ 9፥19-22)፤ (መ) የክርስቶስንና የሐዋርያትን ወንጌል ያውጃሉ፣ ጥብቅናም ይቆሙለታል (ፊል 1፥16 እና ማብ፤ ይሁ 1፥3 እና ማብ ይመ)።

(3) የመንፈስ ፍሬንና መልእክትን በሕይወት መፈተን፤ የሐሰተኛ ትምህርት ሰባኪዎች ፍሬያማነት፣ ለእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን አሳልፈው ካልሰጡት አዲስ ምእመናን ሕይወት አኳያ ይመዘናል (ማቴ 7፥16 እና ማብ ይመ)።

(4) በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ያላቸው ተደጋፊነት የቱን ያህል ሥር እንደ ሰደደ ለይቶ ማወቅ፤ እንግዲህ ዋናው ጉዳይ ይህ ነው፤ የመጀመሪያው የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቃል ሙሉ በሙሉ እስትንፋስ እግዚአብሔር እንዳለበትና እኛም በውስጡ ላዘለው ትምህርት መገዛት እንደሚገባን ያምናሉን? (2ዮሐ 1፥9-11 ይመ፤ በገጽ 1941 ላይ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። የማያምኑ ከሆነ ግን እነርሱም ሆኑ መልእክታቸው ከእግዚአብሔር እንዳልሆኑ ርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

(5) በመጨረሻም የጌታን ገንዘብ በታማኝነት እንደምን አድርገው እንደሚይዙት መፈተን፤ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ብዙ ገንዘብ መውሰድን እምቢ ይላሉን? ማንኛውንም ገንዘብ በታማኝነትና በሙሉ ኀላፊነት ይይዛሉን? የእግዚአብሔርንስ ሥራ ለመሪዎች በአዲስ ኪዳን ላይ በተደነገገው መስፈርት መሠረት ያከናውናሉን (1ጢሞ 3፥3፤ 6፥9-10)?

ታማኝ የሆኑ ክርስቲያኖች የአንድን ሰው ሕይወትና መልእክት ለመመዘን የቱን ያህል ቢጥሩም፣ እነዚህ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በሰይጣን ረዳትነት ማንነታቸው ሳይደረስበት፣ እግዚአብሔር እነርሱን ለማጋለጥ እስከወሰነበት ዕለት ድረስ ሳይታወቅባቸው በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሊኖሩ እንደሚችሉ መታወቅ አለበት።

27እርሱም መላእክቱን ልኮ ከአራቱ ነፋሳት፣
ከም ድር ዳርቻ እስከ ሰማያት ዳርቻ
ምርጦቹን ይሰበስባል።
28"ምሳሌውን ከበለስ ተማሩ፤ ቅርንጫፏ
ሲለመልም፣ ቅጠሏ ሲያቈጠቍጥ በጋ እንደ
ተቃረበ ታውቃላችሁ፤ 29እንዲሁ ደግሞ
እነዚህ ነገሮች መፈጸማቸውን ስታዩ እንደ
ቀረበ፣ በደጅም እንደ ሆነ ዕወቁ። 30እውነት
እላችኋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች እስከሚፈጸሙ
ድረስ ይህ ትውልድ[ሀ] አያልፍም፤ 31ሰማይና
ምድር ያልፋሉ፣ ቃሊ ግን አያልፍም።

## ቀኑና ሰዓቱ አይታወቅም

32"ነገር ግን ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያ
ችም ሰዓት ከአብ በቀር፣ የሰማይ መላእክ
ትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን፣ ማንም አያው
ቅም። 33ስለዚህ ጊዜው መቼ እንደሚሆን
አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፣ ጸልዩም[ለ]።
34ይህም ቤቱን ለአገልጋዮቹ ትቶ፣
እያንዳንዱን አገልጋይ በየሥራ ድርሻው ላይ
አሰማርቶ፣ በረኛው ነቅቶ እንዲጠብቅ አዝዞ
የሄደውን ሰው ይመስላል። 35እንግዲህ የቤቱ
ባለቤት በምሽት ወይም በውድቅት፣ በዶሮ
ጩኸት ወይም ጎሕ ሲቀድ እንደሚመጣ
አታውቁምና ተግታችሁ ጠብቁ፤ 36ድንገት
ሲመጣ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ፤
37ለእናንተ የምነግራችሁን ለሰው ሁሉ
እናገራለሁ፤ ተግታችሁ ጠብቁ!"

13፥27 ዘካ2፥6
13፥30 ማር9፥1፤ ሉቃ17፥25
13፥31 ማቴ 5፥18
13፥32 ሐሥ1፥7፤ 1ተሰ5፥1፡2
13፥33 1ተሰ5፥6
13፥34 ማቴ25፥14
13፥37 ሉቃ12፥35-40
14፥1 ማቴ12፥14፤ ዮሐ11፥55
14፥3 ማቴ21፥17፤ ሉቃ7፥37-39
14፥7 ዘዳ15፥11
14፥8 ዮሐ19፥40
14፥9 ማቴ24፥14፤ ማር16፥15

## ኢየሱስን ሽቶ የቀባችው ሴት

*14፥1-11 ተጓ ምባ — ማቴ 26፥2-16*
*14፥1፡2፡10፡11 ተጓ ምባ — ሉቃ 22፥1-6*
*14፥3-8 ማመ — ዮሐ 12፥1-8*

14 ፋሲካና የቂጣ በዓል ሊከበር ሁለት ቀን
ሲቀረው፣ የካህናት አለቆችና ጸሐፍት
ኢየሱስን የሚይዙበትና የሚገድሉበትን
ዘዴ ይፈልጉ ነበር። 2ሆኖም፣ "ሕዝቡ ዐመፅ
እንዳያነሣ በበዓሉ ሰሞን መሆን የለበትም"
ይባባሉ ነበር።
3እርሱም በቢታንያ በለምጻሙ ስምዖን
ቤት በማእድ ተቀምጦ ሳለ፣ አንዲት ሴት
ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ ንጹሕ የናርዶስ
ሽቱ የተሞላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ
ይዛ መጣች፣ ቢልቃጡንም ሰብራ ሽቱውን
በራሱ ላይ አርከፈከፈችው።
4በዚያ ከነበሩት አንዳንዶቹ በድርጊቱ
ተቈጥተው እንዲህ ይባባሉ ነበር፤ "ሽቱው
ለምን በከንቱ ይባክናል? 5ከሦስት መቶ ዲናር
በላይ ተሽጦ፣ ገንዘቡን ለድኾች መስጠት
ይቻል ነበር።" ሴትየዋንም ነቀፏት።
6ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፤
"ተዉአት፣ ለምን ታስቸግሯታላችሁ?
መልካም ነገር አድርጋልኛለች። 7ድኾች ምን
ጊዜም ከእናንተ ጋር ናቸው፤ በፈለጋችሁ
ጊዜ ልትረዷቸው ትችላላችሁ፤ እኔ ግን
ሁልጊዜ ከእና ንተ ጋር አልኖርም፤ 8እርሷ
ማድረግ የምት ችለውን ያህል አድርጋለች፤
ለመቃብሬ እን ዲሆን ሰውነቴን አስቀድማ
ቀብታለች። 9እውነት እላችኋለሁ፤

*[ሀ]13፥30 ወይም ዘር*
*[ለ]13፥33 ጸልዩ የሚለው ቃል በአንዳንድ ቅጆች አይገኝም።*

13፥27 **ምርጦቹን**፤ ማቴ 24፥31 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
13፥28 **ከበለስ**፤ ማቴ 24፥32 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
13፥29 **እነዚህ ነገሮች ... ስታዩ**፤ ማቴ 24፥33 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
13፥30 **ይህ ትውልድ**፤ ማቴ 24፥34 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
13፥32 **ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያችም ሰዓት ... ማንም አያውቅም**፤ ማቴ 24፥36 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
13፥33 **ተጠንቀቁ**፤ ማቴ 24፥42 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
13፥35 **በምሽት ... በውድቅት ... ጎሕ ሲቀድ**፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ ለሆኑት፣ ማለትም ለአብያተ ክርስቲያናት ታማኞች፣ የእርሱ መመለሻ ወቅት መሆን ከሚችሉት ዐራት ሰዓታት በአንዱ በሌሊት ወይም በማለዳ ንጋት ላይ ሊሆን እንደሚችል አረጋገጠ። ይህም ለእነርሱ ሲል መምጣቱ በማንኛውም ጊዜ ሊሆን እንደሚችልና እንደዚሁም ታማኝ የሆኑት ከምድር የሚነጠቁበትን (ይኸውም ነመነጠቅ ማለት ነው፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "ንጥቀት" የሚለውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) የዳግም ምጽአቱ የመጀመሪያው ደረጃ ያልተጠበቀ የተሰወረ መሆኑን በአጽንዖት ይገልጻል፤ ይህም የማይቀርና ያልተጠበቀ በመሆኑ፣ አማኞች ሁሉ በመንፈሳዊ ረገድ ንቁና ታማኞች መሆን አለባቸው (ማቴ 24፥42 እና ማብ፡ 24፥44 እና ማብ ይመ፤ ከሉቃ 12፥35-36፡38-40፡46፤ 21፥34-36 ጋር ያነጻጽሩ)።
14፥9 **ወንጌል**፤ ወንጌል (በግሪክ፣ 'ኢቫንጀሊዮን')፣ የምሥራች ማለት ሲሆን፣ እግዚአብሔር በሞት (በጥፋት) አፋፍ ላይ የሚገኘውን የሰውን ዘር ለማዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ሥግው መሆን፣ ሞትና ትንሣኤ በኩል ያከናወነው ተግባር የምሥራች ቃል ነው (ሉቃ 4፥18-21፤ 7፥22፤ ዮሐ 3፥16)። ይህ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በሚታወጅበት ቦታ ሁሉ የሚከተሉትን ተግባራዊ ያደርጋል (1ቆሮ 2፥4፣ ገላ 1፥11)፡ (1) በኀይል ይመጣል (ማቴ 28፥18-20)፤ (2) የእግዚአብሔርን ጽድቅ ያሳያል (ሮሜ 1፥16-17)፤ (3) ሰዎች ንስሓ ይገቡ ዘንድ ያስገድዳል (1፥15፤ ማቴ 3፥2፤ 4፥17)፤ (4) ስለ ኀጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል (ዮሐ 16፥8 ይመ፤ ከሐሥ 24፥25 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (5) እምነት እንዲኖር ያደርጋል (ሮሜ 10፥17፤ ፊል 1፥27)፤ (6) ድነትን፣ ሕይወትንና የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እውን ያደርጋል (ሐሥ 2፥33፡38-39፤ ሮሜ 1፥16፤ 1ቆሮ 15፥22፤ 1ጴጥ 1፥23)፤ (7) ከኀጢአትና ከሰይጣን ኀይል ይታደጋል (ማቴ 12፥28፤ ሐሥ 26፥18፤ ሮሜ 6)፤ (8) ተስፋን (ቈላ 1፥5፡23)፣ ሰላምንና (ኤፌ 2፥17፤ 6፥15) ኢመዋቲነትን እውን ያደርጋል (2ጢሞ 1፥10)፤ (9) ስለ ፍርድ ያስጠነቅቃል (ሮሜ 2፥16)፤ (10) አንቀበልህም በተባለ ጊዜ ፍርድንና

ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በሚሰበክበት
በማንኛውም ስፍራ እርሷ ያደረገችው
መታሰቢያ ሆኖ ይነገርላታል።"
10ከዚህ በኋላ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የሆ
ነው የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ ሊሰጠው
ወደ ካህናት አለቆች ሄደ። 11እነርሱም ይህን
ሲሰሙ ደስ አላቸው፤ ገንዘብ ሊሰጡትም
ቃል ገቡለት፤ ስለዚህ እርሱን አሳልፎ
የሚሰጥበትን ምቹ ጊዜ ይጠባበቅ ነበር።

## የጌታ እራት

*14፥12-26 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥17-30፤ ሉቃ 22፥7-23*
*14፥22-25 ተጓ ምብ — 1ቆሮ 11፥23-25*

12የፋሲካ በግ በሚታረድበት በቂጣ በዓል
የመጀመሪያው ቀን፣ ደቀ መዛሙርቱ ወደ
ኢየሱስ ቀርበው፣ "የፋሲካ እራት የት እንድ
ናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?" አሉት።
13እርሱም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን
እንዲህ ሲል ላካቸው፤ "ወደ ከተማ ሂዱ፤
እንስራ ውሃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል፤
14ወደሚገባበት ቤትም ተከተሉት፤ የቤቱንም
ጌታ፣ " 'መምህሩ፣ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር
የፋሲ ካንራት የምበላበት የእንግዳ ማረፊያ
የትኛው ነው?' ብሎአል በሉት፤ 15እርሱም
በሰገነቱ ላይ የተሰናዳና የተነጠፈ ሰፊ
አዳራሽ ያሳያችኋል፤ እዚያ አዘጋጁልን።"
16ደቀ መዛሙርቱም ወጥተው ወደ
ከተማዪቱ ሄዱ፤ ማንኛውም ነገር ኢየሱስ
እንዳላቸው ሆኖ አገኙት፤ ፋሲካውንም
አሰናዱ።
17በመሸም ጊዜ ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ
ጋር መጣ። 18በማእድ ላይ ሳሉም፣ "እውነት
እላችኋለሁ፣ ከመካከላችሁ አንዱ፣ አብሮኝ
የሚበላው እርሱ አሳልፎ ይሰጠኛል"
አላቸው።
19እነርሱም አዘኑ፤ እያንዳንዳቸውም፣
"እኔ እሆንን?" ይሉት ጀመር።
20እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ከዐሥራ
ሁለቱ አንዱ፣ ከእኔ ጋር እጁን በወጭቱ ውስጥ
የሚያጠልቀው ነው። 21የሰው ልጅስ ስለ
እርሱ እንደ ተጻፈው ይሄዳል፤ የሰውን ልጅ
አሳልፎ ለሚሰጥ ለዚያ ሰው ግን ወዮለት፤

14፥10 ማቴ10፥4፤ ማር3፥16-19
14፥12 ዘፀ12፥1-11፤ ዘዳ16፥1-4፤ 1ቆሮ5፥7
14፥15 ሐሥ1፥13
14፥20 ዮሐ13፥18-27
14፥21 ማቴ8፥20
14፥22 ማቴ14፥19
14፥23 1ቆሮ10፥16
14፥24 ማቴ26፥28
14፥25 ማቴ3፥2
14፥26 ማቴ21፥1
14፥27 ዘካ13፥7
14፥28 ማር16፥7
14፥30 ቊ66-72፤ ሉቃ22፥34፤ ዮሐ13፥38
14፥31 ሉቃ22፥33፤ ዮሐ13፥37

ያ ሰው ባይወለድ ይሻለው ነበር።"
22ሲበሉም እንጀራ አንሥቶ ባረከ፤
ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸውና፣
"እንኩ፤ ይህ ሥጋዬ ነው" አላቸው፣
23ጽዋውንም አንሥቶ፤ አመስግኖም
ሰጣቸው፤ ሁሉም ከዚያ ጠጡ።
24ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ "ይህ ስለ
ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ[a] ኪዳን ደሜ
ነው፤ 25"እውነት እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር
መንግሥት አዲሱን የወይን ፍሬ እስከምጠጣ
በት እስከዚያች ቀን ድረስ ዳግም ይህን
አልጠጣም።"
26ከዚህ በኋላ መዝሙር ዘምረው ወደ
ደብረ ዘይት ተራራ ወጡ።

## ጴጥሮስ እንደሚክደው ኢየሱስ አስቀድሞ ተናገረ

*14፥27-31 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥31-35*

27ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤
"እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ ሁላችሁ
ትክዱኛላችሁ፤
" 'እረኛውን እመታለሁ በጎቹም
ይበተናሉ' "
28ከተነሣሁ በኋላ ግን፣ ቀድሜአችሁ ወደ
ገሊላ እሄዳለሁ።"
29ጴጥሮስም፣ "ሁሉም ቢሰናከሉ እንኳ
እኔ አላደርገውም" አለ።
30ኢየሱስም፣ "እውነት እልሃለሁ፤
በዚህች ሌሊት ዶሮ ሁለት[b] ጊዜ ሳይጮኽ፣
ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" አለው።
31ጴጥሮስም፣ "ከአንተ ጋር ብሞት እንኳ
ከቶ አልክድህም" በማለት ይበልጥ አጽንቶ
ተናገረ። ሁሉም ደግሞ እንደዚሁ አሉ።

## ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ጸለየ

*14፥32-42 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥36-46፤ ሉቃ 22፥40-46*

32ከዚህ በኋላ ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ

*[a]14፥24 አንዳንድ ቅጆች አዲስ የሚለው ቃል የላቸውም።*
*[b]14፥30 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሁለት ጊዜ የሚለው ሐረግ የላቸውም።*

የዘላለምን ሞት ያመጣል (ዮሐ 3፥18)።
14፥9 **ያደረገችው መታሰቢ ሆኖ፤** ማቴ 26፥13 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
14፥14 **የፋሲካን እራት፤** ማቴ 26፥2 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
14፥21 **ባይወለድ፤** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትን የሚያየውና የሚገመግመው ከመንፈሳዊና ከዘላለማዊ ሕይወት አንጻር ነው። አንድ ሰው ወደዚህ ዓለም መጥቶ ኢየሱስን ጌታውና አዳኙ መሆኑን ሳይቀበል ቀርቶ ከዚህ የተነሣ በገሃነም ለዘላለም የሚሠቃይ ከሚሆን፣ ባይወለድ ይሻለው እንደ ነበር ጌታ ኢየሱስ አረጋገጠ (ዮሐ 6፥64 እና ማብ ይመ)።
14፥22 **እንጀራ ... ሥጋዬ፤** ሉቃ 22፥20 እና ማብራሪያውን፤ 1ቆሮ 11፥24-25፡27 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
14፥24 **የአዲስ ኪዳን ደሜ፤** የክርስቶስ ደም ለእኛ ይቅርታንና ድነትን ያስገኝ ዘንድ ፈሰሰልን። በመስቀል ላይ መሞቱ በእግዚአብሔርና ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርገው በሚቀበሉ መካከል አዲስ ኪዳን መሠረተ (ኤር 31፥31-34 እና ማብ ይመ)። ንስሓ የሚገቡና በክርስቶስ በማመን ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱ ሁሉ ይቅር ይባላሉ፤ ከሰይጣን ኀይል ትድግናን ያገኛሉ፤ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወትን ይቀበላሉ፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ፤ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ፤ ምሕረትን፣ ጸጋን፣ ብርታትንና ርዳታን ያገኙ ዘንድ በማንኛውም ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መብት ተሰጥቷቸዋል (ማቴ 26፥28 እና ማብ፤ ዕብ 4፥16፤ 7፥25 ይመ)።
14፥32 **ጌቴሴማኒ ... ስጸልይ፤** ኢየሱስ ያከናወነው ተግባር አማኞች በታላቅ ጭንቀት ወይም ሐዘን ውስጥ በሚገኙበት ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመለክት ምሳሌ ነው፤ (1) በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ተመለስ (ቊ 32:35-39)፤ (2) የወንድሞችን ርዳታ ፈልግ

ሄዱ፤ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን፣ "እኔ
ስጸልይ እናንተ እዚህ ቈዩ" አላቸው። [33]ጴጥሮ
ስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስንም ይዞ ሄደ፤
እጅግ ያዝን ይጨነቅ ጀመር። [34]ደግሞም፣
"ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤
እዚሁ ሁኑና ነቅታችሁ ጠብቁ" አላቸው።
[35]ጥቂት ዕልፍ ብሎም በምድር ላይ
በመውደቅ ቢቻል ሰዓቱ ከእርሱ እንዲያልፍ
ጸለየና፣ [36]"አባ[a]፤ አባት ሆይ፤ ሁሉ ነገር
ይቻል ሃልና ይህን ጽዋ ከእኔ አርቀው፤ ነገር
ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ
ይሁን" አለ።
[37]ተመልሶም ሲመጣ ደቀ መዛሙርቱን
ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም እንዲህ
አለው፣ "ስምዖን ሆይ፣ ተኝተሃልን? አንድ
ሰዓት እንኳ ነቅተህ መጠበቅ አቃተህ? [38]ወደ
ፈተና እንዳትገቡ ትጉ፤ ጸልዩም፤ መንፈስ
ዝግጁ ነው፣ ሥጋ ግን ደካማ ነው።"
[39]እንደ ገናም ሄዶ መጀመሪያ የጸለየውን
ደግሞ ጸለየው። [40]ዳግመኛም ሲመለስ
ዐይናቸውን እንቅልፍ ከብዶት ተኝተው
አገኛቸው፤ የሚመልሱለትንም አያውቁም
ነበር።
[41]ሦስተኛ ጊዜም መጥቶ እንዲህ አላቸው፤
"አሁንም እንደ ተኛችሁና እንዳረፋችሁ
ናችሁ? ይበቃል! ሰዓቲቱ ደርሳለች፤
እነሆ፤ የሰው ልጅ ለኀጢአተኞች እጅ
አልፎ ይሰጣል። [42]ተነሡ፤ እንሂድ፤ አሳልፎ
የሚሰጠኝ መጥቶአል።"

14፥33 ማቴ4፥21
14፥34 ዮሐ12፥27
14፥35 ቍ41፤ ማቴ26፥18
14፥36 ማቴ20፥22፤ 26፥39፤ ሮሜ8፥15፤ ገላ4፥6
14፥38 ማቴ6፥13፤ ሮሜ7፥22፡23
14፥41 ቍ35፤ ማቴ26፥18
14፥43 ማቴ10፥4
14፥45 ማቴ23፥7
14፥49 ኢሳ53፥7-12፤ ማቴ1፥22፤ 26፥55
14፥50 ቍ27

## ኢየሱስ ተያዘ

*14፥43-50 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥47-56፤ ሉቃ 22፥47-50፤ ዮሐ 18፥3-11*

[43]ወዲያው እየተናገረ ሳለ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ይሁዳ መጣ፤ አብረውትም ሰይፍና
ዱላ የያዙ፣ ከካህናት አለቆች፣ ከጸሐፍትና
ከሽማግሌዎች የተላኩ ብዙ ሰዎች ነበሩ።
[44]አሳልፎ የሚሰጠውም፣ "እኔ የምስመው
እርሱ ነውና ያዙት፤ ተጠንቅቃችሁም
ውሰዱት" በማለት አስቀድሞ ምልክት
ሰጥቶአ ቸው ነበር። [45]እንደ ደረሰም
ወዲያው ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ "መምህር
ሆይ!" ብሎ ሳመው፤ [46]ሰዎቹም ኢየሱስን
ያዙት አሰሩትም። [47]በአቅራቢያው ቆመው
ከነበሩት አንዱ ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን
አገልጋይ ጆሮ ቈረጠ።
[48]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እንደ
ወንበዴ በሰይፍና በቈመጥ ልትይዙኝ
መጣችሁን? [49]በየዕለቱም በቤተ መቅደስ
እያስተማርሁ ከእናንተ ጋር ስኖር
አልያዛችሁኝም፤ መጻሕፍት ይፈጸሙ
ዘንድ ይህ ሆነ።" [50]በዚህ ጊዜ ሁሉም
ትተውት ሸሹ።
[51]ዕርቃኑን ለመሸፈን በፍታ ያገለደመ
አንድ ወጣት ኢየሱስን ይከተል ነበር።
ሰዎቹም ይህን ወጣት በያዙት ጊዜ፣
[52]ግልድሙን ጥሎ ዕራቍቱን ሸሸ።

[a]*14፥36* በአራማይክ ቋንቋ አባት የሚጠራበት ነው።

---

(ቍ 33-34፡42)፤ (3) እግዚአብሔር ለአንተ የሚያስብ ሰማያዊ አባት መሆኑን በልብህ አረጋግጥ (ቍ36)፤ (4) እግዚአብሔርን መታመኛህ አድርግ፤ ለፈቃዱም ራስህን አሳልፈህ ስጥ (ቍ 36)፤ ስለ ክርስቶስ ሥቃይ የተመለከቱትን ዐሥር ደረጃዎች ለማስተዋል፣ ማቴ 26፥37 እና የሚከተሉትን ቍጥሮች ይመልከቱ፤ እንዲሁም በተከታታዩ የሰፈሩትን ማብራሪያዎች ይመልከቱ።

**14፥35 ሰዓቱ ከእርሱ እንዲያልፍ፤** ማቴ 26፥39 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**14፥37 አንድ ሰዓት እንኳ ነቅተህ መጠበቅ፤** ጴጥሮስና ሌሎች ደቀ መዛሙርት ነቅቶ መጠበቅንና መጸለይን ችላ አሉ፤ ይህም በዚህ የፈተና ወቅት ከውድቀት የሚጠብቃቸው ብቸኛ መንገድ ነበር (ቍ 50)። ጸሎት ካላደረግን በቀር የክርስትና ሕይወታችን ከውድቀት እንደማያመልጥ የተረጋገጠ ነው (ሐሥ 10፥9 እና ለአንድ ሰዓት ሕይወትን ለጸሎት አሳልፎ ስለ መስጠት የቀረበውን ማብ ይመ)።

**14፥46 ያዙት፤** ከክርስቶስ መያዝ አንሥቶ እስከ ስቅለቱ ያለውንና በቅደም ተከተል የተከናወነውን ሁናቴ ለመረዳት ማቴ 26፥57 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**14፥50 ሁሉም ትተውት ሸሹ፤** ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ማለትም ከድል በኋላ ሊከሡት የሚችለውን የመጋቢዎችን ወይም የሽማግሌዎችን መንፈሳዊና ግብረገባዊ ውድቀት፣ ኢየሱስ በተያዘ ጊዜ ከጴጥሮስና ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት መንፈሳዊ ድክመት ጋር ከቶ ማወዳደር የለብንም። ደቀ መዛሙርት ያፈገፈጉት ቀጥሎ ካሉት ምክንያቶች የተነሣ ነው፤ (1) ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት በድካማቸው ወቅት ገና በአዲሱ ኪዳን ሥር አልነበሩም። አዲሱ ኪዳን የክርስቶስ ደም በመስቀሉ ላይ እስከ ፈሰሰ ድረስ እውን አልሆነም ነበር (ዕብ 9፥15-20)።

(2) ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ እውን የሚሆነውን አዲስ ልደት ወይም ዳግም ልደት በአዲስ ኪዳን ሙሉ እሳቤ መሠረት ገና ተመክሯቸው አላደረጉም ነበር። በጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ ዕለት ጌታ፣ «እፍ» በማለት፣ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» እስካለበት ድረስ መንፈስ ቅዱስ በልብ ውስጥ በማደርና በመቀደስ ሀልዎት በእነርሱ ውስጥ አልነበረም (ዮሐ 20፥22)። በዚያን ወቅት የደቀ መዛሙርቱ ጽንቶ አለመገኘት ከክፋት ሳይሆን ከድካም የመጣ ነበር።

(3) ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ክርስቶስን ትተው በሸሹ ጊዜ መሥዋዕት የሆነው የክርስቶስ የመስቀል ሞት ያለው እንድምታ ምን እንደ ሆነ ግንዛቤ እንዳገኙት ክርስቲያን ወገኖች የማስተዋል ዕድል አልነበራቸውም (ሮሜ 6)፤ ወይም ክርስቶስ ከሞት በመነሣቱ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለበት ጽኑ እምነት አልነበራቸውም።

በሌላ አገላለጽ የአገልግሎት መልሶ አቋቋሚ መሪዎች ከግል ኀጢአታቸውና ከግብረ ገባዊ ቸልተኝነታውን የተነሣ፣ የመጋቢነትን መስፈርት በፈቃዳቸው ከግል ሕይወታቸውና ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው ላስወጡት፣ «ሰው እኮ፥ ምንጊዜም ደካማ ነው» በሚለው ሰበብ ራሳቸውን ለሸነገሉት ይህ ምንባብ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም (በገጽ 1925 ላይ፣ *«የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

የሸንጎ አባልና የእግዚአብሔርን መንግሥት
ይጠባበቅ የነበረው የአርማትያሱ ዮሴፍ
በድፍረት ወደ ጲላጦስ ሄዶ የኢየሱስን
ሥጋ ለመነው። 44ጲላጦስም እንዲህ
በቶሎ መሞቱን ሲሰማ ተደነቀ፤ የመቶ
አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ምን ያህል ጊዜ
እንደ ሆነ ጠየቀው፤ 45መሞቱንም ከመቶ
አለቃው ካረጋገጠ በኋላ ሥጋውን ለዮሴፍ
ሰጠው። 46ዮሴፍም በፍታ ገዛ፤ ሥጋውንም
አውርዶ በበፍታው ከከፈነው በኋላ፣ ከዐለት
በተወቀረ መቃብር አኖረው፤ የመቃብሩንም
ደጃፍ በድንጋይ ገጠመው። 47ማርያም
መግደላዊትና የዮሳ እናት ማርያም የት
እንዳኖሩት ይመለከቱ ነበር።

## ትንሣኤው

*16፥1-8 ተጓ ምብ — ማቴ 28፥1-8፤*
*ሉቃ 24፥1-10*

**16** ሰንበት ካለፈ በኋላ መግደላዊት
ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያ
ምና ሰሎሜ ሄደው የኢየሱስን ሥጋ
ለመቀባት ሽቱ ገዙ። 2በሳምንቱ መጀመሪያ
ቀን ጠዋት በማለዳ፣ ገና ፀሓይ እንደ
ወጣች፣ ወደ መቃብሩ በመሄድ ላይ ሳሉ፣
3"ድንጋዩን ከመቃብሩ ደጃፍ ላይ ማን
ያንከባልልልናል?" በማለት እርስ በርሳቸው
ይነጋገሩ ነበር።
4ቀና ብለው ሲመለከቱ፣ በጣም ትልቅ
የነበረው ድንጋይ ከደጃፉ ላይ ተንከባሎ
አዩ። 5ወደ መቃብሩ እንደ ገቡም፣ ነጭ
ልብስ የለበሰ ጐልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ
አዩና ደነገጡ።
6እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤
"አትደንግጡ፤ የምትፈልጉት የተሰቀለውን
የናዝሬቱን ኢየ ሱስን ነው፤ እርሱ
ተነሥቶአል፤ እዚህ የለም፤ እርሱን
ያኖሩበት ስፍራ ይኸውላችሁ። 7ነገር ግን
ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱና ለጴጥሮስ፣
'ቀድሞአችሁ ወደ ገሊላ ይሄዳል፤ እንደ
ነገራችሁ እዚያ ታገኙታላችሁ' ብላችሁ
ንገሯቸው።"
8ሴቶቹም እየተንቀጠቀጡና እየተደነቁ
ከመቃብሩ ሸሽተው ወጡ፤ ፈርተው ስለ
ነበር ለማንም አንዳች አልተናገሩም።
9በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ማለዳ ከሙታን
ከተነሣ በኋላ፣ ሰባት አጋንንት ላወጣላት
ለማርያም መግደላዊት በመጀመሪያ ታየ።
10እርሷም ሄዳ፣ ከእርሱ ጋር የነበሩት እያዘኑ
ሲያለቅሱ አግኝታ እርሱ ሕያው መሆኑንና
ለእርሷም መታየቱን ነገረቻቸው፤ 11እነርሱ
ግን አላመኗትም።
12ከዚህ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱ
ወደ ገጠር ሲሄዱ በሌላ መልክ ታያቸው።
13እነርሱም ተመልሰው ይህንኑ ለቀሩት
ነገ ሯቸው፤ ይሁን እንጂ እነርሱንም
አላመኗቸውም።
14ከዚያም በኋላ አሥራ አንዱ በማዕድ ላይ
ሳሉ ተገለጠላቸው፤ ከተነሣ በኋላ ያዩት
ሰዎች የነገሯቸውን ስላላመኗቸው፣
አለማመናቸውንና የልባቸውን ድንዳኔ
ነቀፈ። 15እንዲህም አላቸው፤ "ወደ ዓለም
ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ
ስበኩ፤ 16ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ
ግን ይፈረድበታል። 17የሚያምኑትን እነዚህ
ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን
ያወጣሉ፤ በአዲስ ልሳንም ይናገራሉ፤
18እባቦችን በእጃቸው ይይዛሉ፤ የሚገድል
መርዝ ቢጠጡ እንኳ አይጐዳቸውም፤
እጃቸውንም በሕመምተኞች ላይ ይጭናሉ፤
እነርሱም ይፈወሳሉ።"
19ጌታ ኢየሱስ ይህን ከተናገራቸው
በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በእግዚአብሔርም
ቀኝ ተቀመጠ። 20ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ
ወጥተው፣ በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፤
ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፤
ትምህርታቸውንም ተከትለው በሚፈጸሙ
ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር[1]።

[1]*16፥20 አንዳንድ የጥንት ቅጆች በቍ 9-20 ላይ ያለው ክፍል የላቸውም፡*

15፥45 ቍ39
15፥46 ማር16፥3
15፥47 ቍ40
16፥1
ሉቃ23፥56፤
ዮሐ19፥39:40
16፥3 ማር15፥46
16፥5 ዮሐ20፥12
16፥6 ማር1፥24
16፥7 ማር14፥28፤
ዮሐ21፥1-23
16፥9 ማር15፥47፤
ዮሐ20፥11-18
16፥11 ቍ13:14፤
ሉቃ24፥11
16፥12
ሉቃ24፥13-32
16፥14
ሉቃ24፥36-43
16፥15
ማቴ28፥18-20፤
ሉቃ24፥47:48፤
ሐሥ1፥8
16፥16
ዮሐ3፥16:18:36፤
ሐሥ16፥31
16፥17 ማር9፥38፤
ሉቃ10፥17፤
ዮሐ4፥48፤
ሐሥ2፥4፤
5፥16፤ 8፥7፤
10፥46፤ 16፥18፤
19፥6:13-16፤
1ቆሮ2፥10:28:30፤
13፥1፤ 14፥2-39
16፥18
ሉቃ10፥19፤
ሐሥ6፥6፤
28፥3-5

**16፥6 እርሱ ተነሥቶአል፤** ማቴ 28፥6 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**16፥9-20 የኢየሱስ መገለጥ፤** ይህ ሐረግ በዋናው ጽሑፍ ላይ ባይገኝም አጠቃላይ ሐሳቡ እንደሚከተለው ነው፣ በቍ 9-20 ላይ ያለው ክፍል እጅግ ጥንታዊ በሆነው ጽሑፍ ላይ የሌለ ቢሆንም እንኳ፣ በሌሎቹ የጥንት ጽሑፎችና በዓለም ሁሉ በሚገኙት አብዛኛዎቹ የግሪክ ጽሑፎች ላይ ይገኛል። ስለዚህ ብዙኀኑ ሊቃውንት ማንኛውም ጽሑፍ በአብዛኛው ጥንታዊ ጽሑፍ እስከ ተረጋገጠ ድረስ፣ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊ ጽሑፍ አካል ሳይሆን አይቀርም በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፤ ስለዚህ ቍ 9-20 እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለው የእግዚአብሔር ቃል አካል መሆን አለበት።

**16፥17 እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤** በገጽ 1527 ላይ፣ *"አማኞች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**16፥18 እባቦችን በእጃቸው ይይዛሉ፤** መንፈሳዊነትን ለማረጋገጥ ሲባል እባብን በእጅ መያዝ ወይም መርዝ መጠጣት የመንፈሳዊነት ብቃት መለኪያ ወይም የሰማዕትነት መፈተኛ ሥርዐት ተደርጎ መታየት የለበትም። እነዚህ ምልክቶች የክርስቶስን የዕለት ተዕለት ዐደራ ሲያከናውኑ እንዲህ ያለ ያልተጠበቀ አደጋ ለሚያጋጥማቸው አማኞች የተሰጡ ተስፋዎች ናቸው። በራስ አነሣሽነት በማያስፈልግ አደጋ ወይም ፈተና ውስጥ በመግባት እግዚአብሔርን መፈተን ኀጢአት ነው (ማቴ 4፥5-7፤ 10፥23፤ 24፥16-18)።